# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት፣የማስፈጸም አቅም ግንባታ እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ስትራቴጂ

**(የፀደቀ)**

ግንቦት 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ........ 2

መቅድም........ 3

I. ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና አቅም ግንባታ መነሻ ሁኔታ........ 9

1. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አፈፃፀም........ 9
2. የመንገድ ልማትና ማስፋፋት አፈፃፀም........ 13
3. የውሃ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም........ 15
4. የኢነርጂ የማስፋፋት ሥራዎች አፈፃፀም........ 16
5. የከተሞች መሠረተ ልማትና ማስፋፋት ሥራዎች አፈፃፀም........ 17
6. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ የጋራ የሆኑ የነበሩና ያሉ ማነቆዎች........ 18

II. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማትና ማስፈፀም አቅም ግንባታ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች........ 30

III. በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የልማት ዕቅዳችን በኮንስትራክሽን ሴክተር የታቀዱ ፕሮግራሞችና ዋና ዋና ሥራዎች........ 39

1. የመንገድ ልማት ኘሮግራም........ 39
2. የባቡር መሠረተ ልማት ኘሮግራም........ 40
3. የስኳር ልማት ዘርፍ ኘሮግራም........ 41
4. የማዳበሪያ ፋብሪካ ልማት ኘሮግራም........ 42
5. የቤቶች ልማት ኘሮግራም........ 43
6. የውሃ ልማት ኘሮግራም........ 45
7. የኢነርጂ አቅርቦት ልማት ኘሮግራም........ 48
8. የኮብል ስቶን እና የከተማ መሠረተ ልማት ፕሮግራም........ 49
9. በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍላጎት........ 51

IV. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ዋና ዋና ጉዳዮችና የአፈፃፀም ሥልቶች........ 58

1. ዓላማዎችና መርሆዎች........ 58
2. የአነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ኘሮግራም........ 59
3. የሰው ኃይል ልማት ፕሮግራም........ 60
4. የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ኩባኒያዎች ልማት ፕሮግራም........ 62
5. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት አቅም ግንባታ ፕሮግራም........ 64
6. የኮንስትራክሽን ግብዓት አቅርቦትና ማምረቻ ተቋማት አቅም ግንባታ ፕሮግራም........ 65
7. ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የተሻሉ ቴክኒዎሎጂዎችን መጠቀም ፕሮግራም........ 66
8. የመንግስትና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ፕሮግራም........ 67
9. የኮንስትራክሽን ማስፈፀሚያ የፖሊሲ የህግና አሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ ፕሮግራም........ 68
10. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኤግዚቢሽንና ንግድ ትርኢትና ምክክር መድረክ........ 70

V. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ባለሚናዎች፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ተቋማትና ሚናቸው........ 71

1. የልማት ዕቅዶቹን ለማሳካት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ባለሚናዎች፤........ 71
2. የስትራቴጂው አስፈጻሚ አካላትና ድርሻ........ 72

VI. የክትትልና የግምገማ ሥርዓት........ 74

VII. ማጠቃለያ........ 78

# መግቢያ

ሀገራችን በ2012 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ ለማስቻል የተጠናከሩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ለዚሁ ዕቅድ ስኬት መሠረት ለመጣል መንግስት ባስቀመጠው የልማት አቅጣጫ የዕድገትና የትንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ በባቡር መሠረተ ልማት፣ በመንገድ፣ በኃይል ማመንጫ፣ በስኳር ማስፋፊያ፣ በመስኖ፣ በተቀናጀ የቤት ልማት፣ በዩኒቨርሲቲ ግንባታ፣ በከተሞች የመሠረተ ልማት ግንባታና በማዳበሪያ ምርት አቅርቦት ግዙፍ የልማት ሥራዎችን በከፊል ወደ ግንባታ በመግባት ሂደትና ቀሪዎቹም በፍጥነት ለማስገባት ከፍተኛ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ከዚህ እንቅስቃሴ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የዕቅዱ መሠረታዊ ዓላማ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

በመንግስት የተነደፈው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከሚፈፀምባቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል አንዱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማት ነው፡፡ በሀገሪቱ ለዘመናት ስር ሰዶ የኖረውን የድህነት አረንቋ ከሥሩ ለመናድ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በስፋት መከናወናቸው መሠረታዊ በመሆኑ ለዕቅዱ ስኬታማነት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለለውጡ መፋጠን ማዘጋጀትና ማብቃት ይጠይቃል፡፡ በኢንዱስትሪው ውስጥ ባለው የተዛባ የገበያ ውድድር እና ደካማ የማስፈጸም አቅም የኮንስትራክሽን ሥራዎች ዋጋ ከሚፈለገው በላይ እየናረ በመሄዱ መንግስት የሚያስፈጽማቸው የኮንስትራክሽን ፕሮግራሞች በውድ ዋጋ እንዲሰሩ የሚያስገድድ ከመሆኑም ባሻገር ከዚህ ጋር ተጣምሮ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችንና ተግባሮችን ከወዲሁ ለይቶ ለማስወገድ መታገል ለዕቅዱ መሳካት ወሳኝ ይሆናል፡፡

በሀገራችን የተገነባው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የደረሰበት ደረጃ ከታቀደው ዕቅድ አንፃር ሰፊ የአቅም ክፍተት ይታይበታል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ለሚገኙት አስፈፃሚ አካላት፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የግንባታ ማሽነሪዎችና የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦትና ፍላጎት ረገድ የሚታየውን የአቅም ክፍተት ለመቅረፍ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ዐቅዶ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር የሀገሪቱን የግንባታ አገልግሎቶችን፣ የግንባታ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ነባራዊ አቅም እንዲሁም የአቅም ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮች ቀርፎ ኢንዱስትሪውን ለመምራት  እና ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የማስፈጸም አቅም ግንባታና የድጋፍ ማእቀፍ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

ስትራቴጂው ሰባት ዋና ዋና ምዕራፎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማትና አቅም ግንባታ በሴክተር ልማቶቹና በኢንዱስትሪው ዙሪያ የተደረገውን ዳሳሳ በአጭሩ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ የልማት ኘሮግራሞቹ እንዲሳኩ በኢንዱስትሪው የሚታዩ ክፍተቶች መነሻ በማድረግ ትኩረት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች ጠቅለል አድርጎ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ምዕራፍ ሶስት በልማት ፕሮግራሞቹ የተያዙ ዋና ዋና ሥራዎች ተገልፀዋል፡፡ ከምዕራፍ አራት እስከ ሰባት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽንኑን ዕቅድ ማስፈጸሚያ ዋና ዋና ጉዳዮች፣ የአፈፃፀም ስልቶች፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ባለሚናዎችና ሚናቸው  እንዲካተት ተደርጓል፡፡

# መቅድም

## 1. የአምስት ዓመት እቅድ፣ ኮንስትራክሽን እና የስራ ዕድል ፈጠራ

ከጥቂት ዓመታት በፊት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታን በአዲስ አበባ ውጪም ጭምር ለማስፋፋት ተወስኖ ስራ ተጀምሮ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ ሥራ በአንድ በኩል የመጠለያ ችግርን ለመፍታትና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች የቤት ባለቤት እንዲሆኑ በማስቻል የገቢ ክፍፍል ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ታስቦ የታቀደ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በግንባታው ሂደት ሰፊ የስራ ዕድልን ለመፍጠር፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞችን ለማስፋፋት የታሰበ ነበር፡፡ይሁንና ከአዲስ አበባ ውጪ ቤቶቹ ከተገነቡ በኋላ ፍላጐቱ በታሰበው መጠን ባለመሆኑ ከአዲስ አበባ ውጪ ያለው ግንባታ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

ይህ ስራ በመጨረሻ ቤቶቹን የሚገዛ ሰው በታቀደውና በተገነቡት ቤቶች መጠን ባለመገኘቱና በርካታ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሌሎች ችግሮችም የነበሩት ነው፡፡በመጀመሪያ ደረጃ ቤቶቹ ሙሉ በሙሉ ክልሎች በሚበደሩት ገንዘብ የሚፈፀም በመሆኑ የክልሎች የፋይናንስ ሁኔታን አስቸጋሪ ከማድረጉ ባሻገር የብድር አቅርቦትን ከሌሎች አጣዳፊ ስራዎች ጋር በመጋራቱ ለማክሮ ኢኮኖሚው አለመረጋጋት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረከተ ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የግንባታው ዘርፍ በከፍተኛ ፍጥነት ከማደጉ ጋር ተያይዞ በበቂ መጠን እናመርተው የነበረው ሲሚንቶ ሳይቀር ከገበያው ፍላጎት ጋር ባለመራመዱ ከውጭ እንድናስመጣ የተገደድንበትና የሌሎች የኮንስትራክሽን ነክ ምርቶች ፍላጎትም የናረበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ይህ በአንድ በኩል የውጭ ምንዛሪ እጥረታችንን ሲያባብስ በሌላ በኩል ደግሞ የምርቶቹን ዋጋ በማናር የቤቶቹም ዋጋ እንዲጨምርና የገዢዎች አቅምን መፈታተን ምክንያት ሆኗል፡፡ ለፕሮጀክቶቹ መጓተትም አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡በመጨረሻም ግንባታውን የሚያስተባብሩ ኮንትራክተሮችና የሚፈፅሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች በበቂ ፍጥነትና መጠን ማዘጋጀት ባለመቻሉ ፕሮጀክቶቹ እንዲጓተቱ፣ ጥራታቸው እንዲጓደልና ወጪያቸው እንዲንር ምክንያት ሆኗል፡፡እነዚህን የተወሳሰቡ ችግሮች ተሸክሞ የመጣው የክልሎች የቤቶች ግንባታ በአምስት ዓመት ዕቅዳችን ከአዲስ አበባ ውጭ ትኩረት የሚሰጠው ዘርፍ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

የፈጣን ልማት ዕቅድ ከአንዳች ዓይነት የኮንስትራክሽን ስራ ውጪ ስለማይታሰብ የአምስት ዓመት ዕቅዳችንም ለቤቶች ግንባታ ትኩረት ባይሰጥም ሰፊ የኮንስትራክሽን ስራን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የመንገድ፣ የባቡር፣ የመስኖ ስራዎች ከፍተኛ የኮንስትራክሽን አቅምን የሚጠይቁ በመሆናቸው የአገር ውስጥ ኮንትራክተሮችንና ኮንሰልታንቶችን በብዛት ማዘጋጀትን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በየዘርፉ የኮንትራክተር እጥረት እንዳያጋጥም የተሞካከሩ ስራዎች ቢኖሩም፣ የመንገድ የኮንትራክተሮች እጥረትን በመቅረፍ የትራንስፖርት ሚኒስቴር እንዲይዘው የተጠየቀ በተነፃፃሪ ሰፋ ያለ የአቅም ግንባታ ስራ ቢኖርም ይህ ስራ በዕቅዱ ካለው ድርሻ ጋር የሚመጥን ትኩረት ሰጥተነዋል ማለት አይቻልም፡፡

ምንም እንኳ የአምስት ዓመታት ዕቅዳችን ለከተሞች ቤት ግንባታ ትኩረት ባይሰጥም (ከአዲስ አበባ ውጭ) በተግባር ግን ለቤቶች ግንባታ ትኩረት በሰጠንበት ወቅት ከስራናቸው ቤቶች በእጅጉ በሚበዙ የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክቶችን ይዘናል፡፡ ቢያንስ አስር ዩኒቨርስቲዎችን እንገነባለን፡፡ በእያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ የሚገነባው የቤቶች ብዛት በክልል ከተሞች ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው የቤት ግንባታ በእጅጉ የላቀ ይሆናል፡፡ በመካከድ ላይ ባሉ ቢያንስ ሁለት የስኳር ፋብሪካዎችና በተጨማሪ ስምንት ያህል የስኳር ፋብሪካዎች ሰፊ የቤቶች ግንባታ እደሚኖር መገመት አያዳግትም፡፡

ከአስር በማያንሱ ከማዳበርያ ፋብሪካዎች ግንባታ ጋር ተያይዞም እንደዚሁ የቤቶች ግንባታ ስራ ይኖራል፡፡ በሌላ አነጋገር በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከ30 የማያንሱ መካከለኛ ከተሞችን ከዜሮ፣ ጀምረን ስለምንገነባ በፕላን እንዲመሩ ማድረግ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ የቁጠባ ባህል ከማበደር ጋር ተያይዞ የሚሰሩ ቤቶችም ይኖራሉ፡፡ ይህ የቤት ግንባታ ስራ እስካሁን ከተሞከረው በእጅጉ የሰፋና የተወሳሰበ ቢሆንም በየፕሮጀክቱ ተበጣጥሶ አልፎ አልፎ ከሚታይ በስተቀር ከስራው መጠንና ውስብስብነት ጋር የሚመጣጠን ትኩረት ተሰጥቶታል ማለት አይቻልም፡፡

ከዋና ዋና የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ተያይዞ የሚሰራው የኮንስትራክሽን ስራና ከኢንዱስትሪ ከተሞች ግንባታ ጋር ተየይዞ የሚሰራው ቢያንስ የ30 ከተሞች ግንባታ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበበ በመንግስት የሚሰራ የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታና በሁሉም ክልሎች በግሉ ዘርፍ የሚሰሩ የግንባታ ፕሮጀክቶችም እንደሚኖሩ መገመት ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ከተሞች በመሰረተ ልማት ግንባታ ሂደት የሚያስሯቸው ሰዎች በተለይም የኮብል ስቶን ግንባታ ፕሮጀክቶች በአስር ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ጊዜያዊ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች እንደሚሆኑ መገመት ይቻላል፡፡ እነዚህን በየፕሮጀክቱና በየአካባቢው ነጣጥለን ስናያቸው የቆየን ፕሮጀክቶችን አንድ ላይ አጣምረን ማየት ስንጀምር እጅግ መሰረታዊ

አንድምታ ያላቸው መሆናቸውና የአምስት ዓመቱ ዕቅድ መሳካት አለመሳካቱን የሚወስኑ እንደሚሆኑ መገመት አያዳግትም፡፡ ዋና ዋና እንድምታዎችን በአጭሩ ቀጥሎ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

## 2. የኮንስትራክሽን ስራዎች እንድምታ

### 2.1. የአቅም ግንባታ እንድምታ

ዋና ዋና የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማስፈፀም የሚፈለገው የኮንትራክተርና ኮንሰልታንት አቅም ግንባታ ጉዳይ በጨረፍታም ቢሆን ታይቷል፡፡በመሳሪያ አቅርቦት፣ በኩባንያ አደረጃጀት፣ በፕሮጀክት አሰጣጥ፣ በተወሰነ ደረጃ በስልጠና ረገድ ምን መስራት እንዳለበት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ያስቀመጣቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ የፕሮጀክቶች ባለቤቶችም በየራሳቸው መንገድ ችግራቸውን ለማቃለል የነደፏቸው መፍትሄዎች መኖራቸው አልቀረም፡፡ ይሁንና ሁሉም በየዘርፉ ያቀደው ተግባር ተቀናጅቶ አንድ ወጥ ዕቅድ ሆኖ መውጣቱ እና በየዘርፉ የተነደፉ ዕቅዶች በዝርዝር ተገምግመው ጥራታቸውንና ለተግባራቱ ያለውን የማስፈጽም ዝግጁነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በተናጠል የተዘጋጁ ዕቅዶች በዝርዝር ተፈትሸው ይህ የሀገር አቀፍ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ከተሞች የኮብል ስቶን ሥራን ለመሥራት የሚያስችላቸው የየራሳቸው ዕቅድ አላቸው፡፡በቀጣይም የስልጠናው ስራ በዚያው ሊያልቅ እንደሚችል አድርጎ መገመቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከቤቶች ግንባታ ጋር ተያይዞ በየክልሉ የተፈጠረ የተወሰነ አቅም አለ፡፡የትምህርት ሚኒስቴር የዩኒቨርስቲ ግንባታን ለማስፈፀም የያዘው የራሱ ዕቅድ እንዳለ ይታወቃል፡፡ የትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ማዕከል የሚያደርጉ ከተሞችን በመገንባት ረገድ የኮንትራክተሮች፣ የአማካሪዎች እና የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች አቅም መገንባት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡በሌላ አነጋገር በቤቶች ግንባታ ረገድ ያለው ዝግጅትና ዕቅድ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት አንድ ወጥ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡በድምሩ የኮንስትራክሽን ስራው እጅግ በጣም ሰፊና ፈጣን የአቅም ግንባታ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ የሁሉም ባለሚናዎች መስተጋብርና የአፈጻጸም ርብርብ ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም አስፈጻሚ መ/ቤቶች በራሳቸው፣ ከቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ ተቋማት፣ ከከፍተኛ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያስፈጽሟቸውን የአቅም ግንባታ ሥራዎች በዝርዝር ታቅዶ አንዳንዶቹም ወደ ትግበራ ተሸጋግረዋል፡፡ ይህንኑ አጠናክረን ካለቀጠልን ከፍተኛ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተት፣ የጥራት መጓደል እና የወጪ መናር ችግር ሊያጋጥመን ስለሚችል ይህ እንዳይሆን በዕቅዶቹ አፈጻጸም የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

## 2.2. የስራ ፈጠራና የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋሞች ልማት

የአምስት ዓመታት ዕቅዳችን ማጠንጠኛው ለዜጎች በተለይም ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ዕቅዶቻችን በአጠቃላይ ሲፈፀሙ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ከማመንና የስራ ዕድል የመፍጠሪያ አቅጣጫዎች (በገጠርም በከተማም) ከማመላከት በተጨማሪ በተጨባጭ ምን ያህል የሥራ ዕድል በየትኛው መስክ እንደሚፈጠር በዝርዝር ለይተን አስቀመጥናል፡፡ዋናው የስራ ዕድል ፈጣሪ ግብርና፣ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞችና በተወሰነ ደረጃም ባለሀብቱ በመሆናቸው ይህን ያህል የስራ ዕድል በዚህ መስክ ይፈጠራል ብለን ስናቅድ የተወሰነ አስቸጋሪነት እንዳለው አልተዘነጋም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ከሞላ ጎደል ቆጥሮ ማስቀመጥ ስለተቻለ ዕቅዱን ማዘጋጀት ችለናል፡፡በዚህ ረገድ ትኩረት የሰጠነው ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ ብለን በገመትናቸው የስኳር፣ የማዳበሪያ፣ የዩኒቨርስቲዎች፣ የአ.አ ቤቶች፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡የኮብል ስቶን ስራን ጨምሮ የመንግሥት የኮንስትራክሽን ሥራ ብቻውን እስከ አንድ ሚሊዮን የሥራ ዕድል ሊፈጥር እንደሚችል በዝርዝር ዕቅዱ ላይ ታይቷል፡፡

የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ በራሱ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞችን የማስፋፋት ዓላማችን በሁለት መንገድ ተፅዕኖ ያሳርፍበታል፡፡በመጀመሪያ ደረጃ የኮንስትራክሽን ስራው ቢያንስ በከፊል በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች አማካኝነት መፈጸሙ ስለማይቀር ለነባር ተቋሞች የሥራ ዕድል በመፍጠርና አዳዲሶች እንዲቋቋሙ በር በመክፈት አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች በማስፋፋትና በማጠናከር ረገድ የበኩሉን ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ዘርፉ የሚፈጥረውን ሰፊ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጠራን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች መስፋፋት በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋፅኦን ያበረክታል፡፡በመጀመሪያ ደረጃ ሥራና መነሻ ካፒታል የሌለው ወጣት (ከዩኒቨርስቲ የተመረቀም ቢሆን) በተጠቀሰው ዘርፍ የሥራ ዕድል በመፍጠር የሥራ ባህሉን ለማዳበር፣ ማንኛውም ሥራ ያለመጠየፍ አመለካከቱን ለማዳበርና ቢያንስ በኮንስትራሽንና ተዛማጅ መስኮች ያለውን ክህሎት ለማዳበር ያስችለናል፡፡ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች መስፋፋትና መጠናከር አጅግ መሰረታዊ ተፈላጊነት ያለውን የአስተሳሰብ ለውጥ ለመፍጠር ልማታዊ ባህልን ለማጎልበት ተወዳዳሪ የማይገኝለት አስተዋፅኦን ያበረክታል፡፡ከዚህ ጎን ለጎን በዘርፉ የተሰማራው እያንዳንዱ ስራ ፈላጊ ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ የተወሰነውን በግድ እንዲቆጥብ ከተደረገ የቁጠባ ባህልን ለማዳበር፣ በወጣቱ የጠባቂነትን መንፈስ ለመስበር፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሞች ማስፋፊያ የሚሆን ገንዘብ በከፊል ለመሸፈንና በዚህ ረገድ ያለውን የብድር ስርዓት ጤነኛ አቅጣጫ ይዞ እንዲያድግ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ ባሻገር በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማት ላይ ሊጫወት የሚችለውን አዎንታዊ ሚና ማጎልበት የሚቻለው ከላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች ለመተግበር የሚያስችል ዝርዝር ዕቅድ ይዘን ማስፈጸም ስንችል ነው፡፡ይህ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አቅጣጫዎች ለዘርፉ ካስቀመጥነው አጠቃላይ ስትራቴጂ ጋር ካልተያያዘ ጠቀሜታውን አሟጦ ለመጠቀም የሚቻል አይሆንም፡፡የአምስት ዓመት ዕቅዱን በምናስቀምጥበት ወቅት በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማት መስክ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ዋና ዋና አቅጣጫዎችን አመላክተናል፡፡ በአምስት ዓመት ዕቅድ ማዕቀፉ የተቀመጠውን አቅጣጫ እና የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ በማከልና የቀድሞ ተሞክሮዎቻችን ቀምረን የቆየውን ስትራተጂያችንና መርሀ-ግብራችንን በማሻሻል ወጥና ሁሉን አቀፍ መፍትሔ አስቀምጠናል፡፡

## 2.3. የማክሮ ኢኮኖሚ እንድምታ

ባለፉት ዓመታት ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከተያዙት የኮንስትራክሽን ዕቅዶች በእጅጉ ያነሱ ስራዎችን ስንሰራ በነበርንበት ወቅት ከታዩ ክስተቶች በመነሳት የጉዳዩ አንድምታዎችን በይበልጥ መረዳት ይቻላል፡፡ የስራው ማክሮ ኢኮኖሚያዊ እንድምታን በመጀመሪያ እንመልከት፡፡ከዚህ በፊት ስራዎችን ስንሰራ ከሲሚንቶ ጀምሮ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ከፍተኛ እጥረትና ዋጋ መናር አጋጥሞናል፡፡በርካታ የተጀመሩና በመጠናቀቅ ላይ ያሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ስላሉን የሲሚንቶ እጥረት ያጋጥመናል ተብሎ አይገመትም፡፡የሲሚንቶ ዋጋ ይወድቃል፣ ፋብሪካዎች በሙሉ ማምረት ሲጀምሩ የገበያ ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል ብለን ስንሰጋ የነበረው ግን መሰረተ ቢስ ስጋት የሚሆን ይመስላል፡፡ ይሁንና ዋጋውን በመጠኑ ለመቀነስና በሂደት የሲሚንቶ እጥረት እንዳያጋጥም ብዙ ርቀት ያልሄዱትን የሲሚንቶ ፕሮጀክቶችን ለማፋጠንና ለመግፋት ጥረት ማድረግ ግን ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኮንስትራክሽን ብረታ ብረት ፍላጎትና ዋጋ በከፍተኛ መጠን እንደሚጨምር፣ የቤቶች የማጠናቀቂያ ዕቃዎችና የፈርኒቸር ፍላጎትና ዋጋም እንደሚጨምር ግን መገመት ይቻላል፡፡ይህ በአንድ በኩል ከውጭ የምናስገባው ኮንስትራክሽን ነክ ዕቃን በመጨመር በውጭ ምንዛሪ ገበያው ላይ ከፍተኛ ጫና ከማሳደር አልፎ የኮንስትራክሽን ወጪን በአጠቃላይ በመጨመር የፕሮጀክት ወጪንና የዋጋ ግሽበት ግፊትን ሊጨምርብን ይችላል፡፡

ይህ ክስተት በአምስት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ከላይ የተጠቀሰውን ስጋት የመደቀኑ ያህል በዚያው ልክ ለኢምፖርት ሰብስቲትዩሽን ስራችን መጠናከር ልዩ እድል ሊሰጠን ይችላል፡፡ በውጭ ከምናስመጣቸው የኮንስትራክሽን ምርቶች ውስጥ ዋናው ብረታ ብረት ስለሆነ እስከተቻለ ድረስ ከ2003 ጀምረን ተኪ ፋብሪካዎችን በማቋቋም ችግሩን መፍታት እንችላለን፣ ይገባናልም፡፡በፊትም እንዳሰብነው ጥሬ ዕቃውን ከማዕድን ዘርፍ በመውሰድ የሚሰራ ስራ በጣም ብዙ ወጪና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ በአምስት ዓመቱ ዕቅድ ሂደት መካሄድ ያለበትም ቢሆን በተፈለገው ፍጥነት የሚደርስልን አይሆንም፡፡ለፈጣን መፍትሔ የሚኖረን አማራጭ ያለንን በብዙ መቶ ቶኖች የሚቆጠር ስክራፕ በአፋጣኝ አሰባስበንና እንዳይባክንና ወደ ውጭ እንዳይወጣ ከልክለን ይህንኑ በማቅለጥ የብረታ ብረት ፍላጐታችንን የሚሸፍኑ ፋብሪካዎችን በሜታልና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን አማካኝነት በፍጥነት መገንባት ነው፡፡ ሌሎቹ ምርቶችም በተመሳሳይ መልኩ አንድም በኢንዱስትሪ ዞኖች እየገቡ ባሉ ትላልቅ የውጭ ባለሀብቶች አሊያም በአገር ውስጥ

ባለሀብቶች ሊከናወኑ የሚችሉበት የተጠናከረ ሥራ መስራት ያስፈልገናል፡፡በዘርፉ መመሪት ስላለባቸው ምርቶች የተሟሉ የፊዚቢሊቲ ጥናቶችን ማስጠናትና ይህንኑ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ማቅረብ አንዱ አማራጭ ሲሆን፣ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ዞኖች ከሚያስተዳድሩ ኩባንያዎች ጋር በመነጋገር በተመረጡት ዘርፎች ፈጥነው ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉ ትላልቅ የውጭ ባለሀብቶች መመልመል ሌላው አማራጭ ነው፡፡ ሁለቱንም አጣምሮ መጠቀምም ይበልጥ ተመራጭ ይሆናል፡፡

በዘርፉ የሚካሄደውን የኢምፖርት ስብስቲትዮሽን ስራ በማፋጠን በውጭ ምንዛሬ ገበያውና በኮንስትራክሽን ወጪ ላይ የተደቀነውን አደጋ በመቀነስና ወደ ልማት ዕድል መቀየር የሚቻል ቢሆንም በአገር ውስጥ ፋይናንስ ላይ የሚኖረው ተፅእኖን ለማቃለል በዝርዝር ታቅዶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ የኮንስትራክሽን ወጪውን ለመቀነስ የተለያዩ ጥረቶች ማድረግ እንደሚኖርብን ተገንዝበን የጀመርነውን የክትትል ሥራ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልገናል፡፡ምናልባትም የኢንዱስትሪ ከተሞችን ስንገነባ በሌላ አማራጭ ማስኬድ ከተቻለ ወይም የሚካሄደው ግንባታ መጠንና ወጪ ለመቀነስ የሚያስችል አማራጭ ካለ በጥብቅ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ይህ እስከሆነ ድረስ የኮንስትራክሽን ስራ የፕሮጀክቶቻችን አንድ ቁልፍ አካል በመሆን የመንግስት ኢንቬስትመንት ወጪን ማናሩ ስለማይቀር ግንባታዎች ወጪዎችን በዝርዝር እየተፈተሹ መመራት ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡

ለኮንስትራክሽን የምናወጣው ገንዘብ ወደ ስራተኛው ገብቶ ለፍጆታ በመዋል የዋጋ ግሽበት ጫና ከሚፈጥር ይልቅ ቢያንስ የተወሰነው ክፍል እንዲቆጠብ ለማድረግ መስራት የሚቻልና የሚገባ ይመስላል፡፡ አብዛኛው የጉልበት ሰራተኛ ወይም የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ተዋናይ አዲስ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም የመፍጠር ወይም የማስፋፋት ስራ ሲሰራ ብዙም መነሻ ካፒታል ስለማይኖረው ብድር ስጡኝ ማለቱ አልቀረም፡፡ይህ የቁጠባ ባህልን ከመጉዳቱም ባሻገር ያለዋስትና የሚሰጥ ብድር እንዲስፋፋና ያለመመለስ አደጋ እንዲስፋፋ እያደረገ ነው፡፡በምትኩ በነዚህ ስራዎች የሚሰማራ ሰው ሁሉ ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ የተወሰነውን እንዲቆጥብ የሚያስገድድ ኮንትራት ከመጀመሪያው ፈርሞ እንዲገባ ብናደርግና በዚህ መልኩ የሚቆጥበው ገንዘብ፤ ተቋም ለመፍጠር ወይም ለማስፋፋት ሲፈልግ ተጨማሪ ብድር እንደሚያስገኝለት ተደርጎ ቢቀረጽ ቁጠባን ለማዳበርና የዋጋ ግሽበት ጫናን ለመቀነስ እንደሚረዳ ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ኮንትራክተሮችን በዚህ መልኩ ቆጥቡ በማለት ብዙ የማያሠራን ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና የማሽነሪ ፍላጎታቸውን ለማርካት በሊዝ ወይም ብድር የምንሰጣቸው ከሆነ ከገቢው እየተቆረጠ ለክፍያ እንዲውል ቢደረግ ቢያንስ የዋጋ ግሽበት ጫና (ሰከንደሪ ኢፌክቱን) መቀነስ ይቻላል፡፡ በፋይናንስ ረገድ ያለውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስ ከላይ የተቀመጡት የፖሊሲ አቅጣጫዎች በጥብቅ ዲሲፕሊን መፈጸም ይጠይቀናል፡፡

## 3. ትኩረት ሰጥተን ልንረባረብባቸው የሚገቡ የትኩረት ነጥቦች

የአምስት ዓመታት ዕቅዳችን የሚያስከትለውን የኮንስትራክሽን ፍላጎት አንድ ላይ በማጣመር በምንመለከትበት ወቅት ምን ያህል ግዙፍና በዕቅዱ ስኬታማነት ላይ ወሳኝ ድርሻ ያለው ሥራ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚያም በላይ ይህ ግዙፍ ስራ ምን ዓይነት ተፅዕኖዎች ሊያስከትል እንደሚችልና ምን ዓይነት የስኬት ዕድሎችን ሊፈጥር እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም እነዚህን ተፅዕኖዎች ለመቀነስና በመልካም ዕድሎቹ በይበልጥ ለመጠቀም የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይኖርብናል፡፡

### 3.1. የአቅም ግንባታ ስራን ወጥ በሆነ መንገድ አቅዶ መፈጸም

ከላይ እንደተጠቀሰው በኮንስትራክሽን ዘርፍ እንደሚሰማሩ ለሚጠበቁት ተዋንያን የሚሆን ሰፊና ውስብስብ የአቅም ግንባታ ስራ የሚያስፈልግ በመሆኑ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የአጫጭር ስልጠና ማዕከላት ተቀናጅተው መንቀሳቀስ ጀምረዋል፤ ይህንኑ ሥራ በማጠናከርና በማፋጠን ማስፈጸሙን መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡በተለይ በሥራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች የሙያ ደረጃ (occupational standards) ሰርተፊኬሽን በመንግስት ፕሮጀክቶች ዙሪያ በማጠንጠን በፍጥነት የሙያ ብቃትን እያረጋገጡ መፈጸም ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ተደርጐ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

### 3.2. የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማትና የሥራ ዕድል ፈጠራ

ዘርፉና የመንግሥት ዕቅዱ የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል ለመተንበይ፣ ሥራውና ሰራተኛው ስለሚገናኙበት መንገድ አቅጣጫዎችን ዘርዝር አድርጎ ለማስቀመጥ በተለይም ስራው በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማት መስክ የሚኖረውን በጎ ተፅዕኖ አሟጦ ለመጠቀም እንዲያስችለን ተሻሽሎ በፀደቀው የስትራቴጅና መርሀ-ግብር መሠረት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡በዚሁ መሠረት ለዚሁ ዓላማ ተብሎ ዳግም የተደራጀው የፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ኤጀንሲ ተልዕኮውን ወስዶ ሥራውን በንቅናቄ መልክ ለማስፈጸም መረባረብ ይጠበቅብታል፡፡

### 3.3. ኢምፖርት ሰብስቲትዩሽንን ማጠናከር

ሀ/ በዚህ ረገድ የሜታል እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽንን ማዕከል በማድረግ በአገሪቱ ያለው ስክራፕ ብረታ ብረት በመጠንና ዓይነት ተለይቶ የሚታወቅበት በአግባቡ ሚሰባሰብበትና ጥቅም ላይ የሚውልበት ስርዓት መቀየስና በአፋጣኝ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ኮርፖሬሽኑ በአንድ ዓመት ውስጥ ይህንኑ በመጠቀም ለኮንስትራክሽን ከውጭ የምናስገባውን የአርማታ ብረት በከፍተኛ መጠን መቀነስ ከተቻለም ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት የሚያስችል ዕቅድ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ በመሆኑ ይህንኑ አጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

ለ/ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ግንባታ እንዳይስተጓጎልና ፈጥኖ እንዲጠናቀቅ ከማድረግ ባሻገር ሌሎች ኮንስትራክሽን ነክ የሆኑ ምርቶችን ፈጥኖ በአገር ውስጥ ለማምረት የተቀመጡትን አቅጣጫዎች በማዳበር ወደ ተግባር ማሸጋገርም አስፈላጊ ይሆናል፡፡እነዚህ ሥራዎች የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኃላፊነቱን ወስዶ አፈጻጸሙን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

# I. ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና አቅም ግንባታ መነሻ ሁኔታ

## 1. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አፈፃፀም

### 1.1 የተከናወኑ ልማቶችና የተፈጠረ የሥራ ዕድል

በሀገራችን ዋና ዋና ከተሞች ካለው ሰባ በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ደረጃቸውን ባልጠበቁ፣ በተጨናነቁና በአጠቃላይ ለመኖሪያ በማይመቹ አካባቢዎች የሚኖርና አንዳንድ ጥናቶች እንደጠቆሙትም የቤት አቅርቦት እጥረት 1 ሚሊዮን እንደነበረ ይገመታል፡፡ ይህንን ገጽታ ለመቀየር መንግስት ከ1998 እስከ 2002 ድረስ 396 ሺህ የጋራ መጠቀሚያ ቤቶችን ለመገንባት፣ 10 ሺህ የሚሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲፈጠሩና ለ200 ሺህ የከተማ ነዋሪዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ተገብቷል፡፡ በፕሮግራሙ አፈጻጸም ከተመዘገቡት ዋና ዋና ውጤቶች መካከል ከዚህ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

1) በፕሮግራሙ በአዲስ አበባና በክልሎች ልዩ ልዩ ከተሞች እስከ አሁን ድረስ ወደ 170 ሺህ የሚጠጉ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው በአብዛኛው ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ በመደረጋቸዉ ቤት አልባ የነበሩ ዜጎቻችን የቤት ባለቤት መሆን መቻላቸው፣

2) የቤት ልማት ፕሮግራሙ ለከተማ ነዋሪዎች የቁጠባ ባህል በማዳበር የቤት ባለቤት እንዲሆኑና የተሻለ አኗኗር እና የከተሞችን ገጽታ በመቀየር በኩል የበኩሉን አስተዋፅዖ ሊያደርግ መቻሉ፣

3) በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማስፈጸም አቅም ግንባታ ሂደት የሚታየውን የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር በማሳደግ ለተጨማሪ አቅም ግንባታ መሰረት መሆኑ፣

4) በኘሮግራሙ መሠረት ከ1999 እስከ 2002 ዓ.ም. ባሉት አራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለከተማ ነዋሪዎች በተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ለ176 ሺህ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር መቻሉ፣

5) በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚታየውን ዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የቁርጥ ነጠላ ዋጋ አሰራር በመጠቀም የግንባታ ዋጋ መቆጣጠር መቻሉና ለመጀመሪያ ጊዜ በእሴት ሰንሰለቱ ላይ የሚታዩትን ተደጋጋሚ ወጪዎች በማስቀረት የአነስተኛ ሥራ ተቋራጮችን ተሳትፎ በማጎልበት ወጪ መቆጠብ መቻሉ፣

6) በአገር አቀፍ ደረጃ በግንባታና በምርት ስራዎች መሳተፍ የሚችሉ 4306 አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በአስፈላጊው የሙያዊ ክህሎት፣ የመነሻ ካፒታል እና የግንባታና የማምረቻ መሳሪያዎች አቅማቸው እንዲገነባ በማድረግ በቤት ልማት ፕሮግራሙ እንዲሳተፉ መደራጀታቸው፣

## 1.2 የዲዛይንና የግንባታ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

የቤት ልማት ግንባታው በአነስተኛ ዋጋ ለመገንባት ይቻል ዘንድ ወጪ ቆጣቢ ዲዛይኖችንና የአገነባብ ቴክኖሎጂዎችን እንዲከተል ጥረት በመደረጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ስራዎችና ልምዶች ስራ ላይ ውለዋል።

1) በዲዛይንና ግንባታ ሂደቱ በስታንዳርድ የተዘጋጀ የፕሪካስት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከነበሩ የህንፃ መዋቅር አሰራር የአርማታ ግብዓቶችን መጠን ከ 5 እስከ 10 በመቶ መቀነስ መቻሉ፣
2) የሕንፃውን የግድግዳ አካል በወጪ ቆጣቢ የአግሮስቶን ምርት በመጠቀም የመከፋፈልና የመሸፈን ሥራዎች ለመስራት የአግሮ ስቶን ፓኔል ማምረቻ ማዕከላቶች በሰባት ቦታዎች መቋቋማቸውና የግድግዳ ወጪ መቀነስ መቻሉ፣
3) የፕሮጀክት ማኔጅመንት ብቃት በየደረጃው ባሉ ፈፃሚ አካላት መገንባት መቻሉ፣

## 1.3 የተቋራጭና አማካሪ አቅም ግንባታ

በመንግስት ድጋፍ የተካሄደው የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም በዕቅድ ዘመኑ ብር 16 ቢሊዮን በላይ ፈጅቷል። በመሆኑ ለዚህ ፕሮግራም የሚያስፈለገው የግንባታ፣ የማማከርና የቁጥጥር አገልግሎት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ የሚከተሉት አቅሞች ተፈጥረዋል፣

1) በቤቶች ልማት እየተሳተፉ የነበሩ ነባር ሥራ ተቋራጮች ብዛት 1 ሺህ አካባቢ ብቻ ሲሆን እነዚህም ቢሆኑ የግንባታ መሳሪያና የካፒታል እጥረት ሲያጋጥማቸው የነበረ በመሆኑ መልካም አፈፃፀም ላሳዩ ሥራ ተቋራጮች በተመጣጣኝ ዋጋ በባንክ ብድር ትስስር ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የካፒታል አቅማቸው በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ በማስቻሉ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መጎልበት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ማበርከቱ፣
2) በቤቶች ልማትና በተለያዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ይታይ የነበረውን የሥራ ተቋራጮች እጥረት ለመቅረፍ 752 ባለሙያዎችን መርጦ ለስራ ተቋራጭነት ለማብቃት የአቅም ግንባታ ፕሮግራም በመዘርጋት የሥራ ተቋራጭነት ስልጠና በመስጠት፣ የፋይናንስና የግንባታ መሳሪያዎች ድጋፍ በማመቻቸት እና በልዩ ልዩ የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች የስራ ትስስር እንዲፈጠርላቸው በማድረግ ቁጥራቸው ወደ 2 ሺህ ከፍ እንዲል መደረጉ፣
3) ከዚህ በፊት በቤቶች ልማት ሲሳተፉ የነበሩ አማካሪዎች ቁጥር ከ10 የማይበልጥ የነበረ በመሆኑ የነበረውን የወጪ ቆጣቢ ዲዛይን ዝግጅትና የጥራት ቁጥጥር ክፍተት ለመሙላት ባለሙያዎችን መርጦ ለአማካሪነት ለማብቃት በተዘረጋው የአቅም ግንባታ ፕሮግራም የተለያየ ሙያ ያላቸው 147 መሃንዲሶችና ቴክኒሺያኖች ያቀፉ 43 የሚደርሱ የአማካሪ አሃዶች /Consulting Firms/ አስፈላጊው ለአማካሪነት የሚያበቃ ስልጠና በመስጠት እንዲሁም በቤቶች ልማትና በተለያዩ የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች በመሳተፍ የስራ ትስስር መደረጉ፣

4) በአማካሪዎች ዘንድ ከቤቶች ልማት ፕሮግራም ትግበራ ሂደት በዲዛይንና በጥራት ቁጥጥር የተገኘው አቅም ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መጠናከር የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ማበርከቱ፣

## 1.4 የግንባታ ዕቃዎችና መሣሪያዎች አቅም ግንባታ

በትግበራ ሂደቱ የታየውን ከፍተኛ የሆነ የማስፈፀም አቅም ውሱንነት ለመቅረፍ ከኮንስትራክሽን አቅም ግንባታ ጋር በተያያዘ የነባርና የአዲስ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች እንዲሁም የባለሙያዎች አቅም ግንባታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ የቤቶች ልማት ኘሮግራም እና የመንግሥት ልዩ ልዩ ኘሮጀክቶችን በማሽነሪና ተሽከርካሪ የሎጀስቲክስ አቅም ግንባታ እና የቤቶችን ግንባታ ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ ከውጭ ሀገር የፋብሪካ ውጤት የሆኑ የግንባታ ግብዓቶች በተለይም ሲሚንቶ፣ አርማታ ብረት፣ ሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪካል እና የአግሮስቶን ጥሬ ዕቃዎች  በስፋት ከውጭ የማስገባት ሥራ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡

የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከነበሩበት ውሱንነቶች አንዱ የግንባታ ዕቃዎች አቅርቦት እንደመሆኑ መጠን ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ በተደረገው የግንባታ ዕቃዎችና ሎጂስቲክስ አቅም የማሳደግ ጥረት:-

### 1.4.1. የፋብሪካ ግብዓቶች አቅርቦት

1) 1.2 ሚሊዮን ቶን ስሚንቶ እንዲሁም 150 ሺህ ቶን አርማታ ብረት ከዉጪ ሀገር እንዲገባ በማድረግ እንዲሁም ከሃገር ዉስጥ ፋብሪካዎች በማቀናጀት አቅርቦቱ  የተቀላጠፈና በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ጥረት መደረጉ፣
2) ለማጠናቀቂያ ስራ የሚያስፈልጉ የሳኒተሪና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች አቅርቦት ለማሟላት ከውጭ ሀገር በስፋት ግዢ እንዲገባ ከተደረገዉ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ የመንግስትና የግል ፋብሪካዎች እንዲስፋፉ አስፈላጊው ድጋፍና ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፣
3) ፕሪፋብሪኬትድ ማቴሪያሎች የሆኑ እንደ ብሎኬት፣ፕሪካስት ቢም እና በሮችና መስኮቶች በመላ ሀገሪቱ በሺዎች የሚቆጠሩ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊው የክህሎት ስልጠና፣ የፋይናንስና የማምረቻ መሳሪያዎች የማሟላት ድጋፍ በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ተመቻችቶላቸው ለቤቶች ልማትና ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አምርተው ማቅረብ በመቻላቸው ከፍተኛ የሆነ ፕሪፋብሪኬትድ ማቴሪያሎችን የማምረት አቅም የተፈጠረ ሲሆን ይህም ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መጠናከር የራሱ የሆነ ድርሻ ማበርከቱ፣
4) የአግሮስቶን ፓኔል ምርት የሲሚንቶ ምርት በመጠቀም ከሚወጣው ወጪ በግማሽ ወጪ ቆጣቢ የሆነ ሆኖ በአሁኑ ወቅት በመዲናችን በአዲስ አበባ በሁለት ሰፋፊ የማምረቻ ማዕከላት፣በተገጣጣሚ ህንፃ አ/ማ/ድ፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በሀዋሳ፣ በአማራ ክልል በባህርዳርና በደሴ፣ በኦሮሚያ ክልል በአዳማ እንዲሁም በተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የአግሮስቶን ማምረቻ ማዕከላቱ ተስፋፍተው የሚገኙ በመሆኑ የዚህ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ለቤት ግንባታ ወጪ ቆጣቢ ሆኖ እጥረትን ለማቃለል ከማገዝ ባለፈ በልማቱ

አማካይነት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የአቅርቦት አቅም በማሳደግ ጥረት አኳያ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ማድረጉ፣

### 1.4.2. የአካባቢ የግንባታ ዕቃዎች አቅርቦት

የአካባቢ የግንባታ ማቴሪያሎችን ማለትም ጠጠርና አሸዋ የመሳሰሉትን በተመለከተ ምንም እንኳን እንደ ጥሬ ዕቃ ከበቂ በላይ ሊባል በሚችል መጠን በስፋት በሀገራችን የሚገኙ ቢሆንም የእነዚህ አቅርቦትና ሎጂስቲክስ አቅም ማነስ ሌላው ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚታይበት ገፅታ እንደመሆኑ በቤቶች ልማት አፈፃፀም የተገኙ ውጤቶች :-

1) ከዚህ ቀደም በሌላው የሚመረተውንና የሚቀርበውን መጠን ለማሳደግ በመቶዎች የሚቆጠሩ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በተለይም ለጠጠር ምርት አስፈላጊው የአደረጃጀትና የቢዝነስ ዴቬሎፕመንት፣ የክህሎት ስልጠና፣ የፋይናንስና የማምረቻ መሳሪያዎች የማሟላት ድጋፍ ተመቻችቶላቸው ለቤቶች ልማትና ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አምርተው ማቅረብ እንዲችሉ መደረጉ፣

2) በከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ስራ ማነቆ ሆኖ የቆየውን የጠጠር አቅርቦት አቅም ውሱንነት ሊያሳድግ የሚችል በሠዓት 100 ቶን ጠጠር የማምረት አቅም ያላቸው ክሬሸሮች በአብዛኛው ተተክለው የጠጠር አቅርቦቱ በከፍተኛ መጠን እንዲያድግ ማስቻሉ፣

### 1.4.3. የግንባታ መሣሪያዎች አቅርቦት

የቤት ልማቱን ማዕከል በማድረግ መንግስት የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ በብድርና ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ሁኔታዎችን በማመቻቸት፡-

1) ሥራ ተቋራጮችና የግንባታ ዕቃ አቅራቢዎች የተላለፉ 1000 ገልባጭ ተሽከርካሪዎችና 350 ሎደሮች፣
2) ለጠጠር አቅራቢ ኢንተርኘራይዞች 65 ክሬሸሮች፣
3) ከወደብ ወደ ተርሚናሎችና ከዚያም ወደ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይቶች የግንባታ ዕቃዎችን የሚያመላልሱ አዲስ 1100 የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪዎች፤

ከውጪ እንዲገቡ በማድረግና በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ በአሁኑ ወቅት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሎጂስቲክስ አቅም የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

## 1.5 ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ

1) የቤቶች ልማት ኘሮግራም ከፌዴራል ጀምሮ በተዋረድ በክልልና በከተማ ደረጃ የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት እንዲቋቋሙ እንዲሁም የቤቶች ግንባታ ያለበትን ደረጃ ለመገምገም በየሩብ ዓመት በመስክ

በሚገኙ ውጤቶች የጋራ የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ለሚያጋጥሙ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሔ ለመስጠት የተደረጉ ጥረቶች የሚበረታቱ መሆናቸዉ፣

2) ኘሮግራሙ ሲጀመር የቤት ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤቶች በክልሎችና በከተሞች እንዲሁም በማዕከል ደረጃ በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ሥር ሆኖ የሚያስተባብር ቢሮ እንዲኖር መደረጉ፣

### 1.6 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

1) የቤት ልማት ፕሮግራም ጥናት የቤት ችግሩን ሊቀርፍለት የተነሳውን የህብረተሰብ ክፍል ከመግዛት አቅም ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ በተለይ በየክልሉ የተገነቡትን ቤቶች በማስተላላፍ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው አለመቻሉ፣
2) በግንባታ ግብአት ዕጥረትና ዋጋዎች መናር በአብዛኛው የቤት ልማት ፕሮግራሙ ግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ በመራዘሙ ቤቶቹን በወቅቱ ማስተላለፍ እና ፕሮግራሙን በታሰበው ሁኔታ ማካሄድ አለመቻሉ፣
3) በክልሎች ፋይናንስ ላይ ጫና ከመፍጠሩም ባሻገር የፋይናንስ አቅርቦቱን በወቅቱ ሥራ ላይ አውሎ መመለስ ባለመቻሉ የገንዘብ ፍሰት ዕቅዱን ማዛባቱ፣
4) አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት በበቂ ፍጥነትና መጠን ማዘጋጀት ባለመቻሉ በአፈፃፀም ላይ የታዩ መጓተት እና የጥራት ጉድለቶች በሥራ ተቋራጮች ላይ ጫና መፍጠራቸው፣

## 2. የመንገድ ልማትና ማስፋፋት አፈፃፀም

### 2.1 የተከናወኑ ልማቶች

መንግስት ለመንገድ መሰረተ ልማት ከሰጠው ልዩ ትኩረት የተነሳ የትራንስፖርትና የመገናኛ አውታር መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት በተወሰደው መሠረተ-ሠፊ እርምጃ ከሀገሪቱ ዓመታዊ ገቢ ትልቁን ድርሻ የሚሆነው ለዚሁ ተግባር እንደዋለ ይገመታል። ባለፉት አመታት ከፍተኛ የመንገድ ግንባታዎች ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን የመንገድ ሽፋኑ ከነበረበት ከ34 በመቶ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ 46 በመቶ ሊደርስ ችሏል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት 5000 ኪ.ሜ የአስፋልት ፣24000 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ እንዲሁም 32000 ሺህ የገጠር መንገዶች በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከተመዘገቡት ዋና ዋና ውጤቶች መካከል፡-

1) በፌደራልና በክልል ደረጃ ባለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት /1990-2002ዓ.ም./ ከ641 በላይ በሆኑ ፕሮጀክቶች ያካተተ የ18,350 ከ.ሜ. የዲዛይን፣ የማማከር፣ የአዲስ መንገድ ግንባታና የነባር መንገዶች የጥገና ሥራ በብር 55.01 ቢሊዮን ተከናውኗል:: ከዚህ ውስጥ ብር 52.78 ቢሊዮን ያህሉ ለግንባታ የወጣ ሲሆን ብር 2.23 ቢሊዮን ያህሉ ለማማከር አገልግሎት የዋለ ነው።
2) ከ1998 እስከ 2002 የነበረውን አፈፃፀም በተመለከተ የወረዳ መንገዶችን ሳይጨምር 36400 ኪ.ሜ. የፌደራልና የክልል መንገዶች ተገንብተው የሀገሪቱ የመንገድ ሽፋን 48800 ኪ.ሜ. አድርሶታል። ይህ ዕድገት የመንገድ ጥግግትን ከነበረበት 33.6 ኪ.ሜ. በ1000 ካሬ ኪ.ሜ. በ33 በመቶ በማሳደግ ወደ 48.8 ኪ.ሜ. ሲያደርስ፣ በዕቅዱ መነሻ የነበረውን 64 በመቶ በጥሩና በደህና ሁኔታ የሚገኘን የመንገድ መጠን ወደ 81 በመቶ እንዲሻሻል አድርጓል።

## 2.2 የዲዛይንና የግንባታ ባለሙያዎችን ማብቃትና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም

1) ያለውን ሰው ኃይል ክህሎቱን እንዲያዳብር እና ከጊዜው አሠራርና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲሄድ ባለፉት 12 ዓመታት ከ85 በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉ፣

2) ሁሉም የፌደራል መንገድ ፕሮጀክቶች ከመሠራታቸው በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት እንዳስፈላጊነቱ በማድረግ ህዝቡን በተሻለ ሁኔታ ለማስፈር የሚያስችል ጥናት በማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎች የአፈርን መሸርሸር ለመከላከል እና የውሃ ብክለትን ለመቀነስ መሠራታቸው፣

3) በክልሎች የሰው ጉልበትን መሠረት ያደረገ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በራሳቸው ኃይል በርካታ መንገዶችን የሚሠሩ ሲሆን ከሃያ የማያንሱ አነስተኛና መካከለኛ ተቋራጮችን በመጠቀም 400 ኪ.ሜ. ያህል የመንገድ ጥገና ሥራ ተከናውኗል። ከ3000 በላይ ቴክኒሻያኖችን በጉልበት ተኮር የግንባታ ዘዴ እንዲሰለጥኑ መደረጉ፣

## 2.3 የተቋራጭና አማካሪ አቅም ግንባታ

1) ባለፉት 13 ዓመት የማማከር አገልግሎቶች 58.5% አካባቢ በውጭና 41.5% በአገር ውስጥ ድርጅቶች ተሳትፎ የተሰራ ነው። ከግንባታ ሥራዎች ውስጥ ግን 61.45 በመቶ ድርሻ ያለውን የውጭ አገር የሥራ ተቋራጮች ያከናወኑት ሲሆን የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ድርሻ 32.70 በመቶ ነበር:: ባለፉት 13 ዓመታት ለጨረታ ከቀረበ ብር 59.2 ቢሊዮን ውስጥ ብር 21.3 ቢሊዮን የሚያወጡ ፕሮጀክቶች ለሀገር ውስጥ ተቋራጮች ተሰጥቷል።

2) መንግስት የሀገር ተቋራጮችን ለማበረታታት የተለያዩ መመዘኛዎችን በማላላት፣ ሥልጠናዎችን በመስጠቱ እና በበርካታ ሥራዎች እንዲሳተፉ በማድረጉ ለውጦች ታይተዋል። አገራዊ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የሚሳተፉባቸው የፕሮጀክቶች ቁጥር በየጊዜው በማደጉና አቅማቸውም በመጎልበቱ በጣም አነስተኛ ከሆነ ደረጃ ተነስቶ በአሁኑ ሰዓት ከ50 ከመቶ በላይ የሚሆነውን የፌዴራል መንገድ ሥራ በመያዝ ላይ ነው።

3) የመንገድ ግንባታ አቅምን ለማሳደግ 100 ሮለሮችና 25 ሎቤዶች ከውጭ ተገዝተው ለተለያ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ተከፋፍለዋል።

## 2.4 ያጋጠሙ ችግሮች

1) በተቋራጮች ዘንድ የታዩ የማኔጅመንት ብቃት ችግሮች፣ ጨረታ ለማሸነፍ ሲባል ዋጋ የመስበር፣ ኘሮጀክቶችን የማጓተት፣ የምርታማነት ዝቅተኛ መሆን እና የጥራት ችግር መኖር፣

2) በሌላ በኩል በመንገድ ዘርፍ የተሰማሩ ተቋራጮች ቁጥር ውስን መሆን ያለው ገበያ ውድድር አነስተኛና ግልፅ ያለመሆን፣

3) አማካሪ ድርጅቶች የይገባኛል ጥያቄዎችን ወደ ኢመባ መግፋት እና ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ አለማድረግ፣ የውሳኔ አሰጣጥ ዘገምተኛ መሆን፣ የዲዛይን ኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት ድጋፍ አነስተኛ መሆን እና በዝቅተኛ ዋጋ ሥራ መውሰድና ኘሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ መቋረጥ፣

4) የዘርፉ የምርምር አቅም አለማደግ ወጪን ሊቀንሱ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን እና አሠራሮች እንዳይስፋፉ እና ልማዳዊ አሠራሮች እንዲቀጥሉ ማድረጉ፣

5) የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዋጋ መጨመር፣ የባንክ ብድር በሚያስፈልጋቸው መጠን አለማግኘት፣ በኢንዱስትሪው የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት አሰራር አለመዳበር፣

6) የክልልና የወረዳ መስተዳድር አካላት ድጋፍ የተፈለገውን ያህል አለመሆን፣ በካሣ ግምት እና ንብረት ማስነሳት፣ ተደጋጋሚ የመንገድ ማሻሻያ ጥያቄ፣ መንገዱ እንደሚጀመር ሲታወቅ የድንጋይ፣ የአሸዋ ቦታዎችን እያወቁ ሆን ብሎ ለሌሎች መስጠትና ባለይዞታ የካሣ ክፍያ እንዲያገኝ ማመቻቸት፣

7) የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ዕጥረት፣ በሚሠሩት ሥራ ላይ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ዕጥረት የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

# 3. የውሃ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም

## 3.1 የተከናወኑ ልማቶች፣ የተቋራጭና አማካሪ አቅም

1) በሀገሪቱ በአጠቃላይ የመጠጥ ውኃ ሽፋን በ1997 ከነበረበት 36 በመቶ በ2002 ወደ 68.5 በመቶ አድጓል፡፡

2) የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ለማሳደግ በተደረገው ጥረት እስከ 2000 መጨረሻ ድረስ 793 ጥልቅ ጉድጓዶች፣3353 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓዶች፣ 8762 የእጅ ጉድጓዶች፣8195 ምንጭ የማጎልበት ሥራዎች፣478 የውሃ ማጠራቀሚያ ኩሬ፣ 3294 ከዝናብ ውሃና 7 ከገፀ-ምድር የሚገኝ የመጠጥ ውሃ ማቆር ለገጠሩ ህዝብ ተሠርቷል፡፡

3) ከስድስት ዓመት ወዲህ በጥቅሉ 21 የመስኖ ልማት ኘሮጀክቶች የፊዚቢሊቲ፣ የዲዛይን ጥናቶችና የግንባታ ሥራዎች በብር 2.45 ቢሊዮን እየተካሄዱ ሲሆን የአሥራ ስምንት ፕሮጀክቶች የፊዚቢሊቲ ጥናት በብር 471.27 ሚሊዮን በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡የተገለፁት የፊዚቢሊቲ ጥናት ሥራዎች የተሰሩት አሥራ ሶስቱ በሀገር ውስጥ አማካሪ ድርጅቶች ሲሆን በስምንቱ ብቻ የውጭ ድርጅቶች በንዑስ አማካሪነት ተሳትፈዋል::

4) በሌላ በኩል በብር 1.98 ቢሊዮን የሶስት ኘሮጀክቶች የግንባታ ሥራ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን 66.6 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ሲይዙ ቀሪው 33.4 በመቶ የሚሆነው የተያዘው በውጭ የሥራ ተቋራጮች ነው::

5) በአጠቃላይ በመስኖ ሥራዎች ዙሪያ ከወጣው የ2.45 ቢሊዮን የገንዘብ መጠን ውስጥ ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ሃይል የተሰራው 2.08 ቢሊዮን እና ሙሉ በሙሉ በውጪ ተሳትፎ የተሰራው 278 ሚሊዮን ያህሉ ሲሆን ቀሪው 92 ሚሊዮን ያህሉ በጋራ የተሰራ ነው።

### 3.2 ያጋጠሙ ችግሮች

1) የመካከለኛ እና ሰፋፊ የመስኖና ድሬኔጅ ልማት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ ምክንያት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር የውሃ ሃብት ያላት ቢሆንም ይህን ሃብቷን ለመስኖ ልማት በማዋል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማፋጠን ረገድ ያበረከተው አስተዋፅዖ ዝቅተኛውን ድርሻ ይይዛል።
2) ለዚህም በዋነኛነት ፕሮጀክቶች ከታሰበላቸው ጊዜ ዘግይቶ የመጠናቀቅ እና ላልታሰበ ከፍተኛ ወጪ መዳረግ ያለንን ውስን ሀብት እንዳንጠቀም አድርጎናል።

## 4. የኢነርጂ የማስፋፋት ሥራዎች አፈፃፀም

### 4.1 የተከናወኑ ልማቶች

የሀገሪቱን የሃይል ማመንጫዎች አቅም ለማሳደግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በዕቅድ ዘመኑ የተከዜ፣ የግልገል ጊቤ ሁለትና የበለስ የኃይል ማመንጫዎች ግንባታ ለማጠናቀቅ ተችሏል።

ሃገራችን ካላት ዕምቅ የውሃ ሃብት ሊመረት ይችል የነበረው የኤሌክትሪክ ኃይል ከ714 ሜ.ዋ. በላይ ቢሆንም ከ1998-2002 እስከ 3270 ሜ.ዋ. ለማድረስ ታቅዶ እስከአሁን ማልማት የተቻለው 1994 ሜ.ዋ. 61 በመቶ ያህሉ ላይ ብቻ ነው፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጪያ ጣቢያዎች ግንባታ በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን፡-

1) በአሁኑ ወቅት በብር 43.22 ቢሊዮን የአዳዲስ የሃይል ማመንጪያዎችና የነባሮችን ማደስና ማሳደግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡
2) በሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ሂደት ውስጥ ቀጣዩ ተግባር ከላይ በተመለከተው መልኩ ተገንብቶ የሚመነጨውን ኃይል በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ የኃይል ማስተላለፊያ መሥመሮች በ1997 ከነበረበት 8380 ኪሎ ሜትር በ2002 ወደ 14792 ኪሎ ሜትር ለማሳደግ ታቅዶ አፈፃፀሙ ወደ 12147 ኪሎ ሜትር ማሳደግ ሲቻል በማሰራጫ መሥመሮች ግንባታም ከ25000 ኪሎ ሜትር ወደ 136320 ኪሎ ሜትር ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ በክንውኑ 126038 ኪሎ ሜትር ለማድረስ ተችሏል።

### 4.2 የተቋራጭና አማካሪ አቅም እና ልምድ

1) በብር 121 ሚሊዮን ወጪ በተገመተ አንድ ፕሮጀክት በኮርፖሬሽኑ ሲከናወኑ ከነበሩና አሁንም በመከናወን ላይ ከሚገኙ የፊዚቢሊቲ ጥናትና የዲዛይን ስራዎች ላይ አንድ የአገር ውስጥ ድርጅት

ከውጭ ኩባንያ ጋር ተቀናጅቶ ከመስራቱ በስተቀር ሁሉም ጥናቶች የሚከናወኑት በውጭ አማካሪዎች ነው::

2) የሰብ-ስቴሽንና የትራንስሚሽን ኮንስትራክሽን ሥራዎችን በተመለከተ በግንባታው ሂደት የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ተሳትፎ ከጠቅላላ የኘሮጀክቶች ዋጋ ከ10 በመቶ ያልበለጠና የማማከር፣ የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎች በኮርፖሬሽኑ የውስጥ ሃይል ለማከናወን ተችሏል፡፡

3) በአጠቃላይ እስከ አሁን በተካሄዱና በመካሄድ ላይ ባሉ በኢነርጂው ዘርፍ የተደረጉ የግንባታና የጥናት ሥራዎች ከ79.7 ቢሊዮን ብር በላይ የወጣ ሲሆን በዚህም የአገር ውስጥ ኮንትራክተሮችና አማካሪዎች ድርሻ የለም ማለት ይቻላል፡፡

### 4.3 ያጋጠሙ ችግሮች

1) በሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጪያ ጣቢያዎች ልማት ውስጥ ግንባታ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ መሆኑ፣ እጅግ ከፍተኛ የግንባታ ኢንዱስትሪንና ወጪን የሚጠይቅ ሲሆን ኢንዱስትሪው ይህን ለመቋቋም የሚያስችል ሁኔታ የተፈጠረለት ያለመሆኑ፣

2) እስካሁን በተሠሩት ፕሮጀክቶች ከቅድመ ጥናት ጀምሮ እስከ ግንባታው ማገባደጃ ድረስ ሙሉ በሙሉ በውጭ ተቋራጮች እንደተከናወነና አንድም የአገር ውስጥ ድርጅት በማማከርም ሆነ በግንባታ ሥራው ዕድል እንዲያገኝ ሁኔታዎች ያልተመቻቹለትና ይህ ነው የሚባል ድርሻ ያልነበረው መሆኑ፣

3) የሀይል ማመንጫ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሠረት መጠናቀቅ ያለመቻልና በአንዳንዶቹ የግንባታ ሥራቸው በተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችም ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ማስከተሉ በአገሪቱ ሀብት አጠቃቀም ላይ ጫና ማሳደሩ፣

## 5. የከተሞች መሠረተ ልማትና ማስፋፋት ሥራዎች አፈፃፀም

### 5.1 የተከናወኑ ልማቶች

በአጠቃለይ በ2001 በጀት ዓመት በማስፈጸሚያ ሥርዓቶች ዝግጅት' በፋይናንስና የግዥ ሥርዐት አፈጻጸም ድጋፎች የተሰጡ ከመሆኑም በላይ ለዲዛይን አማካሪ ቅጥር እና ለኮብልሰቶን መንገድ ንጣፍ ግንባታ የሚውል 278.2 ሚሊዮን ብር በጀት ታቅዶ 171.1 ሚሊዮን ብር ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በተለይ በ15 ከተሞች የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ተገንብቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በ2002 በጀት ዓመትም፡-

1) በ444,121,640 ብር 149.4 ኪ.ሜ የኮብል ሰቶን መንገድ፣ 28 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት፣ ላንደፊል፣ ድልድዮች፣ የጎርፍ መከላከያ እና 31.7 ኪ.ሜ. የመንገድ ተፋሰስ፣ የአውቶቡስ መነሃሪያ፣ የገበያ ማሻሻያዎችን እና ሁለት መናፈሻዎች እንዲሁም

2) የውሃ አቅርቦትና የንፅህና አጠባበቅ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በአጠቃላይ እስከ 2002 በጀት ዓመት በዚህ ፕሮግራም እስካሁን በጠቅላላው 997 ሚሊዮን ብር ከላይ የተጠቀሱት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

3) ከፍተኛ የሰው ጉልበት በማሳተፍና የሥራ ዕድልን በስፋት በሀገራችን በተፈጠረው የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ንዑስ ፕሮጀክትና ከላይ በተገለፁት የመሠረተ ልማት ሥራዎች 51905 ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

4) በ2001 የነበረውን እንቅስቃሴ የሚያሳዩት መረጃዎች 247 ለሚሆኑ የድንጋይ አንጣፊ ፎርማኖችና ለ1600 ድንጋይ አንጣፊዎች ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉንና በዚያው ጊዜም 860 የሚሆኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተቋቁመዋል፡፡

### 5.2 ያጋጠሙ ችግሮች

1) ወጥ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት ያለመኖር የእጅ ሙያ ችሎታ የውሃ ልክ ከፍታ አጠባበቅ የተለያየ መሆን፣

2) ዘመናዊ የድንጋይ መቁረጫ መሣሪያ መጠቀም ባለመቻሉ ከፍተኛ ጥራት ያለው የማዕዘን ቅርፅ ለማውጣት ያለመቻል በማሰካካትና በመደርደር ለክፍተትና መንጋደድ አስተዋፅዖ ማድረጉ፣

3) በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በእንደዚህ ያሉ ሙያዎች ውስጥ መሳተፍ የዝቅተኛነት አመለካከት በዘርፉ በተሠማራውም ሆነ ገና እንዲገባ በሚጠበቀው የህብረተሰብ ክፍል ልማቱን በማካሄድ ደረጃ ጫና መፍጠሩ፣

## 6. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ የጋራ የሆኑ  የነበሩና ያሉ ማነቆዎች

### 6.1 የሰዉ ኃይል አቅም

#### 6.1.1 ብቃትና መጠን

ባለሙያዎች በኮንስትራክሽን 23,414፣ በዲዛይን ደግሞ 10,616 በጥቅሉ በዘርፉ 34,030 በተለያየ ደረጃ የሙያ ምስክር ወረቀት የወሰዱ ቢሆንም ለነዚህ ውስን ለሆኑት በኢንዱስትሪው ለተመዘገቡ ባለሙያዎች ለያዙት ደረጃ የሚመጥን ብቃት እንዳላቸው የሚያረጋገጥ ምዝና የተካሄደባቸው አይደሉም።

በአገራችን ያሉት የትምህርት ተቋማት ኢንዱስትሪው የሚያስፈልገውን ያህል የሰለጠነ የሰው ኃይል በዓይነትና በመጠን በሚፈለገው ደረጃ አሰልጥኖ ለማውጣት ባለመቻላቸው በገበያ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በከፍተኛ ደረጃ መከሰት ምክንያት ሆኖ ይታያል።

በአጠቃላይ በኢንዱስትሪው የተሰማራው የሰው ኃይል በተቋማት የስልጠና ስርዓትና አካሄድ ውስጥ ያለፈው ጥቂት ሲሆን አብዛኛው ባለሙያ ደካማ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚንቀሳቀስና ለዘልማዳዊ አሰራሮች የሚያደላ ነው። በሰው ኃይል አቅርቦት ከሚታዩት ዋና ዋና ችግሮች መካከል፡-

1) በኢንዱስትሪው የተሰማሩ ባለሙያዎች ምርታማነታቸው አናሳ መሆን፣ በአንድ ቦታ ተረጋግቶ ያለመሥራት፣ ክፍያቸውም በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ በሚፈለገው መጠንም በገበያ ላይ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ፣

2) የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ልምድ በሌላቸው እና የክህሎት ክፍተት በሚታይባቸው በተወሰኑ ሙያዎች የክህሎት ሽግግር ወይም ተከታታይ ስልጠና ያለመኖር ወይም የትምህርት ሥርዓቱ ከተግባር ዝግጅት አንፃር ያለመቃኘት፣

3) አብዛኞዎቹን የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች ኦፕሬተሮችን መደበኛና በቂ ሥልጠና ያልወሰዱና የብቃት ምዘናና ሰርተፊኬሽን የተሰጣቸው አይደሉም። በዚህም ምክንያት በአያያዝ እና በአጠቃቀም ጉድለት የተነሳ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጡና ሀገሪቷን ለመለዋወጫ ዕቃዎች ግዢና ለውጭ ምንዛሪ መዳረጉ፣

4) ሁሉንም ሙያዎች በመለየት በመካከለኛና በረጅም ሥልጠናዎች ሽፋን እንዲያገኙ ያለማመቻቸት፣ በሥልጠናዎች ደረጃቸውን ያሳደጉ ባለሙያዎች የምዝገባ መስፈርትና አቻ ግመታዎች እንዲዘጋጅላቸው ያለማድረግ፤

5) በዘርፉ ያለው ውስን የሰለጠነ የሰው ኃይል ከፕሮጀክት ፕሮጀክት የሚያደርገው ፍልሰት እየጨመረ በመምጣቱ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ጊዜ አለመጠናቀቅና ወቅታዊ የሆነ የግንባታ ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረጉ፣

6) ባለሙያዎች ለሙያቸው የሚሰጡት ክብር ያነሰ ሆኖ በመምጣቱ ሥራዎችን ጀምረው ሳያጠናቅቁ፣ በአግባቡ ሳያስረክቡ፣ በድንገት ጥሎ መጥፋት፣ በሙያውም የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ያለመወጣት በሰፊው የሚታይ መሆኑ፣

7) በኢንዱስትሪው የተሰማራው የሰው ኃይል ከፍላጎት ጋር በጥራት፣ በቁጥርና በዓይነት የተጣጣመ ባለመሆኑ የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ዝቅ ያደረገና ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ፣ በጀት፣ ጥራት ደረጃና መጠን እንዳይጠናቀቁ ዋነኛ መንስኤ መሆኑ፣

### 6.1.2 በአመራርና ሥነ ምግባር

በአገራችን ሙስናና ብልሹ አሠራር ጎልቶ ከሚታይባቸው ዘርፎች አንዱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መሆኑ ይታወቃል። በኮንስትራክሽን ሥራዎቻችን እሴት ሰንሰለት ባሉት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ግዢ የሚውለው ፋይናንስ ቅብብሎሽ ሂደት በርካታ በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ አሠራራችን ግልፅና የተቀላጠፈ ባለመሆኑ ለሙስና በር የሚከፍት ሆኖ ይገኛል። በባለሙያ፣ በአማካሪ፣ በተቋራጭች፣ በውስጥና በመካከላቸው ባለው ግንኙነት በአመለካከትም ሆነ በተግባር የሚታዩ የሥነ ምግባር ጉድለቶች አሉ።

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በየደረጃው ያሉን አደረጃጀቶች አመራር ብቃት ከኢንዱስትሪው ዕድገት ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ባለማደጉ በአፈፃፀም ወቅት ለሚያጋጥሙ ክፍተቶች ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የማይታይ ሲሆን ከዚሁ አንፃር ጎልተው የሚታዩ ችግሮች፡-

1) በዲዛይን፣ በጨረታ መስፈርቶችና በውለታ ሰነዶች ዝግጅት ወቅት ሆነ ተብሎ በሚመቻቹ ኢ-ሥነ ምግባራዊ ድርጊቶች ለተጨማሪ ያለአግባብ ወጪዎችና ጥቅሞች ባለቤት እንዲጋለጥ ማድረግ፣

2) በዕሴት ሰንሰለቱ ባሉ አካላት ሥነ ምግባር በጎደላቸው ባለሙያዎችና ድርጅቶች መካከል በሚኖር መመሳጠር የሀገርና የህዝብ ሀብት እንዲመዘበር በማድረግና በየጊዜው እያደገና እየተስፋፋ ለመጣው ሙስናና ተገቢ ያልሆነ አሠራር እንዲነግስና ለኢንዱስትሪው ዕድገት ማነቆ ከመሆንም በላይ የሀገሪቱን የሀብት አጠቃቀም ክፉኛ እየጎዳው መሆኑ፡

3) የኢንዱስትሪውን የህግ ክፍተቶችንና የማስፈፀም አቅም ችግርን ሽፋን በማድረግ የሚፈፀሙ የተዛቡ ግብይቶች፣

4) ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ለሚመሩት ተቋም ከሚያስገኙት ትርፍ በበለጠ የሙያ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት ተነሳሽነት ዘርፉን ከሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲፀዳ ሊያግዝ በሚችል ደረጃ አስተዋፅኦ አለማድረግ፣

5) በኢንዱስትሪው የተደራጁ የሙያ ማህበራት ይህንን መጥፎ ገጽታ ለመለወጥ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የሚታወቅ ሲሆን ማህበራቱ ባለመጠናከራቸውና የመንግስት ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም በሚፈለገው ደረጃ ባለመገንባቱ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚታየው ሙስናና የስነ ምግባር መጓደል በኢንዱስትሪው ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑ ናቸው።

## 6.2 የግንባታ ግብዓት አቅርቦት

የግንባታ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን አቅርቦት የተሟሉ በማድረግ ረገድ ባለፉት ዓመታት የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከሚጠበቁት ልማቶች አንፃር ብዙ መሥራት እንደሚጠይቀን ከዳሰሳዎች ማየት ይቻላል።

### 6.2.1 የመሣሪያዎች አቅርቦት

1) በኮንስትራክሽን ማሽኖች አቅርቦትና የማጓጓዣ እጥረትን በማቃለል በኩልም የአቅም ግንባታ ድጋፎች ሲሰጡ ቆይተዋል። የኮንስትራክሽን ማሽኖችን ከቀረጥ ነጻ በማስገባት በረዥም ጊዜ ብድር አዲስ ለተቋቋሙት እና ለነባር ሥራ ተቋራጮች የተከፋፈሉ ሲሆን ለማሽን አከራዮች የብድር፣ የቀረጥ መጠን፣ የቦታ እና ሌሎች ተከታታይነትና ቀጣይነት አልነበራቸውም።

2) በአጠቃላይ በዕቅድ ዘመኑ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጎልበት ምቹ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው የግል የሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች፣ አማካሪዎች፣ የግንባታ ቁሳቁስ አቅራቢዎችና የኮንስትራክሽን ማሽን አከራዮች በብዛት ወደ ኢንዱስትሪው መግባት የጀመሩ ቢሆንም አሁን በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተያዘው የልማት ግብ አንፃር የሚጠየቀው ከፍተኛ የመሣሪያ አቅርቦት ሊቋቋም የሚችል አቅም የለም፡፡

### 6.2.2 ዋና ዋና ዕቃዎች አቅርቦት

የግንባታ ግብዓት ዕቃዎች ውስጥ በኢንዱስትሪው በከፍተኛ ሁኔታ እጥረት የሚታይባቸውና ዋና ዋና ተብለው በዚህ ክፍል የተወሰዱት ሲሚንቶ፣ ብረታ ብረትና የማጠናቀቂያ ዕቃዎች (ሴራሚክ፣ ቀለም፣ መስታወት፣ የኘላስቲክና ኤሌክትሪክ ዕቃዎች) ናቸው፡፡

#### 6.2.2.1 ሲሚንቶ

በሀገራችን የሲሚንቶ የተለያዩ የሲሞንቶ ዓይነቶች የሚመረቱ ቢሆንም ፍላጎታቸው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱትን ሁለት የሲሚንቶ ዓይነቶች ማለትም ፖርት ላንድ ፖዞላና እና ኦርዲናሪ ፖርትላንድ ናቸው፡፡፡

የሲሚንቶ አቅርቦት ለማሻሻል ጥረቶች የተረጉ ሲሆን በተለይም በአገር ውስጥ ሊሟላ ያልቻለውን የሲሚንቶ አቅርቦት መንግሥት ከውጭ አገር የውጭ ምንዛሪ በመመደብ እንዲገባ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከ1999-2002 ዓ.ም ባለው ጊዜ ከፍተኛ መጠን ያለው ሲሚንቶ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባና እንዲከፋፈል ለማድረግ ተገዷል፡፡ በዚህም ረገድ አቅርቦቱን አስተማማኝ ለማድረግ የሚያግዙ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተወስደው እንቅስቃሴዎች የተጀመሩ ቢሆንም የሀገር ውስጥ ከፊል ፍላጎትን በሀገር ምርት መሸፈን አልተቻለም፡፡

በአሁኑ ወቅት በማምረት ሂደት ላይ የሚገኙ ከፍተኛና አነስተኛ የማምረት አቅም ያላቸው የሲሚንቶ ማምረቻ ፋብሪካዎች ሙሉ የማምረት አቅም ለመጠቀም አልቻሉም ፡፡ ለዚህም፡-

1) የኤሌክትሪክ ሀይል እጥረትና ለተደጋጋሚ ጊዜያት በድንገት መቋረጥ፣
2) በንዑስ ዘርፉ በቂ ስልጠና የወሰደ የሰው ኃይል በሚፈለገው ጥራትና ብዛት ማግኘት አለመቻሉ፣
3) ክሊንከር ለማምረት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ኃይል ለማግኘት አማራጭ የኃይል ምንጭ /ድንጋይ ከሰል/ የመሳሰሉት ከአገር ውስጥ ማግኘት አለመቻል፣
4) ለንዑስ ዘርፉ ልማት የሚሰጡ ድጋፎችና አገልግሎቶች ዘገምተኛ መሆን፣
5) የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ጥራትና ደረጃን በተፈለገው ልክ መፈተሽና ማረጋገጥ የሚችል የተሟላ ዘመናዊ ላቦራቶሪ የሌለ መሆኑ፤

ከዚሁ በተጨማሪ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መዘግየት እንደዋናነት የሚታየው የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጡ ኩባንያዎች እስከአሁን ከአደረጉት እንቅስቃሴ አንፃር ሲታይ

አብዛኛዎቹ ኩባንያዎች ባወጡት መርሃ ግብር መሠረት መንቀሳቀስ ያለመቻላቸው ይጠቀሳሉ፡፡

### 6.2.2.2 ብረታ ብረት

ከብረታ ብረት ምርቶች የአርማታ ብረት እና ቶቦላሬ ባላቸው ከፍተኛ ፍላጎትና የምርት ዕጥረት በዚህ ሰነድ ለማየት የተሞከረ ሲሆን የአርማታ ብረት አቅርቦት ለማሻሻል ከ1999-2002 ዓ.ም ባለው ጊዜ የውጭ ምንዛሬ በማፍሰስ ከፍተኛ መጠን ያለው የአርማታ ብረት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባና እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ አርማታ ብረት አቅርቦት ረገድ በሀገር ውስጥ በግንባታው በነበረው ዕጥረት ምንም ያህል ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች እንዳልነበሩ ማየት ይቻላል፡፡

1) በኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ኩባንያዎች በአቀዱት መጠን ሊያመርቱ ያለመቻልና በድንገተኛ የኃይል መቆራረጥ ሠራተኛና የሥራ ሥምሪት በአግባቡ ባለመጠቀም ለተጨማሪ ወጪ መዳረግ፤
2) የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ማነስና የግብይት ሥርዓት የተዛባ መሆን፤በሌላ በኩል የሀገራችን የአርማታና ቱቦላሬ ብረቶች ንዑስ ክፍለ ኢንዱስትሪ የጥሬ ዕቃ ፍላጐት በአብዛኛው በውድቅዳቂ ብረታ ብረቶች (scraps) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
3) በውድቅዳቂ ብረት የሚመረቱ የአርማታ ብረቶች የጥራት ደረጃቸው መለስተኛ /Grade 40 ብቻ የሚያሟሉ/ ወይም ከዚያም ያነሰ በመሆኑ ፋብሪካዎቻችን የአመራረት ቴክኖሎጂ ደረጃንና የምርት ጥራት መለኪያዎችን ብቃትና ዘመናዊነትን የተላበሱ አለመሆን፣
4) በግብአት እጥረት የተነሳ የብረታ ብረት ንዑስ ክፍለ ኢንዱስትሪዎች በዓመት ከማምረት አቅማቸው ከ906 ሺ ቶን ውስጥ 40% /362 ሺ.ቶ ቶን/ ብቻ እንደሚያመርቱ ይታወቃል፡፡ ለዚህ ዋንኛው ምክንያት የሚሰበሰቡት ውድቅዳቂ ብረቶች በአይነታቸው ስለማይለዩና በጅምላ የማቅለጥ ሥራ ስለሚካሄድ ለከፍተኛ ግንባታ የሚያገለግለውን የደረጃ 60 (Grade 60) የአርማታ ብረትን ማማረት አለመቻሉ፣
5) የብረት በርና መስኮት ለመስራት የምንጠቀምባቸውን ቱቦላሬ (LTZ, RHS) ምርቶች የማምረት አቅም 87,500 ቶን ሲሆን ከዚህ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ እየተመረተ ያለው 37,160 (42%) ቶን ብቻ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 6.2.2.3 የማጠናቀቂያ ምርቶች

በሌሎች የፋብሪካ ምርቶችና የጥሬ ዕቃ አቅርቦቶች ዙሪያ ከፍተኛ ርብርብና ትኩረት ከሚጠይቁት ውስጥ የወለል እና የግድግዳ ሴራሚክ፣ የኤሌክትሪክና የሳኒታሪ የፕላስቲክ ምርት ዝቅተኛ መሆን፣ ዕጥረትና ዋጋ መናር በገሀድ የሚታዩ ችግሮች ሲሆኑ፡-

### ሀ. የሴራሚክ ውጤቶች

ለግንባታ ማጠናቀቂያ የሚያስፈልጉ የሴራሚክ ውጤቶች የሆኑ የሽንት ቤት መቀመጫ እና የእጅ መታጠቢያ በሀገር ውስጥ ያለው የታቦር ሴራሚክስ ፋብሪካ የማምረት አቅሙ ከፍላጉቱ ጋር ሲነፃፀር እጅግ አናሣ በመሆኑ አብዛኛው ከውጭ ሀገር የገባ ነው፡፡ የታቦር ሴራሚክስ ውጤቶች ፋብሪካ በአጠቃላይ በዓመት ወደ 6,000 ቶን የማምረት አቅም ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ 3,000 ቶን የግድግዳና ወለል ንጣፎች፣ 2,000 ቶን የገበታ እቃዎች እና 1,000 ቶን የመጸዳጃ ዕቃዎች የማምረት አቅም አለው፡፡ የድርጅቱ ዓመታዊ የማምረት አቅምም በአማካይ የአቅሙን 47 ከመቶ ብቻ ነው፡፡

### ለ. መስታወት (Glass sheet)

በአገራችን ከኮንስትራክሽን ዘርፉ ማደግ ጋር ተያይዞ ዝርግ መስታወት ምርት የሚያመረት ድርጅት ተቋቁሞ በዓመት 27,000 ቶን ዝርግ መስታወት በማምረት የማምረት አቅሙን (40,000 ቶን) 67.5 በመቶ ተጠቅሞ በማምረት ምርቱን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ባጋጠሙት የተለያዩ ችግሮች፡-

1) ድርጅቱ ለኃይል ምንጭነት የሚጠቀምበት ፈርነስ ኦይል ዋጋው በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ ለከፍተኛ የማምረቻ ወጪ የተዳረገ መሆኑ፤
2) ከውጭ ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ዕቃዎች የሚወጣው ወጪ ከፍተኛ መሆን፤
3) በዋጋ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ያለመሆን ናቸው፡፡

### ሐ. ቀለም (Paints)

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ሙሉ በሙሉ በግል ባለ ሃብቶች የተያዙ 12 /አስራ ሁለት/ የቀለም ፋብሪካዎች በሥራ ላይ ያሉ ሲሆን የአገሪቱ የቀለም ፍላጎት በነዚህ ፋብሪካዎች እየተሸፈነ ይገኛል፡፡

### መ. የፕላስቲክ ዉጤቶች

ጠቅላላ በሃገሪቱ ባሉት ከ300 በላይ የሚሆኑ የተለያየ አይነት የፕላስቲክ ውጤቶችን ለማምረት ከኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ፈቃድ የወሰዱ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከ150 በላይ የሚሆኑት የተለያዩ የፕላስቲክ ምርቶችን በማምርት ላይ የሚገኙ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በማህበር ተመዝግበውና በሀገሪቱ የሚመረተውን የፕላስቲክ ውጤቶች ከ70% በላይ የሚሸፍኑት 35 ያህል ድርጅቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ፋብሪካዎች በአብዛኛው ለኮንስትራክሽን ግንባታ የሚሆኑ የፕላስቲክ ውጤቶች በማምረት ላይ ቢገኙም በአሁኑ ሰዓት በተለያየ ምክንያቶች የማምረት አቅማቸው ከ50-60% ብቻ መሆኑን ከፋብሪካዎቹ የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

እነዚህ ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው የፕላስቲክ ምርቶች በገበያው ከሚፈለጉት ምርት ዓይነት አንጻር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በየአመቱ ከፍተኛ በሆነ መጠንና የውጭ ምንዛሪ ከውጭ እንደሚገባ ለአብነት ብናይ በ2008(እ.አ.አ.) የፕላስቲክ ውጤት ምርቶች ለ422 ሺህ ቶን ምርት በ1 ቢሊዮን ብር ገደማ ለፕላስቲክ ግብዓት ምርቶች 77 ሺህ ቶን ምርት በ1.2 ቢሊዮን ብር ገደማ እንዲገባ ግድ ሆኗል፡፡

**ሠ. የኤሌክትሪክ ዕቃዎች**

በኤሌክትሪክ ዕቃዎች ምርት ላይ የተሰማሩ ተቋማት አራት ሲሆኑ  ነዚም ኤል ሲዊዲ ኬብል ኢትዮጵያ፣ ዩሮ ኬብል፣ ኢትዮ ቻይና አይ ቴክና ኢትዮ ፕላስቲክ ናቸው፡፡ ኢትዮ ፕላስቲክ ስካቶላና ኮንድዩት የሚያመርት ሲሆን ኢትዮ ቻይና አይ ቴክ ደግሞ ሶኬትና ማብሪያና ማጥፊያ የሚያመርት ነው፡፡ ኢትዮ ፕላስቲክ ጨምሮ ቀሪዎቹ ሁለቱ  ኬብልና የኤሌክትሪክ ሽቦ በማምረት ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡ በኩባንያዎቹ የሚቀርቡት ምርቶች የሀገሪቷን ፍላጎት ለማሟላት የሚችል አቅም እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሆኖም፡-

1) የመንግስት ግዢ የሚያከናውነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ  ይል ኮርፖሬሽን የኮንትራት ውሉ  ስከ አንድ ዓመት በመሆኑና በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ የዓለም የኮፐር ዋጋ ስለሚዋዥቅ ገዥው ገቢውን የሚያጣ መሆኑ፤
2) ከውጪ የሚገቡ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ተመሳሳይ ምርቶች የውድድር ሜዳውን ማፋለሳቸው እንደ ችግር ይጠቀሳሉ፡፡

**6.2.2.4 በአካባቢ የግንባታ ዕቃዎች (ጠጠር፣ አሸዋ፣ ድንጋይና ምርጥ አፈር)**

1) በአካባቢ የግንባታ እቃዎች አቅርቦት በኩልም በርካታ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርኘራይዞች በምርቱ ላይ በስፋት እንዲሳተፉ በሥልጠና፣ በፋይናንስና በአደረጃጀት ድጋፍ በመስጠቱ የአካባቢው ግንባታ ቁሳቁሶች ምርት መጠን እንዲጨምር የተደረገ ቢሆንም አቅርቦቱ ፍላጎቱን ሊሸፍን አልቻለም፡፡
2) ለእነዚህ እና ለሌሎችም የግንባታ ዕቃዎች ወደ ገበያ (የግንባታ ቦታዎች) ማድረሻ የሚሆኑ ገልባጭ መኪናዎች በረዥም ጊዜ ብድር አምራቾቹ እንዲያገኙ ቢደረግም ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ የአካባቢው ማቴሪያሎች ጠጠር፣ አሸዋ፣ የድንጋይና የምርጥ አፈር ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ ከመከሰት ከእጥረት የሚገታው አልሆነም፡፡

## 6.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተወዳዳሪነት አቅም

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እሴት ሰንሰለት ላይ በመመርኮዝ ጥራትና ምርታማነትን የማረጋገጥ አሰራሮች ላይ ተመስርቶ ሥራዎችን ማከናወን ላይ ውስንነቶች አሉ፡፡ ይህ በመሆኑ በሀገራችን በየትኛውም ደረጃ የሚከናወኑ ግንባታዎች፣ የዲዛይን ጥናቶች፣ ግንባታ ሥራዎች ጥራት፣ ቁጥጥርና ክትትል ድጋፍ ሊሰጣቸው የሚያስችል ጠንካራ የኮንስትራክሽን አመራር ሬጉላተሪ ሥርዓት አልተፈጠረም፡፡ ይህ በመሆኑ ምክንያት በኢንዱስትሪው የሚሰጡ አገልግሎቶች ቅልጥፍና የሚጎላቸው፣ ከውጤት አንጻር ሲመዘኑም

አናሳነት የሚታይባቸው ለብክነት የተጋለጡ በመሆኑ የመወዳደር አቅማቸው እጅግ አሳሳቢ ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች እንደምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

### 6.3.1 በግንባታ አገልግሎት አቅርቦት የተሟላ አለመሆን

በአንድ ሃገር በአንድ ወቅት ሊከናወን የሚችል የግንባታ መጠን የኢንዱስትሪውን አቅም ደረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ አኳያ በአገራችን ከቅርብ አመታት ወዲህ እየታየ ያለው ከፍተኛ የግንባታ አገልግሎት ፍላጎት ኢንዱስትሪው መሸከም ከሚችለው አቅም በላይ እየሆነ በመምጣቱ የሚካሄደው የግንባታ መጠን ከሚፈለገው አንጻር አነስተኛ መሆኑ ይታያል፡፡ ለአብነት ያህል በአገሪቱ ባሉ ከተሞች መተግበር በተጀመረው የቤቶች ልማት ፕሮግራም ላይ እንደታየው በሁሉም ክልሎች በርካታ ቤቶችን በአንድ ጊዜ አቅዶ ለመገንባት የተቋራጮች እና አማካሪዎች፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ እና እንዲሁም የመንግስታዊ አስፈጻሚ አካላት አቅም ማነስ በማጋጠሙ እየተገነቡ ያሉት ቤቶች ብዛት ከዕቅዱ አንጻር ሲታይ ያነሰ እንዲሆን አስገድዷል፡፡ ከፍተኛ ኢንቨስትመንትና አቅም በሚጠይቁ በኃይል ማመንጫ ሙሉ በሙሉ፣ በመንገድ ልማት ረገድም በሚፈለገው መጠን ግንባታ ለማከናወንና ለማማከር ብቁ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ለማግኘት አዳጋች ሲሆን ልማቱ እንዳይስተጓጎልም በከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ አገልግሎቱ ከውጪ አገር ድርጅቶች እየተገዛ ይገኛል፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር ለበርካታ የልማት ዕቅዶች የጊዜ መራዘምና የዋጋ ንረትና የተለያዩ የይገባኛል ጥያቄዎችን በማስነሳትና መንስኤ በመሆን በተከናወኑት የልማት ሥራዎች መጠን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በተቋራጭና በአማካሪ ኩባንያ ከሚታዩ ችግሮች ውስጥ፡-

1) የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች ቁጥር ማነስ ዋነኛው ወደሥራ ተቋራጭነት እና አማካሪነት ለመግባት የሚጠየቁ የፋይናንስ እና ማሽነሪ አቅሞች ከፍተኛ መሆን፣
2) ለንዑስ ሥራ ተቋራጭነት እና ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት በኢንዱስትሪው የሚደረጉ የአቅም ግንባታ ድጋፎች ውስን መሆናቸው፤
3) ከፍተኛ ልምድንና ብቃትን በሚጠይቁ ሥራዎች ዙሪያ የሚሳተፉ አማካሪ ኩባንያዎች ቁጥር ማነስና በአንዳንድ ሙያዎች እንዲያውም ጭራሹን የሌሉ መሆን፤
4) በሥራ ተቋራጭነት እና አማካሪነት የተሰማሩ አካላት ብቃት ያለውን ባለሙያ ያለማሠራት፤
5) በአማካሪ በሥራ ተቋራጭ ኩባንያዎች በሁለቱም ተቋማት ለዲዛይንም ሆነ ለግንባታ ጥራት ያለ ተነሳሽነት ወይም ዝግጁነት ለጊዜ ከሚሰጡት ትኩረት በእኩል ደረጃ ላይ ባለመሆኑ ለወጪና ለጊዜ መጨመር ምክንያት በመሆኑ የአፈፃፀም ብቃታቸው ዝቅተኛ ሆኖ መታየቱ፤
6) አዲስ ሆነው ወደሥራ ተቋራጭነት እና አማካሪነት የሚቀላቀሉ ተቋማት ሥራ ለማግኘት የሚያስችል የጀማሪ መግቢያ መስፈርት ባለመኖሩ ከሥራ ጋር ባለመተሳሰራቸው የሚወጡ ጨረታዎችን አሸንፈው ወደሥራ ለመግባት ሳይችሉ እንዲቆዩ እንዲሁም ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ ማድረጉ፤

### 6.3.2 በግንባታዎች የአፈፃፀም ደረጃ

#### 6.3.2.1 በጊዜ ያለመጠናቀቅ

ባለፉት ዓመታት ከተከናወኑ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ መገንዘብ እንደሚቻለውም በፕሮጀክት ጊዜ መራዘም ምክንያት በተለያየ መልኩ የዋጋ መጨመር ታይቷል። በርካታ የልማት ዕቅዶችም ተጓተዋል።ይህም ውስን በሆነው የአገሪቱ ሃብት በተቻለ ፍጥነት ለህብረተሰቡ መዳረስ ይገባው የነበረ አገልግሎት እንዲዘገይ አድርጓል።

ከዚህ አንጻር በአገራችን ግንባታዎች በአብዛኛው ከታቀደላቸው ጊዜ እጅግ ዘግይተው የሚጠናቀቁ ሲሆን በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ እንደሚታየውም የታቀደውን ጊዜ እጥፍ የሚወስዱበት አጋጣሚ ብዙ ነው። እንደምክንያት ጎልተው ከሚታዩት ውስጥ፡-

1) ፕሮጀክቶች ከፅንሰታቸው የጥናትና፣ የጠራ ዕቅድ፣ የዲዛይንና የሥራ ዝርዝር ጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ለተደጋጋሚ ጊዜ ለዲዛይን ክለሳ የሚዳረጉ መሆኑ፣

2) የቅድሚያ ክፍያ ለፕሮጀክቱ ሥራና ግብዓቶች እንዲውል የማድረግ አሠራርና ቁጥጥር ደካማ መሆን፣

3) በተጨማሪና የለዉጥ ስራዎች አስተዳደርና በአጠቃላይ በግብዓት አቅርቦት፣ በፕሮጀክት ግንባታና ውለታ አስተዳደር ብቃት ማነስ፣ ተነሳሽነት ያለመኖር፣

4) አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች በሥራው መጓተት ምክንያት ለሚመጣው የጊዜ መራዘም እና የፕሮጀክት ወጪ ንረት ተጠያቂ የሚያስደርጋቸው ሥራዓት ያለመኖር፣ በተለይ አማካሪው ፕሮጀክቱ ባልተንቀሳቀሰበትም ወቅት ክፍያውን እንዳያገኝ የሚከላከል አሠራር ያለመኖሩ ለጊዜ መራዘም እንደ ዋነኛ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ።

#### 6.3.2.2 የግንባታ ወጪ ንረት

በከፍተኛ ወጪ የሚሰሩ ግንባታዎች በጊዜ መራዘም ከሚከሰቱ የኦፐሬሽንና የዋጋ ጭማሪ ወጪዎች በተጨማሪ የኢንዱስትሪው መወዳደርና አቅም የሚገቱ ጉዳዮች፡-

1) የግንባታ ፕሮጀክት ጥናቶች በተገቢው ጥራትና ብቃት ያለመሰራት፣ በተለዋዋጭ ዲዛይኖችና የለውጥ ሥራዎች ምክንያት በግንባታዎች ሂደት ወቅት ላልታሰቡ ወጪዎች መዳረጋቸው፣

2) በቴክኖሎጂ የታገዘ የፕሮጀክት አመራር፣ የወጪ ቆጣቢ ዲዛይኖች፣ የአገነባብ ቴክኖሎጂዎችና ቁሳቁሶች አጠቃቀም በፍጥነት የማላመድ አካሄድ መከተል ባለመቻላችን ወጪ ቆጣቢ በሆኑት ቁሳቁሶችና ዘዴዎች ተጠቃሚ መሆን አለመቻሉ፣

3) አገራዊው የኢንዱስትሪው አቅም ባለመጎልበቱም በስፋት ባልተገባባቸው የኮንስትራክሽን አገልግሎትና የግንባታ ዕቃዎች በከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ከውጪ መገዛታቸው የግንባታዎችን ወጪ መናር፣

4) ቀልጣፋ በሆነ ኮንትራክት አስተዳደር ሥርዓት የሚመራ የጨረታና የውስታ አሠራር አለመኖሩ ግልጽና ፍትሃዊ የገበያ ዉድድር ማስፈን ባለመቻሉ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዕድገት የሚጉትትና የፋይናንስ ብክነትን የሚያስከትል መሆኑ፣

### 6.3.2.3 የግንባታ ጥራት መጓደል

በአገራችን እየተደረጉ ካሉና ቀደም ብለው በተፈጸሙ የግንባታ ውጤቶች ላይ የጥራት መጓደሎች እንዳሉ ምልክቶች ይታያሉ፡፡ በዋና ዋና ከሚጠቀሱት ውስጥ፡-

1) በጥራት መጓደሎች ምክንያት ግንባታዎች የአገልግሎት ዘመናቸው ሳያልቅ ለእድሳት የሚዳረጉበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑ፣

2) የህንፃዎችና የሌሎችም ግንባታ ሥራዎች በቶሎ ለብልሽት መዳረግ ከፍተኛ የጥገና ወጪ የሚያስከትል ሲሆን ለሌላ ተጨማሪ አገልግሎት መዋል ይችል የነበረ መዋዕለ ንዋይ በአንድ አገልግሎት ላይ በተደጋጋሚ እንዲውል መዳረጉ፣

3) በኃይል ማመንጫ በተሠሩ ግንባታዎች የሀገራችን ተቋማትና ባለሙያዎች በዲዛይንና በግንባታ ቴክኖሎጂ ክህሎት ሽግግር ራሳቸውን እንዲችሉ ካለመደረጉም የሚሠሩ ዲዛይኖችንና ግንባታዎችን ጥራትና ደረጃ የሚቆጣጠር ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

4) የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ደረጃቸውን ለማስጠበቅ ዲዛይናቸውንና የሥራ ዝርዝር በሙያው በቂ ዕውቀትና የሥራ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲሠሩ፣ በአዋጪ የገበያ ውድድር የጨረታ ምዘና እንዲከናወን የተቆጣጣሪና አስፈፃሚ አካላት አቅም ግንባታ እንዲሁም ለሥራ ተቋራጮች በስልጠና፣ በሰው ሃይል፣ በፋይናንስና በመሣሪያ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በሚፈለገው ደረጃ ታቅዶ ያለመሠራቱ፣

5) የግንባታና ዲዛይን ጥራት ለማስጠበቅ የሚችሉና በየጊዜው የሚሻሻሉ ደረጃቸውን የጠበቁ የኮንስትራክሽን ህጎች በተፈለገው መጠን በሥራ ላይ ባለመዋላቸው እንዲሁም ሥራውን የሚቆጣጠሩት አማካሪ ድርጅቶች ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል በተሟላ መልኩ የማይተገበር በመሆኑ የግንባታ ውጤቶች የጥራት ጉድለት ያለባቸውና ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሆናቸው፣

6) በሀገሪቱ የጥራት መፈተሻ መሣሪያዎችና የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች በሚያስፈልግ መጠን ያለመኖር፣

## 6.4 የሠራተኞች እና የህብረተሰቡ ጤናና ደህንነት፣

የኮንስትራክሽን ሥራ በርካታ የሰው ኃይል የሚያሳትፍና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑበት እንደመሆኑ ጥንቃቄ ካልተወሰደ በኢንዱስትሪው የተሰማሩ ሰዎችንም ሆነ በሥራው አካባቢ የሚገኙትን ለከፍተኛ ጉዳት የሚያጋልጥ ነው፡፡ በሀገራችን ያለውን እንቅስቃሴ ስናይ፡-

1) በኢንዱስትሪው የሚ የውን የጤናና የደህንነት አደጋ የተሟላ ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ በማድረግ የጉዳት መጠኑን መቀነስ የሚቻል ቢሆንም ይህ ባለመደረጉ ጉዳቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መገኘቱ፣
2) በሃገራችን በተለያዩ አካላት በሚካሄዱ ትላልቅ የግንባታ ሥራዎች በዘልማድ ከሚደረጉ ዝግጅቶችና ጥንቃቄዎች በስተቀር የሠራተኛውን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያግዙና የሚያስገድድ ደንብ ባለመኖር በግንባታዎች አካባቢ ከሞት እስከ ዝቅተኛ የጤና ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፣
3) በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሚታዩት የጤናና የደህንነት አደጋዎች እንደመንስዔ ከሚጠቀሱትና በድርጅቶች የደህንነት ፖሊሲዎች መካተት ከሚገባቸው ውስጥ፡-
   - የግንባታ መሳሪያዎችና መከላከያ ልብሶች አለመሟላት፣ የመፀዳጃና የመታጠቢያ አገልግሎት አለማቅረብ፣ መርዛማና አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን ሠራተኞች እንዲያውቋቸው አለማድረግ፣
   - የሥራ ቦታን ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎች ነጻ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ጥንቃቄዎች ዝቅተኛነት፣ በሠራተኞች የትራንስፖርት እና የግንባታ ዕቃዎች ምልልስ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ አለማድረግ፣ ለግንባታ ሥራ የሚውሉ መወጣጫዎችን በጥራት፣ በጥንካሬና በተገቢው ቁስ አለመሥራት፣ ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ሥራዎች ላይ ማስታወቂያ አለመለጠፍና የተላላጡ የኤሌክትሪክ መስመሮችን አለመጠገን፣
   - በስፋት ከሚታዩት ጉድለቶች ለሰራተኞች የተሟላ የአደጋ መከላከያ ስልጠና አለመስጠት፣ ለከባድ ማሽን ኦፕሬተሮች ተገቢውንና ተከታታይ የብቃት ሥልጠና አለመስጠት፣ ለከባድ ማሣሪያዎች በየጊዜው ሙሉ ጥገና የሚያገኙበት ማዕከል አለመኖር የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## 6.5 የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ መጎዳት

ኢንዱስትሪው በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ከሚያደርሳቸው ጥፋቶች ውስጥ ግንባታ የሚከናወንባቸው ቦታዎች፣ የተፈጥሮ የግንባታ ቁሳቁሶች ማምረቻ ቦታዎችና የፋብሪካ የግንባታ ዕቃዎች ማምረቻ ቦታዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ብክለት ዋነኛቹ ሲሆኑ፡-

1) የግንባታ ዕቃዎች የምርት ሂደት ከተፈጥሮ ሃብት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን ለደኖች ያለአግባብ መጨፍጨፍና መራቆት፣ ለአየርና ውሃ ብክለት፣ ለአፈር መሸርሸርና ለአካባቢ ብክለት የራሳቸው አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑ፣
2) በከተሞች በሚደረጉ የግንባታ ሥራዎችም የግንባታ ተረፈ ምርቶች በየመንገዱና በመኖሪያ አካባቢዎች የሚከማቹ መሆናቸው ነዋሪዎችን ለተለያዩ አደጋዎች በማጋለጥ ላይ መገኘታቸው፣

3) በሀገራችንም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት እየተሰጠ የመጣ ቢሆንም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ይህ ነው በሚባል እየተሰራበት አይደለም፡፡ ለነዚህ በአካባቢ ሀብት ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች መከሰት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ፡-

- በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ስለአካባቢ ጥበቃ ተገቢው ግንዛቤ ያለመኖር፣
- የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ያለማድረግ፣ ለተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ ትኩረት ያለመስጠት፣
- ልማትንና የተፈጥሮ አካባቢን ለማቻቻል የሚያስችል ስልት በመቅረጽ ለመተግበር የሚደረገው ጥረት የሚፈለገውን ያህል ያለመሆን፣
- ቁጥጥር ያለመኖሩ፣ የአስፈፃሚው አካል አቅም አናሳ መሆንና ቅንጅታዊ አሰራር ያለመኖር ናቸው፡፡

## II. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማትና ማስፈፀም አቅም ግንባታ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

በሃገራችን ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግብይት ሰፊውን የቀጣሪነት ድርሻ መንግስት የያዘበት አወቃቀር የተከተለ ቢሆንም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በግሉም ዘርፍ ለተለያዩ ልማቶች የሚከናወኑ ግንባታዎች ቀላል የማይባል ደርሻ እንዳላቸው ማየት ይቻላል፡፡ የኮንስትራክሽን ሥራዎቻችን በአማካሪዎች፣ በሥራ ተቋራጮችና በአሰሪዎች መካከል በሚደረግ የውለታ ሥርዓት ሂደት የሚፈጸም ሲሆን ይህንን በላቀ ደረጃ ዉጤታማ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር በቀጣይ ሥራዎቻችን በሁሉም የመሰረተ ልማትና የህንጻ ግንባታ አፈጻጸማችን ከዚህ የሚከተሉት በልዩ ትኩረት የሚታዩ ይሆናል፡፡

### 1. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የፖሊሲ ማዕቀፍና አሠራር ሥርዓት ያለመኖር

#### 1.1 የፖሊሲ ማዕቀፍ በተመለከተ፣

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማዕቀፍ ስንል ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚመራበት ሲሆን በውስጡም ፖሊሲ፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ስታንዳርዶችና ማንዋሎችን እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ለማለት ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከሚያንቀሳቅሰው ሰፊ የሰው ኃይል እና ፋይናንስ አንፃር ወጥ የሆነ ሀገራዊ ማዕቀፍ መኖሩ የግድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ይህ ከባድ ክፍተት ታይቶ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ በመንግስት ማጽደቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

#### 1.2 የህግና አሠራር ሥርዓት በተመለከተ፣

በሕንፃው፣በመንገድ፣ በውኃ፣ በመስኖ ፣ በግድብ፣ በኃይል ማመንጫ ልማታችን የተሳካ እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዙን የሠራነው ወይም በስርዓት የተዋስነው መሠረታዊ የቴክኒክ ሰነዶች የሉንም፡፡ ስታንዳርድ ስፔስፊኬሽን ዲዛይን ማንዋል ፣ኮንስትራክሽን ካሊቲ ኮንትሮል፣ ኮንስትራክሽን ዋጋ ትንታኔ መመሪያ፣ ኮንስትራክሽን ሳይት ማኔጅመንት ጋይድ ላይን፣ እንዲሁም በርካታ ኮዶች ወዘተ… የመሳሰሉት ስራ ላይ አልዋሉም፡፡ እነዚሁ ቴክኒካዊ ሰነዶች በሀገራችን ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ተመስረተው በሁሉም ዘርፍ መዘጋጀታቸው በሁለት አብይ ምክንያቶች ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡ አንደኛ የምንገነባቸው ፕሮጀክቶች ወጪ ቆጣቢነትና ጥራት ማስጠበቅ ጉዳይ በቅድሚያ መመለስ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ተወዳዳሪ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፎቻችን ኢኮኖሚያዊ ሆነው እንዲጠናቀቁና በሂደትም የሚገነባው ሀገራዊ አቅም ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማስቻል በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

#### 1.3 ኮንስትራክሽን አመራር ሁኔታ፣

በሀገራችን የኮንስትራክሽን ሥራዎች በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ከዓመት ዓመት ዕድገት በማሳየት ላይ ያለ ሲሆን የዕድገቱን መስመር ተከትሎ ዘርፉን በመደገፍ የማስፈጸም አቅማችንን የማሳደግ ሁኔታዎች

እምብዛም ትኩረት አልተሰጣቸውም ማለት ይቻላል፡፡ የኮንስትራክሽን አመራር ሁኔታ ችግር አለበት ሲባል በዘርፉ ውስጥ ተዋናይ ለሆኑት አካላት የሚመሩበት ሥርዓት፣ ሥራን ማዕከል ባደረገ ግንባታዎች ጥራታቸው ተጠብቆ በተመጣጣኝ ወጪ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል የተመቻቸ ሜዳ ለመፍጠር እንቀስቃሴ አልተደረገም፡፡ ስለሆነም በኮንስትራክሽን ዘርፉ ለህንፃ ግንባታ፣ ለመንገድ፣ ለሌሎች መሠረተ ልማቶች ጭምር እንዴት መመራት እንዳለባቸው የሚያሳዩን ቴክኒካዊና ፖለቲካዊ አቅጣጫዎቻችን ተመጋግበው ዘርፉ በሃገራዊ ልማት መስክ የሚጠበቅበትን እንዲወጣ በሚያስችል ደረጃና አሁን የተፈጠረውን የዘርፉን አወቃቀር በቃኝ መልኩ ባለመሆናቸው ወጥነት ለሌለውና ለተዛነፈ አሠራር የተጋለጠ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ በዘርፉ የተመዘገቡት ውጤቶች ቢኖሩም ከሚጠበቀው አንፃር ሲታይ በርካታ ብክነት የሚታይበት፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጠበት፣ የሥራ ጥራት መጓደል የሚታይበት፣ የወጪ ንረት የሚስተዋልበት፣ ብቃት የሌለው አመራር የሚታይበት፣ በኪራይ ሰብሳቢነት መሠረት ላይ የተገነባ የኮንስትራክሽን አመራር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በድምሩ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪያችን ውስጥ የሚታየው ቁልፍ ችግር የኮንስትራክሽን አመራር ሲሆን ከዚህ የሚመነጩ ዝርዝር ችግሮችን በተጓዳኝ ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ በመሆኑም:-

1) በኮንስትራክሽን ክፍለ ኢኮኖሚው ብቃት ያለው አመራር ለመስጠት የሚያስችሉ በርካታ የአሰራር ሥርዓቶች /ከዲዛይን፣ ከቁጥጥር እና ፕሮጀክት አስተዳደር/ ጋር ተያይዞ ያሉትን መፈተሽና ማስተካከል፣

2) የግንባታዎች ጥራትና ደህንነት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢነት አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣

3) የኮንስትራክሽን አመራራችን ብቃት የሚለካው በመጀመሪያ የህዝቡን የልማት ፍላጎት ለማርካት ታቅዶ ወደ መሬት በማውረድ ሂደት በየደረጃው ያለውን የጥራት እርከን አልፎ በሚፈለገው ጊዜ ሲጠናቀቅ በመሆኑ ለዲዛይንና ግንባታ ጊዜ አጠቃቀም ልዩ ትኩረት መስጠት፣

4) በዘርፉ ተዋናይ የሆኑት ሁሉ ለተሳካ ውጤት በቅንጅት ለመስራት የሚያስችላቸው የፖለቲካም ሆነ የቴክኒካዊ  አመራር ብቃት ማሳደግ፣

5) የግንባታ ስራዎቻችን ዕድገት እያሳዩ ከመሄድ ጋር ተከትሎ የመጣውን  የግንባታ ዋጋ ንረትና ያልተስተካከለ ግብይት መቆጣጠር የሚያስችለን አሰራር መፍጠር፣

6) ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ጠንካራ ፖለቲካዊና ቴክኒካዊ አመራር በየደረጃው በመፍጠር  የምንገነባው ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ እንድምታ ከኮንስትክሽን አንፃር ተቃኝቶ አመራራችን ከውጤት ጋር ተያይዞ እየተመዘነ ፈጣን ለውጥ ሊያመጣ በሚችልበት አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችል ቁርጠኝነት መፍጠር፣

## 1.4 የአመለካከት፣ የሥነ-ምግባርና ክህሎት ክፍተቶች

በአስፈጻሚዎች፣ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች አገልግሎት የተሰማራውና ገበያው የሚያቀርባቸው የሰው ኃይል የሚታይበት ኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት እየጎላ በመምጣቱ ይህንን ገፅታ መቀየር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የአመለካከት ግንባታ በሂደት የሚመጣና በዘርፉ በሚሳተፉ አካላት የጋራ ተሳትፎ ሊፈጸም የሚችል ተግባር በመሆኑ በዘርፉ የሚሰማራው ሰው ሃይል የሚታይበትን አመለካከትና ሥነ-ምግባር ችግር ማስተካከል እና መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡

ኮንስትራክሽንና ዲዛይን ተግባራቶች ከሚጠይቁት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ብቻ በመነሳት ያልተገባ ክፍያ የመፈለግና መጠየቅ አባዜዎች በሰው ኃይላችን በአመለካከት ደረጃ ላይ በስፋት የሚታዩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከሙያ ብቃት ውጪ ባለሙያዎች በማሰማራት የአገልገሎት ጥራት በማውረድ አላስፈላጊ ጥቅም ለማግበስበስ የሚደረጉ ተግባራት በመንገድ፣ በህንጻ፣ በውሃና በሌሎችም ኮንስትራክሽኖች ያሉ ችግሮች እንደመሆናቸው እነዚህ አመለካከቶችና ሙያዊ የሥነ-ምግባር ችግሮች በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ የሚያሳርፉት አሉታዊ ተፅዕኖ በማጤን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ተገቢ ይሆናል፡፡

በሀገራችን ነፃና ፍትሃዊ የገበያ ውድድር የሰፈነበት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመገንባት በሚደረገው ትግል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ሰፊ ድርሻ ያለው ሲሆን በምህንድስና ባለሙያው፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ ባሉት ባለሙያዎች፣ በዘርፉ በሚሳተፉ ባለድርሻዎችና አስፈጻሚዎች በአመለካከትና በክህሎት የሚታይባቸውን ችግር ለይቶ ማስተካከል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በመሆኑም፣

1) በሕንፃና በመሠረተ ልማት ግንባታዎች ዕሴት ሰንሰለት ላይ በመመርኮዝ ጥራትና ምርታማነትን የሚያረጋግጥ አሠራሮችን መዘርጋት ላይ የተመሰረተ ፕሮጀክቶችን የማከናወን መሠረት መጣል፣
2) የዲዛይን ጥናቶች፣የግንባታ ሥራዎች፣የቁጥጥርና ክትትል ድጋፍ ሊሰጣቸው የሚያስችል የኮንስትራክሽን አመራርና የሬጉላተሪ ሥርዓት በመፍጠር በዘርፉ ግልፀኝነት እንዲጎለብት ማድረግ፣
3) ለአዳዲስ ፈጠራዎችና አሰራሮች የተዘጋጀ ሀገራዊ የምህንድስና አቅም በመፍጠር የተሻሻሉ አሰራሮችና ወደ ኢንዱስትሪው እንዲገቡ ማመቻቸት፣
4) ለስነ ምግባር መጓደል በር የሚከፍቱ ቀዳዳዎችን በመደፈን ሙያዊ ዲስፕሊንና የሥራ ክብር እንዲያድግ ማድረግ፣
5) በአማካሪ፣ በሥራ ተቋራጭ እና በፕሮጀክት ባለቤቶች መካከል ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት በአስተሳሰብ እና በተግባር የግልፅነትና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣
6) የኮንስትራክሽን አመራራችን እድገትና ቅልጥፍና እንዲሁም ውጤት የሚለካው በፕሮጀክት ስኬት ላይ በመሆኑ በሂደቱ ተሳታፊ በሆኑት አካላት የተናጠል ድርሻና ቅንጅታዊ ስራ ትኩረት መስጠት፣

7) በፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ በሚፈጠር አላስፈላጊ ውዝግብ እና አለመግባባት የሚጠፋው ጊዜና ገንዘብ ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር መፍጠር፣

8) ሀገራዊ የልማት አቅጣጫ የተከተለ ወጪ ቆጣቢ የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር እንዲሰፍን የሚያስችል የጋራ አስተሳሰብ መፍጠር፣

## 2. የሰው ኃይሉ የማስፈፀም አቅም ውስንነት

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፉ በዓመት በአማካይ እስከ 400,000 ድረስ የሚጠጉ ሰው ኃይሎችን በማሰማራት ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል መሆኑ ግንዛቤ ተይዞ ባለፉት 5 ዓመታት በተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮግራማችን ሰፊ የስራ ዕድል ፈጠራ ስራ የተከናወነበት ነው፡፡ በሌሎችም ዘርፎች ቢሆን ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለሙያ ደረጃ የበኩሉን ሚና እንደተጫወተ መገመት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉም የዘርፉ አደረጃጀት የሚገኙ ኃይሎች /Workforce/ ምርታማነት ፍፁም አጥጋቢ እንዳልነበረ አፈጻጸሙ ያስገነዝባል፡፡ የኢንዱስትሪው ተወዳዳሪነት አቅም ሊገነባ የሚችለው የተሰማራው የሰው ኃይል ምርታማነት በማረጋገጥ በመሆኑ ለዚሁም ጉዳይ መነሻው የሚጀመረው የክህሎትና የአመለካከት ዝንፈት በማስተካከል ላይ የሚያተኮር ይሆናል፡፡ በመሆኑም፣

1) በግሉም ሆነ በመንግስት ፕሮጀክቶቻችን የሚሠማራው ሰው ኃይል ለተሰማራበት ስራ የሚመጥን ዕውቀት እንዲጨብጥ የማድረግ  አሰራር መፍጠር፣
2) በሥራ ቦታ ላይ ተገቢውን አመራር ለመስጠትና ለመቀበል የሚያስችል የሰው ሃይል ማልማት አቅጣጫ መከተል፣
3) በኢንዱስትሪው የሚታየውን ክፍተት መሰረት ያደረገ ስልጠናና አፈጻጸም መከተል፣
4) በኮንስትራክሽን ዘርፉ የምናሰማራው ሰው ኃይል በየደረጃው ለሚሰጠው አገልግሎት በየሙያ ደረጃው ሊመዘን የሚችልበትና ውጤቱ እየተለካ ዋጋው የሚወሰንበት ሥርዓትና የሰው ሃይል መረጃ መገንባት፣
5) በሁሉም አደረጃጀታችን የሚገኘው ሰው ኃይላችን በማስፈፀም አቅሙና በሥነ ምግባሩ እየተገነባ የላቀ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት፤ የሰው ሃይል ልማት ጥራት ፈር እንዲይዝ ማድረግ፣

## 3. የሥራ ተቋራጭ አቅም ማነስ፣

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ተሳትፎ ከዓመት ዓመት ዕድገት እያሳየ ሲሆን የተገነባው የሥራ ተቋራጭ አቅምና እንቅስቃሴ ሲታይ በአመለካከቱም ሆነ በቁመናው አስተማማኝ ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም፡፡ በመሆኑም ለአንዳንድ ሥራዎች የውጪ ሀገር ሥራ ተቋራጮችን በማስገባት ለማሰራት እየተገደድንባቸው ያሉ አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኩል ከሚደረገው የምዝገባ መረጃ ላይ እንደሚታየው በርካታው ቁጥር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ሲሆን ይህም ኃይል ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ የሚሠማራ ሳይሆን ፈቃዱን እያከራየ የሚኖር ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተመሳሳይ መልኩ በትልልቆቹ ደረጃዎችም ላይ የሚንፀባረቅ ነዉ፡፡ በዚሁ መነሻነት የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ይደረግባቸዋል፡-

1) በሕንፃ፣ በመንገድ እንዲሁም በውኃና ኢነርጂው ዘርፍ ግንባታ የሚሳተፉ ተቋራጮቻችን በመካከላቸው በሚደረግ ፍትሃዊ የገበያ ውድድር ብቻ ተመስርቶ በገቡት ውለታ ስምምነት ለአሰሪዎቻቸው የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉበት አሰራር መፍጠር፣

2) አሁን በስራ ላይ ያሉት ስራ ተቋራጮቻችን በቀጣይ የሚገነቡትንም ጭምር በግብይት ወቅት የሚያደርጉትን አጀብ /Collusive practice/ የሚጸየፉ ሆነው እንዲያድጉ ማቃናት እና የሚታይባቸውን የአመለካከትና ክህሎት ችግር ማስተካከል፣

3) በሥራ ተቋራጮቻችን የፕሮጀክት አፈጻጸም ሂደት የሚንፀባረቀውን የሥነ-ምግባር መጓደል ችግር በመዋጋት መቅረፍ፣

4) የሥራ ተቋራጮቻችን በሳይንሳዊና በለውጥ አመራር እየተመሩ በሂደት ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸው አደረጃጀት ላይ ለመድረስ አቅደው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

5) የስራ ተቋራጮች የተወዳዳሪነት አቅም እንዲጎለብት ስራዎችን በሃገር በቀል ኩባኒያዎች የሚሰሩበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

6) የኮንስትራክሽን ኩባኒያዎች የምዝገባ ሥርዓት የማሸነሪ አቅርቦትና የሰው ኃይል በዋናነት መሠረት አድርጎ የሚፈፀም በመሆኑ ለአዳዲስ ስራ ተቋራጮች መፍራት፣ የተወዳዳሪነት አቅምን በሚያጎለብት መንገድ መስፈርቶቹን በማሻሻል መፈጸም፣

በአጠቃላይ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ወሳኝ የሆነው የሥራ ተቋራጭ ማስፈፀም አቅም ለማሳደግ በአመለካከቱ፣ በምርታማነቱ፣ በአደረጃጀቱና በአመራሩ የተለወጠ ሥራ ተቋራጭ ማፍራት ቀዳሚ ሥራ ይሆናል፡፡

## 4. አማካሪ ድርጅት አቅም ግንባታ፣

በሀገራችን የተፈጠረውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዕድገት ተከትሎ ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ የሆኑ አማካሪዎች ያሉን ሲሆን እንደ ሥራ ተቋራጮች ሁሉ በርካታ ችግሮች ያሉባቸው ሲሆን ከጠራ ተልዕኮ አፈፃፀም አንፃር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ጉዳዮች ይተኮርባቸዋል፡፡

1) በመርህ ደረጃ አማካሪ ድርጅቶቻችን በሀገራችን ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ልማት አቅጣጫ ላይ ተመስርቶ ውጤታማ የሆነ አገልግሎት ሊሰጡ የሚያስችል ካባቢ በፍጥነት ለመፍጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

2) አማካሪ ድርጅቶች በዲዛይን ጥናትና ፕሮጀክት አስተዳደር አገልግሎት ረገድ ያለውን ክፍተት እንዲሞሉ ለማስቻል በመንገድ፣ በውኃ፣ በሕንፃና በሌሎች አገልግሎት ለማማከር የተመዘገቡትን አማካሪዎች የማስፈጸም አቅም መገንባት፣

3) በአማካሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ፍጥነት፣ ጥራት፣ ወጪና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የአገልግሎት አሰጣጥና ብቃት ማሳደግ፣

4) በአማካሪ ድርጅቶች በኩል የሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ በውጤትና በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ እንዲሆን በማድረግ ተጠያቂነት ያለው ስርዓት መዘርጋት፣

5) የኮንስትራክሽን የማማከር አገልግሎት ሽፋን መሠረቱ ቴክኒካዊ ቢሆንም የዲዛይን አፈፃፀም፣ የቁጥጥር አግባቡ ከራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ በመቅረጽ በዚያ ማዕቀፍ ላይ ተመስርቶ እንዲፈጸም የማድረግ ግልፅ አሰራር ማስፈን፣

6) አሁን በሥራ ላይ ያለው እና ወደ አማካሪነት ዘርፍ ለመግባት እየማለለ ያለው አካል ገና ከጅምሩ ለኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ እንዳይጋለጥ በአማካሪዎች መካከል ያለው አሰላለፍና ግብይት በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ዉድድር ላይ የተመሰረተ  እንዲሆን የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣

በአጠቃላይ የማማከር አገልግሎት አሰጣጥ በልምድ፣ ከትምህርት ቤት፣ ወይም ከሀገር ውጭ በተገኘ የዲዛይን አሠራር የተከተለ ስለሆነ በሁሉም የኮንስትራክሽን ዘርፎች በመንግስት ዕውቅና የተሰጣቸው አሰራሮችንና ማዕቀፎችን በመፍጠር ሊናበብ የሚችልና በዘርፉም ግልጸኝነትን የሚያሰፍን ሀገራዊ የአማካሪ ድርጅቶች አቅም በመፍጠር ላይ ትኩረት በመስጠት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

## 5. ኮንስትራክሽን ግብዓት አቅርቦት ሁኔታ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ግብዓት ዕጥረት ለመቅረፍ የተደረጉ ውስን ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው አቅርቦቱ በሁሉም የኮንስትራክሽን ሥራዎቻችን ማነቆ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በፍጥነት ማደግ ጋር ተያይዞ የሲሚንቶና የብረታ ብረት ውጤቶች እንዲሁም ሌሎች የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እጥረት መፈጠርና የኮንስትራክሽን ዋጋ ንረት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም የግንባታ ግብአት አቅርቦት በማሳደግ የኮንስትራክሽን ግንባታ ወጪ መቀነስ የትኩረት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፣

### 5.1 ስሚንቶን በተመለከተ

የግሉን ዘርፍ እና ሌሎች አነስተኛ እና መለስተኛ ግንባታዎች ጨምሮ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ጠቅላላ የሲሚንቶ ምርት ዕቅድ 27 ሚሊዮን ቶን እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን ነባር ፋብሪካዎች በ2002 ዓ.ም. የሚያቀርቡት የሲሚንቶ መጠን ከፍተኛው 3 ሚሊዮን ቶን ነው፡፡ በሀገራችን በሲሚንቶ ረገድ እየተደረጉ ያሉትንና መደረግ የሚገባቸውን ጥረቶች ካየን፡-

1) ነባር የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች ሙሉ አቅማቸውን ለመጠቀም የ ይል አቅርቦትንና በመስኩ የሠለጠነ ብቃት ያለው የሰው  ኃይል ማሟላት፣

2) የአገር ውስጥ የሲሚንቶ አቅርቦት እንዲሻሻል ጥረት እየተደረገ በመሆኑ በነባር፣ በማስፋፊያና በአዳዲስ የሲሚንቶ ፋባሪካዎች እስከ 2007 በጀት ዓመት በዓመታዊ የማምረት አቅም 13.23 ሚሊዮን ቶን በአገር ውስጥ ምርት ለማሟላት እንደሚቻል ይገመታል፡፡ ይህንን ለማሳካት ከፋብሪካዎቹ መጠናቀቅ ባሻገር በሚጠበቅባቸው አቅም ለማምረት የሚያስፈልጉ ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች አስተማማኝ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

3) ቀሪውን 13.77 ሚሊዮን ሲሚንቶ ፍላጎት ለማሟላት ለልማቱ በቂ ፋይናንስ ማዘጋጀት፣ ከአሁን በፊት መሬት ወስደው ወደ ኢንቨስትመንት ያልገቡ ፕሮጀክቶችን መደገፍ ካልቻሉ መሬቱን ለልማታዊ ባለሀብት ማስተላለፍ፣

4) የልማት መርሃ ግብሮቹ በሲሚንቶ እጥረት እንዳይታነቁ ፍላጎታችንን ከትክክለኛ የማምረት አቅማችን ጋር በየጊዜው በማገናዘብ የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ከውጪ በማስገባቱ አማራጭ መሸፈን ይገባል፡፡

## 5.2 የብረታ ብረት ውጤቶችን በተመለከተ

1) አርማታ ብረት አቅርቦት ረገድ በሀገር ውስጥ በግንባታው በነበረው ዕጥረት ምንም ያህል ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች ካለመኖራቸው ጋር ተያይዞ በቀጣይ አምስት ዓመት ለሚያስፈልገን የግንባታ ብረቶች ለማምረት የጥሬ ዕቃ አቅም ጠገራ ብረት ካላቸው ሃገራት በማስገባት በተፈለገው ዓይነት ለማምረት የሚያስችሉ ፋብሪካዎችና የሰው ሃይል እንዲደራጅ የመደገፍ ሥራ አንዱ ይሆናል፡፡

2) የውድቅዳቂ ብረታ ብረት የግብይት ሥርዓት ህጋዊ በማድረግ በህገወጦች ሳቢያ የሚመጡ ተጨማሪ ወጪዎችን ማስወገድ እና ለመንግስት ግብር በአግባቡ እንዲከፈል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3) በሌላ በኩል የሀገራችን የአርማታና ቱቦላሬ ብረቶች ንዑስ ክፍለ ኢንዱስትሪ የጥሬ ዕቃ ፍላጐት በአብዛኛው በውድቅዳቂ ብረታ ብረቶች (scraps) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ያሉንን ውድቅዳቂ ብረቶች በቁጠባ መጠቀማችን እንደተጠበቀ ሆኖ በውድቅዳቂ ብረት የሚመረቱ የአርማታ ብረቶች የጥራት ደረጃቸው መለስተኛ /Grade 40 ብቻ የሚያሟሉ/ ወይም ከዚያም ያነሰ በመሆኑ ፋብሪካዎቻችን የአመራረት ቴክኖሎጂ ደረጃንና የምርት ጥራት መለኪያዎችን ብቃትና ዘመናዊነትን የተላበሰ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4) በግብአት እጥረት የተነሳ የብረታ ብረት ንዑስ ክፍለ ኢንዱስትሪዎች በዓመት ከማምረት አቅማቸው ከ906 ሺ ቶን ውስጥ 40% /362 ሺቶ ቶን/ ብቻ እንደሚያመርቱ ይታወቃል፡፡ ትላልቅ ለሆኑት ግንባታዎች አቅርቦትን ለመጋራት ከሚፈለገው የብረት ፍጆታ ውስጥ ቢያንስ 50% የግንባታ ብረት ደረጃ G-60 ከፍተኛ የጥራት ደረጃ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የጥሬ ዕቃ አቅርቦታችን በጋራ ግዢ ሥርዓትና ጥብቅ የጥራት ቁጥጥር በመዘርጋት ባለሃብቶችን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡

## 5.3 የማጠናቀቂያ ዕቃዎች

### 5.3.1 የሴራሚክ ውጤቶች

1) በታቦር ሴራሚክ የፋብሪካውን ሁኔታ በመገምገም የማስፋፊያ ፕሮጀክት ወደ ተግባር ማሸጋገር፤

2) ለሴራሚክ ፋብሪካ የጥሬ ዕቃ ግኝት ባለባቸው ቦታዎች ፋብሪካውን ለማቋቋም የሚያስችል የአዋጪነት ጥናት በመንግስት ማካሄድ፤

3) ባለሀብቶችን ወደ ኢንዱስትሪው ለማስገባት በኢንዱስትሪው የገፉ ሀገሮችን በመለየት ልዩ ትኩረት በመስጠት ማፈላለግና መሳብ፤

### 5.3.2 መስታወት (Glass sheet)

ፋብሪካው ያሉበት ችግሮች እንዲቃለሉና ምርት ማምረቱን እንዲቀጥልና በገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲችል በፋብሪካው በራሱና እንዲሁም በመንግስት በኩል እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

1) በፈርነስ አይል ዋጋ መጨመር ምክንያት በፋብሪካው ላይ የደረሰውን የማምረቻ ወጪ መናር ለአጭር ጊዜ ለመቀነስ ይህ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲነሣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የፖወር ፋክተር ኮሬክተር ንዲገባለት በማድረግ የ ይል አጠቃቀምን ንዲያሻሽል ማድረግ፤

2) የአገር ውስጥ ምርትን ለማበረታታትና ለመደገፍ እንዲቻል የግንባታ ዘርፉን እንቅስቃሴ በማይጎዳ መልኩ ድርጅቱ በሚያመርታቸው ምርቶች ተመሳሳይ ከውጪ በሚገቡ ምርቶች ላይ ታክስ ወደ 35 በመቶ ከፍ እንዲል በማድረግ ድርጅቱን በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማስቻል፤

3) በአገር ውስጥ የሚመረተውን የሶዳ አሽ ምርት ለመስታወት ፋብሪካው ከጠቅላላ አቅርቦት ውስጥ 25 በመቶውን እንደያገኝ ታሳቢ ማድረግ፤

4) ፋብሪካው ለምርቱ የሚጠቀምበትን ከውጭ የሚያስገባውን ሶድየም ሠልፌት፤ ሶዳ አሽ የተባለ ግብዓትና እንዲሁም በአገር ውስጥ የማይመረቱትን የማሸጊያ ግብዓቶች ለማስገባት የሚከፈለው በታክስ ቢደገፍ፡፡

5) ፋብሪካው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ሌሎች የምርት ዓይነቶችን (በምርት ስብጥር) “Blue Sheet Glass”፣ “Brown Sheet Glass” እና “Green Sheet Glass” በማምረት በገበያ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ፤

6) ፋብሪካው አሁን ካለበት ችግር እንዲወጣ ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል ተደርጎለት ለተወዳዳሪነት ማብቃት፤

### 5.3.3 ቀለም (Paints)

የቀለም ፋብሪካ ዋና ችግር የጥሬ ዕቃ ግብአት ስለሆነ ይኸው ከሀገር ውስጥ እንዲቀርብ የሚያስችል ሥራዎች እንዲከናወኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 5.3.4 የፕላስቲክ ዉጤቶች

ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ለማቅረብ ጥረት ማድረግ፣

### 5.3.5 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች

1) የመንግስት ግዢ አካላት የረጅም ጊዜ የኮንትራት ግዢ እንዲፈፀሙ ማድረግ፣

2) ከውጪ የሚገቡ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ጥራታቸውን ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ደረጃዎችን ማዘጋጀትና ማስፈፀም፣

በአጠቃላይ የፋብሪካ ምርቶችና የጥሬ ዕቃ አቅርቦቶች ዙሪያ ከፍተኛ ርብርብና ትኩረት ከሚጠይቁት ውስጥ የወለል እና የግድግዳ ሴራሚክ፣ የኤሌክትሪክና የሳኒታሪ የፕላስቲክ ምርት ዝቅተኛ መሆን፣ ዕጥረትና ዋጋ መናር በገሀድ የሚታዩ ችግሮች ሲሆኑ እነዚህን ጉዳዮች በተከታታይነት በባለቤትነት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም፡-

1) በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ስለሚቻልባቸው ምርቶች ፋብሪካዎችን የመትከል በሙሉ አቅም ማምረት እስኪቻል አቅርቦቱ ከውጭ ሀገር የሚገባበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

2) በዋና ዋና ማጠናቀቂያ ግብአቶች በሴራሚክና ፕላስቲክ ቴክኖሎጂ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የማማከር አገልግሎት የሚሰጡባቸውን ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም የማማከር አገልግሎት የሚሰጡባቸውን ሁኔታዎችን በማመቻቸት በዘርፍ የሚሰማሩ አካላት እንዲበራከቱ በውስጣቸው ያሉ ባለሙያዎች ለምርት ዕድገት አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ማገዝ፤

3) የተገለፁትን ስትራቴጅክ ጠቀሜታ ያላቸውን የማጠናቀቂያ ግብአቶችን የሚያመርት ድርጅቶችን ለይቶ መደገፍ፤

4) ለማጠናቀቂያ ዕቃዎች ግብአት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ለማቅረብ በፍለጋ ላይ በቂ ልምድ ያላቸው የውጭና የሀገር ውስጥ የግል ድርጅቶችን በመደገፍ የተጠናከረ ጥረት ማድረግ፤

### 5.4 በአካባቢ የግንባታ ዕቃዎች (ጠጠር፣ አሸዋ፣ የድንጋይና የምርጥ አፈር)

ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ የአካባቢው ማቴሪያሎች ጠጠር፣ አሸዋ፣ የድንጋይና የምርጥ አፈር ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ የተከሠተበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በመሆኑም የአካባቢ ግብዓት የሚገኝባቸው አካባቢዎች ጥናት ማስጠናት ፕሮጀክቶቹ በሚከሔድባቸው አካባቢዎች የግብዓቶችን መገኘት በማረጋገጥና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ባለቤትና ኢንተርፕራይዝ የሚሆኑበት ሁኔታ ማመቻቸትና አጠቃላይ የአቅርቦቱን ሁኔታ በየጊዜው መፈተሽና አስተማማኝ ማድረግና በዋጋ ደረጃም ተመጣጣኝ እንዲሆን አማራጮችን ማየት ያስፈልጋል፡፡

## 6. የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አቅርቦት

ለቀልጣፋና ዉጤታማ የግንባታ ስራ ብቃት ያለዉ የኮንስትራክሽን መሳሪያ ወሳኝ ነዉ፡፡ ሆኖም ብዙዎቹ ፕሮጀክቶቻችን የአገልግሎት ዘመናቸዉን ባጠናቀቁ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የሚፈጸሙ በመሆናቸዉ ምርታማነታቸው ፈጽሞ አጥጋቢ አይደለም፡፡ በዚሁ ምክንያትም ግንባታዎች ለበርካታ መጓተቶች ይዳረጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ገበያዉ በቂ የመሳሪያ አቅርቦት የሌለዉ በመሆኑ ዘርፉ በኮንስትራክሽን መሳሪያ አቅርቦት እጥረት ተጎድቷል፡፡ በመሆኑም ይህንን ችግር ከግምት በማስገባት የመሳሪያ አቅርቦታችንን ማሳደግና ለዚሁም የሚረዱ አሰራሮችንን ዕድሎችን በስፋት መጠቀም ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

## III. በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የልማት ዕቅዳችን በኮንስትራክሽን ሴክተር የታቀዱ ፕሮግራሞችና ዋና ዋና ሥራዎች

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት መጠነ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸው የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች በሰባት የተለያዩ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ሲሆን እነዚህም የቤቶች ልማት ፣ የመንገድ ልማት ዘርፍ፣ የባቡር ኔትዎርክ ዝርጋታ፣ የስኳር ልማት/እርሻና ፋብሪካ/፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ የኮብል ስቶንና ሌሎች የከተማ መሠረተ ልማት እና የውሃና ኢነርጂ/መስኖ፣ መጠጥ ውሃና የገጠር ኢነርጂ/ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በፕሮጀክቶች የሚከናወኑ የልማት ዕቅዶችና የሚፈጠር የሥራ ዕድል ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. የመንገድ ልማት ፕሮግራም

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የመንገድ ዘርፍ የልማት ዕቅድ ዓላማ የሀገሪቱን የመንገድ አውታር ይዞታን ማሻሻል እና የመንገድ አውታርን ማስፋፋት፣ የመንገድ ኤጀንሲዎችን አቅም በማጎልበት የመንገድ አውታርን ለማሳደግና ለማሻሻል የሚያስፈልገው ውጤታማ አመራር እና የቴክኒክ ብቃት እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡ በዘርፉ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች መሠረት የአምስት አመቱ የልማት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ በዘርፉ የተጀመረውን የዋና ዋና መንገዶች ግንባታ ሥራ አጠናክሮ መቀጠል፣ የገጠር መንገድን ማሻሻልና ክረምት ከበጋ የሚሠራ መንገድ በሁሉም ቀበሌዎች እንዲዳረስ ማድረግ ነው፡፡

1) የፌዴራል መንገዶች ሥራ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት 728 ኪ.ሜ. የዋና መንገዶች ማጠናከሪያ፣ 1,089 ኪ.ሜ. የዋና መንገዶች ማሻሻል፣ 3,934 ኪ.ሜ የአገናኝ መንገዶች ማሻሻል፣ 4,331 አዲስ አገናኝ መንገዶች ግንባታ፣ 4,700 ኪ.ሜ. ወቅታዊ ጥገና በድምሩ 14,782 ኪ.ሜ. እና 84,649 ኪ.ሜ. መደበኛ ጥገና ለማከናወን ዕቅድ ተይዟል፡፡
2) በዕቅዱ ዘመን በክልል መንገዶች ባለሥልጣን መ/ቤቶች በኩል 11,212 ኪ.ሜ. የገጠር መንገዶች ግንባታ እና ጥገና ይከናወናል፡፡
3) የዩኒቨርሳል የገጠር መንገድን በተመለከተ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የመንገድ መሠረተ ልማት ኢንቨስትመንትን ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ዋና ከተማና ወደብ ያሉትን ማዕከሎች ለማገናኘት ሁሉንም ቀበሌዎች ከአቅራቢያቸው ከሚገኘው ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ ጋር ለማገናኘት እና ሌሎች ማዕከላትን በማገናኘት ላይ ያተኮረ ሥራ ይሠራል፡፡ በሁሉም ክልሎች በቀጣዮች አምስት ዓመታት በ2007 ዓ.ም ወደ 71,523 ኪ.ሜ. በማድረስ አዲስ የገጠር የመንገድ ግንባታ ሥራ ተከናውኖ ሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ደረጃውን በጠበቀና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል፡፡
4) በዕቅዱ መሠረት የኢትዮጵያ መንገድ ርዝመት በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 48,800 ኪ.ሜ. በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ /2007 ዓ.ም/ ወደ 64,522 ኪ.ሜ. ከፍ ይላል፡፡ በተለያዩ ክልሎች የዞንና ወረዳ ከተሞች ከሚገኙ የጠጠር መንገዶች ውስጥ በዕቅዱ ዘመን ከ1,000 ኪ.ሜ. በላይ ወደ አስፋልት መንገድ የማሳደግ

ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዕቅዱ የመጨሻ ዘመን /2007 ዓ.ም/ ሁሉም ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያስኬድ መንገድ የተገናኙ ይሆናሉ፡፡

የዘርፉ የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዋና ዋና ግቦች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡- የመንገድ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች**

| አመልካቾች | የበጀት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
| የፌዴራል እና የክልል የቅላላ የመንገድ ርክመት /በኪ.ሚ/ | 48800 | 51636 | 54818 | 58211 | 61771 | 64522 |
| ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የወረዳ መንገድ ርዝመት /በኪ.ሚ/ | 0 | 9568 | 24299 | 40044 | 55790 | 71522 |
| ክረምት ከበጋ በሚይስኬድ መንገድ የተገናኙ ቀበሌዎች % | 39 | 48 | 63 | 78 | 93 | 100 |
| በአገር ውስጥ ተቋራጮች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ቁጥር% | 58 | 61 | 64 | 67 | 70 | 73 |

የፌደራል እና የክልል ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የወረዳ መንገድ እና ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ ቀበሌዎችን የሚያገናኙ መንገዶች በተለይም የዩኒቨርሳል ገጠር መንገድ በአነስተኛ ተቋማት ግንባታው የሚሰራ ሆኖ በአጠቃላይ የመንገድ ልማት ዘርፉን ለማስፈፀም የሚሰማራው የሰው ኃይል በአማካይ 364,349 ይሆናል፡፡

## 2. የባቡር መሠረተ ልማት ኘሮግራም

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ከተሰጡት ትኩረቶች ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ የሥራ ዕድል ፈጣሪ እንዲሆን ማድረግና ለመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች እና ቁሣቁሶች በአገር ውስጥ እንደሚመረቱ እና በዋናነትም የኢንዱስትሪ ዘርፉ እንዲስፋፋ ማድረግ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የባቡር ትራንስፖርት የምርት ግብዓቶችንና ምርቶችን በአነስተኛ ዋጋ በአጭር ጊዜ እና በገፍ (In bulk) ለማጓጓዝ የሚያስችል ተመራጭ የትራንስፖርት መስክ በመሆኑ በሀገራችን በአምስት ዓመቱ ዕቅድ የባቡር ኔትወርክ መገንባት ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

1) ለባቡር መሠረተ ልማት ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የአነስተኛ፣ መለስተኛና ከፍተኛ የማምረቻ ተቋማትን አቅም አሟጦ መጠቀምን፣ በተለይም የአገር ውስጥ ብረታ ብረት ፋብሪካዎች /ስሊፐርስ፣ ሎኮምቲብ/ መለዋወጫዎች/ ለመስራት የሚያስችላቸው አቅም እንዲገነቡ በማድረግ በአገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለማምረት የሚያስችል አቅም እንደሚፈጠር ዕቅድ ተይዟል፡፡

2) የባቡር ትራንስፖርት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በጥልቀት በማየት ከጐረቤት አገሮችና ከአማራጭ ወደቦች የሚገናኙ የባቡር መስመሮች እንዲዘረጉ የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማዘጋጀት በዋነኛነት የሀገር ውስጥ አቅምን የመገንባትና የመጠቀም አግባብን በመከተል በተጨማሪም ከግል ባለሀብቶች /የውጭ ኩባንያዎች/ ጋር በቅንጅት መስራት የትኩረት አቅጣጫ ተደርጓል፡፡

3) የባቡር መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት ዋነኛ ማነቆ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ መሆኑ ለዚህ ዘርፍ ልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በብቃት ለማሰባሰብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓትና አቅም መገንባት የትኩረት አቅጣጫ ተደርጓል፡፡

4) በተጨማሪም ከጐረቤት አገሮች ጋር የሚያገናኘውን የባቡር መሠረተ ልማት የየሀገሮቹ መንግሥታት በተናጠል ባለቤት የሚሆኑበትና አገልግሎቱን ሁለቱ መንግሥታት በጋራ የሚያስተዳድሩበት አሠራር ለመቀየስ እንዲቻል ከፍተኛ ልምድ ባላቸው አገሮች ምርጥ ልምድ ቀስሞ ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት የተሰጠው ነው፡፡

5) በአገራችን የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታም ሆነ አገልግሎት የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል አቅጣጫን መከተል ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ ነው፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የባቡር ንዑስ ዘርፍ ዓላማ አገራዊ የባቡር ትራንስፖርት ኔትወርክ መገንባት፣ በባቡር መስክ ሀገራዊ የኢንጅነሪንግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ክህሎት እንዲፈጠርና በቀጣይነት የሀገር ውስጥ የሲቪል ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን እንዲሁም የሜታል እና ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንዱስትሪ በባቡር መስክ አቅማቸውን በማሳደግ ለሀገራዊው ባቡር ትራንስፖርት ግንባታ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው፡፡ ከፍ ብሎ የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን በዕቅዱ ዘመን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡

1. በባቡር ትራንስፖርት ግንባታ የሚሰሩ ከ40-50 የዲዛይንና የሲቪል ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እና የከተማ ቀላል ባቡር አካላት አምራችነት የተሰማሩ ከ20 በላይ የሜታል ኢንጂነሪንግ እና ኤሌክትሮ መካኒካል ኩባንያዎች ይፈጠራሉ፡፡
2. በሶስት ኮሪደሮችና በአምስት መስመሮች በጠቅላላው የ2395 ኪሎ ሜትር ሀገራዊ የባቡር ኔትወርክ ግንባታ /አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ደወሌ 656 ኪ.ሜ.፣ አዋሽ፣ ወልዲያ፣ መቀሌ 556.2 ኪ.ሜ.፣ ወልዲያ፣ ሰመራ፣ ጋላፊ 256.4 ኪ.ሜ. እና አዲስ አበባ፣ ኢጃጂ፣ጅማ፣በደሌ 339.3 ኪ.ሜ.፣ሞጆ፣ኮንሶ፣ወይጦ 587 ኪ.ሜ./ ይጠናቀቃል፡፡
3. በአዲስ አበባ ከተማ ከምሥራቅ ምዕራብና ከሰሜን ደቡብ ባለ ሁለት ኮሪደሮች 34 ኪ.ሜ. ቀላል ባቡር (LRT) ግንባታ ይጠናቀቃል፡፡
4. በመሆኑም በባቡር ኔትወርክ ልማት ዘርፍ የተቀመጡት ግቦች ለማስፈፀም የሚሰማራው የሰው ኃይል በዓመት በአማካይ 359,250 ይሆናል፡፡

## 3. የስኳር ልማት ዘርፍ ፕሮግራም

የስኳርና ተንዳኝ ምርቶች ኢንዱስትሪ የአገሪቱን የስኳር ፍላጐትና አቅርቦት መሸፈን በማረጋገጥና በአገሪቱ የስኳር ተንዳኝ ምርቶችን በማሳደግ የኃይል አቅርቦትን በመደገፍና ቁልፍ የኢኮኖሚ አገልግሎት ላላቸው ተግባራት ማዋል የስኳር ንዑስ ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት እንዲያበረክት ከሚጠበቅበት አስተዋፅኦ አንዱ ነው፡፡ ለዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የስኳር ኢንዱስትሪ በአገሪቱ የውጪ ንግድ ገቢ ያለውን ድርሻ ማሳደግ፣

የስኳር ልማት ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍን ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች ለመፈፀም የሚያስችል የሰው ኃይል ልማት፣ የምርምርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚያደርግ ተቋማዊ ብቃት መፍጠር ሌላው ይሆናል፡፡

የንዑስ ኢንዱስትሪው የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ግቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1) በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የስኳር ምርትን 2.25 ሚሊዮን ቶን ማድረስ ፣ ዓመታዊ የኢታኖል ምርቱን 304,000 ሜ$^3$ ማድረስ፣ እንዲሁም 607 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማምረት፣

2) ተጨማሪ 200,000 ሄክታር የአገዳ ልማት ማካሄድ፣

3) በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ እስከ 623,000 ቶን ጥሬ ስኳር እና 623,000 ቶን ነጭ ስኳር በድምሩ 1,246,000 ቶን ስኳር ኤክስፖርት በማድረግ 661.7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ ማስገኘት፣

4) ምርታማነትን በማሻሻል በሄክታር የሚገኘውን ምርት በ2007 ወደ 155 ቶን ማሳደግ፣

5) በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ከ200ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር፣

የስኳር ልማት ፕሮጀክቶቹ ከዚህ ቀደም ከተጀመሩት ከተንዳሆ 50 ሺ፣ ፊንጫኣ 8,500፣ ከሰም 13ሺ፣ ደቡብ ኦሞ ኩራዝ 150ሺ፣ በለስ 50ሺ እና ወልቃይት 25ሺ፣ ሄክታር የእርሻ ልማት ያካተቱ ናቸው፡፡

የስኳር ልማቱ. በግንባታ ወቅትም ሆነ ፋብሪካዎቹ ተጠናቅቀው ሥራ ሲጀምሩ የሚኖረው የስራ ዕድል በአማካይ 62,478 እንደሚሆን በዕቅድ ተይዟል፡፡

## 4. የማዳበሪያ ፋብሪካ ልማት ኘሮግራም

በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን የማዳበሪያ ፋብሪካ መገንባት ለምንከተለው ግብርና መር ኢንዳስትሪ ልማት የፋብሪካው ግንባታ የኢንዱስትሪው አካል ከመሆኑ ባሻገር ለግብርናው እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የማዳበሪያ ምርት አቅርቦት ከውጭ ማስገባት ብቻ እያደገ ከመጣው የሕዝብ ቁጥር እና የእህል ምርት ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ በሀገር ውስጥ ማምረት የምግብ እህል አቅርቦትን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ማዳበሪያ ፋብሪካ መገንባት የውጭ ምንዛሪ ከማዳንና የሀገራችንን ተወዳዳሪነት ከማሻሻሉ በተጨማሪ ለከሰል ማዕድን ኃይል ማመንጨት ተጓዳኝ ጥቅምና ወደ ዘርፉ ለመግባት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ይሆናል፡፡

የከሰል፣ ማዳበሪያና የኃይል ምርት ፕሮጀክት አቅም በ2007 እ.ኤ.አ የመስከረም ወር ጥናት እንደሚያመለክተው የሚተከለው ፋብሪካ አቅም ከ200—300 ኪሎ ቶን በዓመት እንደሆነና ይህም የሀገሪቱን የግብርና ምርት እድገት ፍላጎት ለማሟላት የ300 ኪሎ ቶን በዓመት ማዳበሪያ ፍላጎት ትንበያን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ የማዳበሪያ ፋብሪካ ልማት፡-

1) የማዳበሪያ ፋብሪካ መቋቋም 2308 ሠራተኞችን የሚቀጥርና በቀጣይ ተጨማሪ የስራ ዕድሎች በዘርፉ ተዛማጅ ልማቶች የሚፈጠር ይሆናል፡፡

2) የፋብሪካውና የአስተዳደር ቢሮዎች ግንባታ ሳይት አቀማመጥ የማዕድን ልማት መስፈርቶችን የሚያሟሉ፣ ለማዳበሪያ ማሽነሪዎች የሥራ ፍሰት፣ ለውስጥና ውጭ እንቅስቃሴ፣ ለተለያዩ የሙያ ስራዎች ቅንጅት መፈጠርና መሳለጥ የተመቻቸ ይሆናል፡፡

3) የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ህንጻዎች ግንባታ በብረት ኮንክሪት ውቅር፣ ሌሎች መለስተኛ የኢንዱስትሪ ህንጻዎችና ማከማቻዎች በብረት ውቅር ብቻ የሚገነቡ እንደሆነና ጠቅላላ የግንባታ ወለል ስፋት 11710 ሜ.ካ መሆኑ ተቀምጧል፡፡

4) 16192 ሜ.ካ የወለል ስፋት የሚይዘው የአስተዳደርና የተለያዩ የሴክሽን ቢሮዎች ኮምፕሌክስ ህንጻ ባለአምስት ወለል የብረት ውቅር ህንጻ ሲሆን የመሠረትና የእያንዳንዱ ወለል በአርማታ ብረትና ኮንክሪት የሚገነቡ ይሆናል፡፡

5) ሌላው ለመሳሪያዎች የዘወትርና ጠቅላላ ጥገና አገልግሎት የሚሰጥ የወርክ ሾፕ ህንጻ ሲሆን የወለል ስፋቱም 1512 ሜ.ካ ይሆናል፡፡

## 5. የቤቶች ልማት ኘሮግራም

የቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች ዘርፍ የሚያካትተው በከተሞች የሚካሄደው የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ በስኳር ልማት የቤቶችና ተጓዳኝ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ ፣ የ 11 የማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ እና የ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታን ነው፡፡ በአምስት ዓመት የዕቅድ ዘመን ውስጥ፡-

1) በቤቶቹ ልማት ኘሮግራም 170 ሺ. ቤቶች የሚገነቡ ሲሆን ጠቅላላ የወለል ስፋታቸው 10.8 ሚሊዮን ሜ.ካ ሆኖ በዚህ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በአማካይ 92,430፣

2) በስኳር ልማት የቤቶች ተጓዳኝ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ ኘሮጀክት 101,022 ቤቶች የሚገነቡ ሲሆን ጠቅላላ የወለል ስፋታቸው 5,917,276 ሜ.ካሬ ሆኖ በዚህ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በአማካይ 64,860፣

3) በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ኘሮጀክት የሚገነቡ ብሎኮች ብዛት 1,251 ሲሆን ጠቅላላ የወለል ስፋታቸው 1,506,596 ሜ.ካሬ ሆኖ በዚህ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በአማካይ 25,045 ነው፡፡

4) በ11 የማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ ፕሮጀክት የሚገነቡ ቤቶች ብዛት 15 ሺህ ሲሆን ጠቅላላ የወለል ስፋታቸው 904,500 ሜ.ካሬ ሆኖ በዚህ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በአማካይ 10,600 ነው፡፡

5) በአጠቃላይ በሦስቱ የቤቶች ልማት የኘሮጀክት ዓይነቶች የሚገነባው ጠቅላላ የወለል ስፋት 19,128,372 ካ.ሜ. ሲሆን፣ በዚህም የሚፈጠረው ጠቅላላ የሥራ ዕድል 172,454 ይሆናል፡፡

### 5.1 የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ኘሮግራም በአገሪቱ ከተሞች የሚታየውን ሥራ አጥነትና የመጠለያ እጥረት መቅረፍ፣ የከተማውን ነዋሪ የቁጠባ ባህል በማዳበር የቤት ባለቤትነትን ማረጋገጥ፣ የኮንስትራክሽን

ኢንዱስትሪውን አቅም ማጐልበት እና የከተሞች ያረጁ አካባቢዎች ማደስና መልሶ ማልማት ዓላማ ያደረገ ኘሮግራም ነው፡፡ በአጠቃላይ፡-

1) የቤት ልማትን በተመለከተ የከተማ አስተዳደሮች ለቤት ልማቱ የሚሆን መሬትና መሠረተ ልማት ማቅረብ፣ ያረጁ ቤቶችና አካባቢዎች በባለንብረቶች እንዲሻሻሉና እንዲታደሱ የአካባቢውን መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ለማሻሻል እገዛ መስጠት፣ የከተማ አስተዳደርና የክልል መንግሥታት ገንዘብ መድበው ወጪ ቆጣቢና ከኑዋሪው ህብረተሰብ አቅም ጋር የሚመጣጠኑ ቤቶችን በመገንባት በረጅም ጊዜ ክፍያ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የቤት ባለቤት እንዲሆኑ እና በከተማ አስተዳደሮችና በማህበራት የሚከናወኑና በመኖሪያ ቤት ቁጠባ ፕሮግራም የሚገነቡ ቤቶች ያረጁ አካባቢዎችን እየተካ የሚያድስና ከተማን የሚያሻሽል እንዲሆን ማድረግ ፣

2) የቤቶች ልማት ዓላማ በከተሞች ደረጃውን የጠበቀና ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የሚመጥን የቤት ልማት ሥራ በማከናወን የከተማ መተፋፈግንና እርጅናን ማስወገድ፣ የመጠለያ ችግርን መቅረፍ፣ የቁጠባ ባህልን ማዳበርና የሥራ ዕድልን መፍጠር፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ የከተማ መሠረተ-ልማት ዘላቂነት ባለው መልኩ ለከተማ ነዋሪዎች ማቅረብ፣

3) ለሥራና ለመኖሪያ ተስማሚ የሆነ ንጹህ የከተማ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፣ በመሠረተ-ልማት ግንባታና አስተዳደር የሰው ጉልበትን በስፋት በመጠቀም ሥራ አጥነትንና ድህነትን በመቀነስ የከተማ ነዋሪውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ሥራዎች የጥራት ደረጃውን ተጠብቀው እንዲከናወኑ ማድረግ፣ ኢንዱስትሪው ለሥራ ዕድል መስፋፋት የጎላ ሚና እንዲጫወትና የአገር ውስጥ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና አቅራቢዎች እንዲስፋፉና አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡

## 5.2 የስኳር ልማት ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት

የስኳር ልማት የነባር የስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፋት እና የአዳዲስ ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ነባር የስኳር ፋብሪካዎች የወንጂ ሸዋ፣ መተሃራ፣ ፊንጫኣ የማስፋፊያ ፕሮጀክት እና ገና ወደ ምርት ያልገባ ቢሆንም በግንባታ ሂደት ላይ ያለው የተንዳሆ ፕሮጀክትን ያካትታል፡፡

1) በተንዳሆ ስኳር ልማት 9,000 የመኖሪያ እና 200 መኖሪያ ያልሆኑ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በመንባት ላይ ያሉና በ5 ዓመቱ የዕቅድ ዘመን ውስጥ የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡

2) በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሚሽን ዕቅድ ተግባራዊ የሚደረጉ የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት የሚካሄድባቸው የ4ቱ አዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችና ደቡብ ኦሞ/ኩራዝ/፣ ከሰም፣ ጣና በለስ እና ወልቃይት ናቸው፡፡ ለእነዚህም 36489 የመኖሪያና ተጓዳኝ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ይገነባሉ፡፡

### 5.3 የ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት

የሀገራችንን ልማት ለማፋጠንና ቀጣይነቱንም ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በብቃት ለማፍራት እንዲቻል መንግሥት ለከፍተኛ ትምህርት መስፋፋትና መጠናከር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና አቅምን ለማሳደግና የተቋማቱን ሥርጭት ፍትሃዊ ለማድረግ፡-

1) 10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎችን በተለያዩ ክልሎች ለማቋቋም የግንባታ ፕሮጀክቶቹ የተጀመሩ ሲሆን ይኸውም አምቦ፣ መቱ፣ ቡሌ ሆራ፣ ወልዲያ፣ ደብረታቦር፣ ሆሣዕና፣ ወልቂጤ፣ አዲግራት፣ አሶሳ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎችን ያካትታል፡፡
2) የግንባታ ፕሮጀክቶቹም ከቤቶች ልማት ፕሮግራም ጋር በማስተሳሰር የሚፈፀም በመሆኑ ባለቤት በመሆን የግንባታ ግብዓት በማሟላትና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሰማራት ፕሮጀክቶቹን የሚያስፈፅሙ ሆኖ፣ የከተማ ቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ የየራሳቸው አማካሪና ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ክልሎች በጋራ በመሆን የተሻለ ብቃት ያላቸውን ሥራ ተቋራጮች በመምረጥ የማሰማራት አሠራር ተዘርግቷል፡፡

### 5.4. የማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች ግንባታ

የሀገሪቱን የማዳበሪያ ፍላጐት በሀገር ውስጥ ለማሟላት እንዲቻል ከከሰልና ማዳበሪያ የኃይል ምርት ፕሮጀክት እንደሚያሣየው የሀገሪቱን የግብርና ምርት ዕድገት ተከትሎ ፍላጐቱን ለማሟላት በኦሮሚያ ክልል ኢሊባቦር አካባቢ የከሠል ማዕድን ማምረቻ ፋብሪካ እንዲሁም በአቅራቢያው የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የማዳበሪያ ፋብሪካ ልማቱን በተጠናከረ መልክ ለማስፋፋት፣

1) በተለያዩ ክልሎች እስከ 15 ሺ ቤቶች የሚደርሱ የማዳበሪያ ፋብሪካዎች የሚገነቡ ሲሆን በፋብሪካዎች ለሚሠሩ ነዋሪዎች የሚሆኑ የመኖሪያ ቤቶች እና ተጓዳኝ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ይገነባሉ፡፡
2) በቤቶቹ ግንባታ 130 አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች 7 አማካሪዎች እና 65 ሥራ ተቋራጮች የሚሣተፉ ሲሆን 10,600 የሥራ ዕድል የሚፈጠር ይሆናል፡፡

## 6. የውሃ ልማት ኘሮግራም

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በውኃና ኢነርጂ ልማት ዘርፍ የተካተቱት ኘሮጀክቶች የመስኖ ልማት፣ የመጠጥ ውኃ እና የገጠር ኢነርጂ ናቸው፡፡

### 6.1 የመጠጥ ውኃ አገልግሎት

በቀጣይ አምስት ዓመታት ዕቅድ ግብ የተጣለ ሲሆን በዚህም መሠረት፡-

1) የከተማውን ንጹህና ደህንነቱ የተጠበቀ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን አሁን ካለበት 91.5 በመቶ ወደ 100%፣

2) የገጠር ንጹህና ደህንነቱ የተጠበቀ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን አሁን ካለበት 65.8 በመቶ ወደ 100% በማድረስ፣

3) አጠቃላይ የሀገሪቱን ንጹህና ደህንነቱ የተጠበቀ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን አሁን ካለበት 68.5 በመቶ ወደ 100% በማድረስ፣

ይህንንም ግብ ከዳር ለማድረስ በገጠር በአምስት ዓመቱ በአጠቃላይ 93,827 የውኃ ተቋማት ለመገንባት የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በቤተሰብ ደረጃ የሚገነቡ 25,219 የውኃ ተቋማት በውጪ 68,608 የውኃ ተቋማት ግንባታ ማካሄድ፣ በከተማ 387 አዲስ የውኃ ተቋማት ግንባታ፣ 128 የውኃ ተቋማት ጥገናና ማስፋፋት፣ 378 ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ ኘሮግራሙ ሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ሁሉም ወረዳዎችና ሁሉም ከተሞች ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሥራዎች በአራት ዋና ዋና አካላት፡- ሥራ ተቋራጮች፣ ጥቃ/አነ/ተቋማት፣ አማካሪዎች እና ቋሚ ሠራተኞች አማካኝነት ይተገበራሉ፡፡ በመሆኑም የከተሞችና የገጠር ውኃ ተቋማት አዲስ ግንባታ እንዲሁም ጥገናና ለማስፋፋት 1,923 አርቲዝያን ለእጅ ጉድጓድና ምንጭ ማጎልበት ሥራዎች፣ 2,439 የሥራ ተቋራጮች ለመለስተኛ ጥ/ጉድጓድ፣ ጥ/ጉድጓድ፣ RPS ከምንጭ፣ RPS ለብዙ መንደሮች እና የከተማ መጠጥ ውኃ ግንባታ ለማከናወን እንዲሁም 117 ለከተማና ለገጠር መጠጥ ውኃ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ያስፈልጋሉ፡፡

1) አነስተኛ የገጠር መስመር ዝርጋታዎች (RPS) እና ብዙ ሕዝብ ተጠቃሚ የሚያደርግ የገጠር መስመር ዝርጋታ (Multi Village RPS) ደረጃ ሶስትና አራት ባላቸው ኮንትራክተሮች ይሰራል፤

2) የከተማ መጠጥ ውኃ ኘሮጀክቶች ደረጃ አንድና ሁለት ባላቸው ኮንትራክተሮች እንደሚሰራ ታሳቢ ተደርጓል፤

3) የገጠር መጠጥ ውኃ ኘሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ማለትም RPS እና Multi Village RPS በኮንሰልታንቶች የሚሠራ ሲሆን ሌሎች ሥራዎች ግን በራስ አቅም /በሴክተሩ/ እንደሚሠራ ታሳቢ ተደርጓል፤

4) የከተማ መጠጥ ውኃ ኘሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን በኮንሰልታንቶች እንደሚሠራ ታሳቢ ተደርጓል፤

በኦኘሬሽንና ጥገና ወቅት የሚያስፈልግ የሰው ኃይል በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ የሚከናወኑ ትላልቅ የውኃ ተቋማት ብዛት 20,899 በመሆናቸው በእነዚሁ የውኃ ተቋማት የማስተዳደርና ቀላል ጥገናዎችን የማከናወን ሥራ የሚያካሄዱ በተቋም ቢያንስ አንድ የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያ ታሳቢ በማድረግ በጠቅላላው 20,899 ባለሙያዎች እና 26,905 የጉልበት ሠራተኞች በድምሩ 47,804 የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

## 6.2 የመስኖ ልማት

በሚቀጥሉት የአምስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን የመካከለኛ እና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ግቦች እንደሚከተለው ተጥሏል፡፡

1) የመስኖ ግንባታው ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል አሁን ያለውን 462,114 ሄክታር ለመስኖ ግንባታ ዝግጁ የሆነ ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን በእቅድ ዘመኑ ወደ 1,208,448 ሄ/ር ማድረስ፣

2) የለማውን 127,242.6 ሂ/ር የመካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ እርሻ ይዞታ በዕቅድ ዘመኑ ወደ 785,582.6 ሂ/ር ማድረስ /ከዚሁ ውስጥ 200,000 ሂ/ር ለስኳር ልማት የታቀደ ነው/፣

3) ለ5570 ሄ/ር ከፍተኛና መካከለኛ የመስኖ እርሻዎች /ከክልሎች በተገኘው መረጃ መሠረት/ የመልሶ ማቋቋምና የማስፋፊያ ሥራ መስራት የመስኖ ልማት ዕቅዶች ናቸው፡፡

4) የመስኖ ግንባታውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል አስራ አምስት መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን ማከናወን፣ በዚህም ሶስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ አሥራ ሶስት ሄክታር መሬት ለመስኖ ግንባታ ዝግጁ ይሆናል፡፡

5) በአጠቃላይ በግንባታ ወቅት ለሚቀጥሉት 5 ዓመታት 115,961 ለሚሆኑ የሰው ኃይል የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ፕሮፌሽናሉ (10+3 እና ከዚህ በላይ) 12,422 ነው፡፡ በተጨማሪም የጥናትና ዲዛይኑን ሥራ ለማከናወን ለ238 መካከለኛና ሰፋፊ ፕሮጀክቶች ለአንድ ፕሮጀክት አንድ አማካሪ እንደሚያስፈልግ ታሳቢ በማድረግ 238 የአገር ውስጥና የውጭ አገር አማካሪዎች እንደሚያስፈልጉ ይገመታል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ለ35 ሰፋፊ ፕሮጀክቶች 35 ደረጃ 1 አማካሪዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን ቀሪዎቹ በደረጃ 2 የሚመደቡ ናቸው፡፡

የልማት ዕቅዱ ዘመን የመስኖ ልማት ዋና ዋና ግቦች ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ፡- 2 አጠቃላይ የሀገሪቱ የመካከለኛ እና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ግቦች በሄክታር፣**

| የሥራው ዓይነት | ዓመታዊ ግብ | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 | |
| የመካከለኛና የሰፋፊ የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ | 244,321 | 168,212 | 146,951 | 113,053 | 73,798 | **746,335** |
| የመካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ልማት ግንባታ፣ | 115,566 | 100,234 | 101,354 | 71,400 | 69,789 | **458,343** |
| የመካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ መልሶ ማቋቋምና ማስፋፊያ | 2,060 | 1,510 | 1,000 | 1,000 | 1,000 | **5,570** |
| **ድምር** | **363,950** | **271,960** | **251,310** | **187,459** | **146,594** | **1,204,248** |

እንዲሁም ለ247 መካከለኛና ሰፋፊ የግንባታ ፕሮጀክቶች 247 ተቋራጮች ያስፈልጋሉ፡፡ ይህም የተሰላው ለአንድ ፕሮጀክት አንድ ተቋራጭ እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ለ35

ሰፋፊ ኘሮጀክቶች 35 ደረጃ-1 ተቋራጮች የሚያስፈልጉ ሲሆን ቀሪዎቹ ደረጃ-2 የሚመደቡ ናቸው፡፡ ለአነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶችን በተመለከተ በግንባታ ወቅት ለ100 ሄክታር አንድ /1/ በአነስተኛና በጥቃቅን ድርጅት ሥር የሚመደብ ተቋም ያስፈልጋል በሚል ታሳቢ በአጠቃላይ ለ4,584 ተቋማት የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል፡፡ በኦፕሬሽን ወቅት የአነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች ሚና ይኖራቸዋል፡፡

## 7. የኢነርጂ አቅርቦት ልማት ኘሮግራም

በቀጣይ አምስት ዓመታት ከ8000-10000 ሜዋ የኃይል ማመንጨት አቅምን መፍጠር በተጣለው ግብ፡-

1) ከውሃ ኃይል ማመንጫ 4993 ሜዋና 22000 ጌዋሰ አቅም ያላቸው ኃይል ማመንጫዎችን ገንብቶ ማጠናቀቅ፤
2) ከንፋስ ኃይል ማመንጫ 764 ሜዋና 2988 ጌዋሰ አቅም ያላቸው ኃይል ማመንጫዎችን ገንብቶ ማጠናቀቅ፤
3) ከጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ 75 ሜዋና 526 ጌዋሰ አቅም ያለው ኃይል ማመንጫ ገንብቶ ማጠናቀቅ፤
4) ከውሃ ኃይል ማመንጫ 8,602 ሜዋና 43,363 ጌዋሰ አቅም ያላቸው ኃይል ማመንጫዎችን ጥናት አጠናቆ ግንባታ መጀመር፤
5) ከጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ 375 ሜዋና 2,589 ጌዋሰ አቅም ያላቸው ኃይል ማመንጫዎችን ጥናት አጠናቆ ግንባታ መጀመር፤
6) የንፋስ ካርታው በሚያሳይባቸው ቦታዎች በሙሉ ጥናት በማጥናት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ማስተር ፕላን እንዲኖር ማድረግ፤
7) የማመንጫ ሥራዎችን ሊሠራ የሚችል ዲዛይን የመሥራትና የመገምግ አቅም ያለው የኢንጂነሪንግ ቡድን መፍጠር፤

በቀጣይ አምስት ዓመታት ከ6,000 ኪሜ በላይ የማስተላለፊያ መስመር መገንባት በተመለከተ፡-

1) በመገንባት ላይ ያሉትን 2224 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ግንባታ ማጠናቀቅ
2) በአጠቃላይ 6,035 ኪሜ መስመር ተገንብቶ የሚጠናቀቅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ባለ 500 ኪ.ቮ 434 ኪሜ፣ ባለ 400 ኪቮ 945፣ 3,387 ኪሜ ባለ 230 ኪቮና ባለ 132 ኪቮ 1,269 ኪሜ ተገንብቶ ይጠናቀቃል፡፡
3) ጥናታቸውን በማጠናቀቅ አዳዲስ የማስተላለፊያ መስመሮችን ግንባታ በመጀመር በቀጣይ የልማት ዘመን እንዲጠናቀቁ ማድረግ፤
4) በሲስተም መስፋፋት ምክንያት የተጨናነቁትን የማስተላለፊያና ማከፋፈያ መስመሮችና ጣቢያዎች ዕድገቱን ተከትሎ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ማከናወን፤
5) የ22 ማከፋፈያ ጣቢያዎችን የመልሶ ግንባታ ሥራ ማከናወን፤

የዲስትሪቢዩሽን ሲስተምን የማስፋፋት ሥራ ከብክነት የጸዳ እንዲሆን ማድረግ

1) 132,000 ኪ.ሜ የዲስትሪቢዩሽን መስመር መዘርጋት፤

2) 8130 ኪ.ሜ የዲስትሪቢዩሽን መስመር የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፤

3) 153 ኪ.ሜ የዲስትሪቢዩሽን ሲስተምን በመሬት ውስጥ እንዲያልፍ ማድረግ፤

አዲስ ደንበኛ ማገናኘት፣ የኤሌክትሪክ አክሰስን ከፍ ማድረግና የኤሌክትሪክ የሚያገኙ ከተሞች

1) የኃይል አቅርቦትን በተከተለ መልኩ የደንበኞችን ቁጥር አሁን ካለበት 2 ሚሊዮን ወደ 4 ሚሊዮን ከፍ ማድረግ፤

2) በቀጣይ አምስት ዓመታት አሁን ካለበት 41 በመቶ አክሰስ በመነሳት 100 በመቶ ማድረስ፤

3) በቀጣይ አምስት ዓመታት ለሁሉም ከተሞችና መንደሮች አክሰስ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

የኃይል ብክነትን ከ 15.66 በመቶ ወደ 8.6 በመቶ ዝቅ ማድረግ

1) የኃይል ማስተላለፊያ የኃይል ብክነትን በአምስት ዓመታት ውስጥ አሁን ካለበት 5.34 በመቶ ወደ 3 በመቶ ዝቅ ማድረግ፤

2) የኃይል ማሰራጫን የኃይል ብክነትን በአምስት ዓመታት ውስጥ አሁን ካለበት 11.5 በመቶ ወደ 5.6 በመቶ ዝቅ ማድረግ፤

3) የኃይል ብክነትን ለመከላከል እንዲቻል ያለውን የሕግ ክፍተት በመርመር መፍትሄ መፈለግ፤

4) ብክነትን በመቀነስ ከለተሳካላቸው አገሮች ጋር በጋራ በመሥራት የኃይል ብክነት እንዲቀንስ የማድረግ ጥረትን ማጠናከር ናቸው።

በመሆኑም በኤሌክትሪክ ኃይል ዘርፍ ፕሮጀክቶች የተቀመጡትን ግቦች ለማስፈፀም የሚሰማራው የሰው ኃይል በዓመት በአማካይ 118,241 ይሆናል።

# 8. የኮብል ስቶን እና የከተማ መሠረተ ልማት ፕሮግራም

## 8.1 የኮብል ስቶን መንገዶች ግንባታ

በከተሞች መልካም አስተዳደርና ልማት በማስፈን፣ ለኑሮና ለሥራ ምቹ እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪ ከተሞች ለመፍጠር ከተያዙ ኘሮግራሞች ውስጥ የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ኘሮግራም አንዱ ነው። የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ኘሮግራም አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች 18 ከተሞች እየተፈጸመ የሚገኝ ሆኖ፣ ዋና ዓላማው በከተሞች የማስፈጸም አቅምን መሠረት በማድረግ ለነዋሪዎቻቸው በቂ የመሠረተ ልማት አገልግሎት ለማቅረብ፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት እና መልካም አስተዳደር ኘሮግራሞች በዘላቂነትና ፍትሀዊነት ለማስፈጸም የማያስችል አቅም እንዲፈጥሩ ማድረግ ሲሆን የከተማ መሠረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን የማሣደግ እና በከተሞች የሥራ እድል የመፍጠር ከሌሎቹ ዝርዝር ዓላማዎች መካከል የሚገኙ ናቸው።

1) በከተሞች የመሠረተ ልማትን በተመለከተ ፈጣንና ፍትሐዊ ልማትን ማረጋገጥ፣ ከተሞች ለኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ያላቸውን ሚና መሠረት በማድረግ መሠረተ ልማት መዘርጋት፣ መሠረተ ልማት የማስፋፋቱ ሥራ በመንግሥት፣ በባለሀብቱና በሕዝብ ቅንጅት እንዲፈፀም ማድረግ እና በከተሞች የሚገነቡ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ሰፊ የሥራ ዕድልና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በሚፈጥር መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2) የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ዓይነቶች በተመለከተ በከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ኘሮግራም ውስጥ ከተሞች የታቀደውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለመፈጸም የሚያስችል ዓቅም እንዲኖራቸውና በከተሞች የሥራ አጥ ቁጥር በመቀነስ በኩል ጉልህ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉና በየአካባቢው ያለውን የግንባታ እቃዎች መጠቀም የሚያስችሉ ኘሮጀክቶችን ግብዓት በማድረግ መፈጸም እንደዋነኛ ዓላማቸው አድርገው ይዘዋል፡፡

3) የኮብልስቶን መንገድ ስራ ለሀገራችን አዲስ ቢሆንም በሌሎች ሀገሮች አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ረዥም የሚባል ጊዜ ያለው ሲሆን እንደማንኛውም አስፋልት መንገድ ሙሉ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ የግንባታ ሂደቱ ከአስፋል መንገድ የሚለየው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የአስፋልት ማሽነሪዎችን እና የውጭ ምንዛሬ የሚጠይቁ ሌሎች የአስፋልት ግብዓቶችን ሳይጠይቅ የአጭር ጊዜ ስልጠና በወሰዱ ስራ አጥ ወገኖቻችን የሚከናወን መሆኑ ነው፡፡

4) በተመሳሳይ ሁኔታ ለግንባታው የሚያስፈልገው ግብዓትም በአካባቢ የሚመረትና አስተዳደሩም በቀላሉ በአካባቢ አቅም የሚመራ ሲሆን የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ጥገናም በአነስተኛ ወጪና ጉልበት በቀላሉ የሚከናወን በመሆኑ እጅግ ተመራጭ ነው፡፡

5) እንደሚታወቀው በከተሞች የመንገድ ጥያቄ ሰፊ በመሆኑ ይህ ስራ ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር የስራ አጥ ዜጎችን ቁጥር በመቀነስና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ያለው አስተዋጽዖ የጎላ ነው፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከታየው ልምድ የኮብልስቶን መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የሥራ ዕድል በመፍጠር በኩል ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ ሲሆን በዚህ ዘርፍ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በአማካይ 51,128 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

## 8.2 ሌሎች የከተማ መሰረተ ልማት ሥራዎች

በዚህ ፕሮግራም ከኮብልስቶን በተጨማሪ ሌሎች የመሰረተ ልማት ፕሮግራሞች የሚከናወኑ ሲሆን ከነዚህ መካከል የጠጠር መንገዶችና የእግረኛ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የጐርፍ ፍሳሽ ማስወገጃ ድሬኔጅ ግንባታዎች፣ የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ተቋማት፣ የከተማ ገበያ ማሻሻያ ግንባታዎች፣ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች ግንባታ፣ ድልድዮች፣ ካልቨርቶችና አነስተኛ ፉካዎች ግንባታ ኘሮጀክቶች፣ የጋራ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታና የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት ኘሮጀክቶችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡

1) የእነዚህ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችም የአካባቢ ማቴሪያልን መሰረት ባደረገና ሰፊ የሰው ጉልበት ባሳተፈ መልኩ እንደሚሰሩ ታሳቢ በማድረግ በተለይም ብዙዎቹ ስራዎች በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሚከናወኑ ሲሆኑ በዚህ ምክንያት ከኮብልስቶን ውጭ ባሉ ከላይ በተጠቀሱት ሌሎች የመሰረተልማት ፕሮጀክቶች በስራ ተቋራጮችና በሚሰሩ ግንባታዎች 91,835 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

2) 130 ከሚሆኑ አማካሪ ድርጅቶች ጋር የሚሠሩ 910 ባለሙያዎች በዚህ ፕሮግራም ይሳተፋሉ፡፡ በመሆኑም ባጠቃላይ በከተሞች የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ኘሮግራም በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በአማካይ 64,494 ሰዎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በኮብልስቶን እና በሌሎች የከተማ መሠረተ ልማት ሥራ ኘሮጀክቶች በድምሩ እና በየዓመቱ በአማካይ 120,622 የሥራ ዕድል የሚፈጠር ይሆናል፡፡

## 9. በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍላጎት

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለታቀዱ ዋና ዋና የኮንስትራክሽን ስራዎች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ስትራቴጂያዊ የሆኑ ግብዓቶችን ፍላጎት በመጠንና በዓይነት በመለየት አቅርቦቱ አስተማማኝ እንዲሆን ክትትል ይደረጋል፡፡ከዚሁ ባሻገር ዝርዝር የአፈጻጸም ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ የግብዓት ፍላጎቱ በሃገር ዉስጥ አቅም እንዲሸፈን የማድረግ አቅጣጫ መከተል ዋነኛው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት የተለዩት ዋና ዋና የግብዓቶች ፍላጎት እንደሚከተለዉ ይቀርባል፡፡

### 9.1 የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጐት

ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጐት በተመለከተ ከየሴክተር ልማቱ ፕሮግራም የተሰበሰበውን የኢንተርፕራይዞች ፍላጎት በሠንጠረዥ 3 ተመልክቷል፡፡ ሰንጠረዡም እንደሚያሳየን፡-

1) የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ፍላጐት በተለይም በከፍተኛ ደረጃ ካሉት ውስጥ ማለት ከደረጃ 1-3 በየዓመቱ በአማካይ 185 የሚሆኑ ለግንባታ ሥራ እንደሚያስፈልጉ ከዚሁ በተጨማሪ በአነስተኛ ደረጃ የሚያስፈልጉ /ደረጃ 4-7/ ሥራ ተቋራጮች ለመንገድ ልማት 877 እንዲሁም ለቤቶች ልማት 2033 በድምሩ 3362 ሥራ ተቋራጮች እንደሚያስፈልጉ ያሣያል፡፡

2) አማካሪዎችን በተመለከተ በየዘርፉ በተለይም በመንገድና በባቡር ልማት ዘርፍ ልምድ ያላቸው አማካሪዎችን ጨምሮ በየዓመቱ ከ100 ያላነሡ ከደረጃ 1-3 የሚገኙ አማካሪዎች ማሣተፍ ያስፈልጋል፡፡

3) የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጐት በመንገድ፣ በባቡር እና መስኖና ግድብ ሥራዎች በስፋት መለየትና ማጠናከር የሚያስፈልግ ሲሆን በቤቶች ልማት እና የከተሞች መሠረተ ልማት ነባር ኢንተርፕራይዞች የሚሰማሩበትን ሙያ በመለየት ማጠናከር ትኩረት የሚሻ ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ፡- 3 2003 - 2007 የሚሠማሩ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ፡ አነስተኛ፣ ኢንተርፕራይዞች ብዛት

| የፕሮጀክቱ ዘመን | የኢንተርፕራይዝ ዓይነት | | የመሠረተ ልማት ተቋማት ዝርዝር | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መንገድ | ባቡር | መስኖና ግድብ | ኃይል ማመንጫ | የቤቶች ልማት | የከተማ መ/ልማት | |
| 2003 | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 69 | 25 | 13 | 5 | 5 | | 117 |
| | | 4 - 7 | 653 | | 275 | 4 | 2855 | 255 | 4042 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 40 | 25 | 4 | 1 | 19 | 5 | 94 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 213 | | 72 | 20 | 605 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 638 | 25 | 4154 | | 5112 | 2112 | 12041 |
| 2004 | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 96 | 25 | 13 | 9 | 7 | | 150 |
| | | 4 - 7 | 885 | | 232 | 8 | 1548 | 206 | 2879 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 45 | 25 | 4 | 4 | 19 | 5 | 102 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 164 | | 72 | 20 | 556 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 855 | 475 | 4231 | | 2218 | 1339 | 9118 |
| 2005 | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 121 | 25 | 13 | 20 | 7 | | 186 |
| | | 4 - 7 | 934 | | 232 | 14 | 1726 | 209 | 3115 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 50 | 25 | 4 | 4 | 19 | 4 | 106 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 155 | | 72 | 17 | 544 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 879 | 637 | 3791 | | 2308 | 1421 | 9036 |
| 2006 | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 139 | 25 | 13 | 40 | 7 | | 224 |
| | | 4 - 7 | 949 | | 224 | 22 | 1845 | 158 | 3198 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 55 | 25 | 4 | 4 | 19 | 4 | 111 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 147 | | 72 | 16 | 535 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 879 | 800 | 3209 | | 2634 | 1422 | 8944 |
| 2007 | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 143 | 25 | 13 | 60 | 7 | | 248 |
| | | 4 - 7 | 964 | | 234 | 32 | 2193 | 154 | 3577 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 60 | 25 | 4 | 4 | 16 | 5 | 114 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 150 | | 68 | 18 | 536 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 879 | 1250 | 3028 | | 3735 | 1764 | 10656 |
| አማካይ | ሥራ ተቋራጭ | 1 - 3 | 114 | 25 | 13 | 27 | 6.6 | | 185 |
| | | 4 - 7 | 877 | | 239 | 16 | 2033 | 197 | 3362 |
| | አማካሪ | 1 - 3 | 50 | 25 | 4 | 3 | 18.4 | 5 | 105 |
| | | 4 - 7 | 300 | | 166 | | 71 | 18 | 555 |
| | አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | | 826 | 637 | 3683 | | 3201 | 1612 | 9959 |

## 9.2 የግንባታ ዕቃዎች ፍላጐት

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን የሴክተር ልማት ፕሮግራም የዋና ዋና የግንባታ ዕቃዎች ፍላጎት ዝርዝር በሰንጠረዥ 4 ተመልክቷል፡፡ ለግንባታው አቅርቦት እጅግ ወሳኝ ከሆኑት የግንባታ ዕቃ ዓይነቶች ውስጥ የሲሚንቶ እና የብረታ ብረት ፍላጎትን በተለየ ሁኔታ ማብራሪያ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡

### 9.2.1 ሲሚንቶ

1) በአምስት ዓመቱ ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገው የሲሚንቶ መጠን ሌሎች የግንባታ ግብዓት አመላካች ሲሆን የፍላጐት አማካይ ግምት 16.7 ሚሊዮን ቶን ሲሆን ይኸው 15% መጠባበቂያ ታክሎበት ለ5 ዓመቱ በመንግስት ለሚካሄዱ የኮንስትራክሽን ልማት ፕሮጀክት የሚያስፈልገው 20 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ይሆናል፡፡

2) በዚሁ መሠረት ለዋና ዋና የመንግስት የልማት ፕሮግራሞች ከአጠቃላይ የሲሚንቶ ፍጆታ 50% የግሉ ዘርፍ 30% እንዲሁም የተለያዩ የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ ፕሮጀክቶች 20% ከዚህ ቀደም ከነበራቸው አጠቃቀም በመነሣት ታሣቢ የተደረገና ለግሉ ዘርፍ በዓመት 2.5 ሚሊዮን ቶን በአምስት ዓመቱ 12.5 ሚሊዮን ቶን እንዲሁም ለተለያዩ የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ ኘሮጀክቶች ቀደም ሲል ከነበራቸው የሲሚንቶ ፍላጐት ግምት በመነሳት በአማካይ በአምስት ዓመት 7.5 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ያስፈልጋል፡፡

3) በመሆኑም የአምስት ዓመት የሲሚንቶ ፍላጐት አማካይ ግምት 40 ሚሊዮን ቶን ሲሆን ይኸውም በየዓመቱ በአማካይ 8 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ያስፈልጋል፡፡

4) በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተካተቱት የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የዓመት የሲሚንቶ ፍላጐት በየበጀት ዓመቱ ተመሣሣይና በአማካይ ቢያንስ 4 ሚሊዮን ቶን እንደሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 4 የተያያዘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 9.2.2 ብረታ ብረት

1) በሌላ በኩል አሁንም ለኘሮጀክቶቹ በአምስት ዓመቱ የሚያስፈልገው የአርማታ ብረት መጠን 1.2 ሚሊዮን ቶን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው Grade 60 የጥራት ደረጃ እንደሚኖረውና ይኸውም 600 ሺ ቶን የአርማታ ብረት እንደሚያስፈልግ በግንባታ ዕቃዎች ፍላጎት የቀረበው ሰንጠረዥ-4 ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ፡- 4 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍላጐት በኘሮጀክት ዘመን "000"**

| ተ.ቁ | የግብዓቱ ዝርዝር | መለኪያ | የመሠረተ ልማት ተቋማት ግንባታ ዝርዝር | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መንገድ | ባቡር | ኃይል ማመንጫ | የከተማ መ/ልማት | ቤቶች ልማት | ማዳበሪያ | መስኖና ግድብ | |
| 1 | ሲሚንቶ | በቶን | 3,884 | 1,100 | 5,057 | 2,800 | 3,078 | 150 | 500 | 16,849 |
| 2 | አርማታ ብረት | በቶን | 603 | 16 | 192 | 28 | 308 | 15 | 50 | 1,223 |
| 3 | አስፋልት | በቶን | 2,550 | | 4 | | | | | 2,554 |
| 4 | ፈንጂ (Explosives) | በቶን | 303 | | | | | | | 303 |
| 5 | ጠጠር | ሜ.ኩ | | 240 | | 380 | 3,720 | | 225 | 4,565 |
| 6 | አሸዋ | ሜ.ኩ | | 314 | | 485 | 4,896 | | 300 | 5,995 |
| 7 | አግሮስቶን | ቁጥር | | | | | 15,407 | | 792 | 16,199 |
| 8 | ሃዲድ | ቶን | | 190 | | | | | | 190 |
| 9 | ባላስት | ሜ.ኩ | | 1,522 | | | | | | 1,522 |
| 10 | የግንብ ድንጋይ | ሜ.ኩ | | 1,383 | | | 3,320 | | | 4,703 |
| 11 | ትራንስፎርመር (10kv - 1250 KVA) 33V | በቁጥር | | | 32 | | | | | 32 |
| 12 | ትራንፎርመር (25 KVA 1250 KVA | በቁጥር | | 2 | 48 | | | | | 65 |
| 13 | ስትራክቸራል ብረት | በቶን | 1 | | 196 | | | 10 | | 206 |
| 14 | ቆጣሪ | በቁጥር | | | | | 233 | | | 233 |
| 15 | ኤጋ ሽት | | | 985 | | | 13,500 | | | 14,485 |

## 9.3 የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ፍላጎት

በዕቅድ ዘመኑ ለተቀመጠው የፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ግብ የመሰረተ ልማትና ህንጻ ግንባታ ስራዎቻችን ፈጣን እንዲሆኑ በሚፈለገው የጥራት ደረጃና ጊዜ ማድረስ ወሳኝ ተግባር ይሆናል፡፡ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ግንባታው ሜካናይዝድ በሆነ መንገድ ሲፈጸም ስለሚሆን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችና ዕቃዎች በዚሁ ረገድ ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ የግንባታ ስራዎቻችንን ሜካናይዝድ የማድረጉ ፍላጎት ከሚኖረዉ ስራ ስፋት፣ የቴክኒክ ውስብስብነት እንዲሁም የስራ ጊዜ ሰሌዳ ለማስጠበቅ በሚደረገው ጥረት እና ይህንን ተከትሎ በሚፈጸሙ ተጨማሪ ፍላጎቶች ይወሰናል፡፡

በሌላ በኩል ያሉንን መሳሪያዎች በተደራጀ አኳኃን በማሰለፍ ስራ ላይ መዋላቸዉን ማረጋገጥ ለኢኮኖሚዉ አዋጭነት ከሚያበረክተዉ አስተዋጽኦ አንጻር ሊታይ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ የመሳሪያ ባለቤት እንዲሆን የሚያስገድድዉን አሰራር በመፈተሽ የመሳሪያ አቅርቦትና ልማት ስራ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ በአምስቱ አመት ዕቅድ በስትራቴጂካዊነቸዉ የተለዩት ልዩ ልዩ መሳሪያዎች በሚከተለዉ ታሳቢ መመራት ይገባቸዋል፡፡

1) በሁሉም የግንባታ ስራዎቻችን የሚሰማሩ የኮንስተራክሽን መሣሪያዎች በተቻለ መጠን ስታንዳርድ እንዲሆኑ ማስቻል፣
2) በተመጣጣኝ ወጪ የላቀ አገልግሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣
3) የብልሽትና የሰርቪስ ጥገና በሃገር ዉስጥ አቅም የሚከናወን ሆኖ የጥገና ጊዜዉም በአጭር ጊዜ እንዲሆን የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣
4) በሃገር ውስጥ በሚኖሩ ልዩ ልዩ የኦፐሬተር ሙያ ዘርፎች ተስማሚ እንዲሆን ማድረግና በስራ ዕድል ፈጠራ ረገድ አስተዋጽኦ ማበርከት፣
5) ከአንድ በላይ አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎችን በላቀ ደረጃ የመጠቀም አቅጣጫ መከተል፣
6) የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በመጠናቸው መካከለኛ እንዲሆኑ ማድረግ እና ተደጋጋሚ ብልሽትን ለማስወገድ በርካታ ተንቀሳቃሽ ክፍሎች ያልበዙበት እንዲሆን ማድረግ፣

   በዚህ ዕቅድ ውስጥ የሚለዩትን ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እንደየ አገግሎታቸው እንዲሁም በማናቸዉም የግንባታ ስራ ላይ በመሰረታዊነት ለማይቀሩ ስራዎች የሚያስፈልጋቸዉን መሳሪያ ዓይነት ታሳቢ ያደረገ በ7 ዋና ዋና ምድቦች /ከምድብ ሀ-ሰ/ ተለይተዉ እንዲቀመጡ የተደረገ ሲሆን በዚሁ አግባብ በየዓመቱ የሚያስፈልገውን መሳሪያ በቁጥር እና በዓይነት ተለይቶ ከሰንጠረዥ ቁጥር 5-9 ተመልክቷል፡፡

**ምድብ ሀ.** ጠጠር መፍጪያ፣ አስፋልትና የኮንክሪት ማዘጋጂያ ፕላንት /Chrusher Plant, Asphalt Hot Mix and Concrete Batch Plant/

**ምድብ ለ.** የአፈር መቆፈሪያ፣ መግፊያና የመዳጫ መሳሪያዎች /Excavating, Earthmoving and Compacting Equipment/

ምድብ ሐ. አፈር እና መሰል የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶችን ማጓጓዣ መሳሪያዎች /Hauling Equipment/

ምድብ መ. ክብደት ማንሻ መሳሪያዎች /Hoisting Equipment/

ምድብ ሠ. የኮንክሪትና የፓይል መግፊያ እና የመሬት መሰርሰሪያ መሳሪያ /Concrete Pumping, Pile Driving and Drilling Equipment/

ምድብ ረ. ጭቃ አካባቢ መቆፈሪያና ማመላለሻ መሳሪያ /Pumping, Dredging and Conveying Equipment/

ምድብ ሰ. የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶች መፈተሻ መሳሪያ /Material Testing Equipments/

ሠንጠረዥ፡- 5 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) የኮንስትራክሽን ጠጠር መፍጪያ፣ አስፋልትና የኮንክሪት ማዘጋጂያ ፕላንት ፍላጐት በፕሮጀክት ዘመን

| ተ.ቁ | የመሳሪያዎች ዓይነት | የመሣሪያዎች ፍላጐት | በሥራ ላይ ያሉ | ልዩነት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. ጠጠር መፍጪያ፣ አስፋልትና የኮንክሪት ማዘጋጂያ ፕላንት /Chrusher Plant, Asphalt Hot Mix and Concrete Batch Plant/ | | | | | | | | | |
| 1 | Hot mix plant (heavy) | 152 | 82 | 70 | - | 11 | 25 | 25 | 11 |
| 2 | Crusher heavy | 451 | 290 | 161 | - | 24 | 56 | 56 | 24 |
| 3 | Concrete batching plant (Heavy) | 82 | 7 | 75 | - | 11 | 26 | 26 | 11 |

ሠንጠረዥ፡- 6 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) የአፈር መቆፈሪያ፣ መግፊያና የመዳጫ መሳሪያዎች ፍላጐት በፕሮጀክት ዘመን

| ተ.ቁ | የመሳሪያዎች ዓይነት | የመሣሪያዎች ፍላጐት | በሥራ ላይ ያሉ | ልዩነት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለ. የአፈር መቆፈሪያ፣ መግፊያና የመዳጫ መሳሪያዎች /Excavating, Earthmoving and Compacting Equipment/ | | | | | | | | | |
| 1 | Bull Dozer (Heavy) | 1,617 | 796 | 821 | - | 123 | 287 | 287 | 123 |
| 2 | Loader (Heavy) | 1,265 | 720 | 545 | - | 82 | 191 | 191 | 82 |
| 3 | Excavator (Heavy) | 1,240 | 556 | 684 | - | 103 | 239 | 239 | 103 |
| 4 | Motor grader (Heavy) | 1,200 | 585 | 615 | - | 92 | 215 | 215 | 92 |
| 5 | Roller (different ) | 3,288 | 880 | 2,408 | - | 361 | 843 | 843 | 361 |
| 6 | Asphat distributer | 153 | 98 | 55 | - | 8 | 19 | 19 | 8 |
| 7 | Paver | 76 | 60 | 16 | - | 2 | 6 | 6 | 2 |
| 8 | Compactor | 196 | | 196 | - | 29 | 69 | 69 | 29 |
| 9 | Selt propelled Chip Spreader | 150 | 102 | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 10 | Sleeper Laying Machine | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 11 | Mechanized Sleeper Laying Machine | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 12 | Trencher | 50 | | 50 | - | 8 | 18 | 18 | 8 |
| 13 | Skidder | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 14 | Scraper | 67 | | 67 | - | 10 | 23 | 23 | 10 |

ሠንጠረዥ፡- 7 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) የአፈር እና መሰል የኮንስትራክሽን ቁሳቁሶችን ማጓጓዣ መሳሪያዎች ፍላጐት በፕሮጀክት ዘመን

| ተ.ቁ | የመሳሪያዎች ዓይነት | የመሣሪያዎች ፍላጐት | በሥራ ላይ ያሉ | ልዩነት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሐ. የአፈር እና መሰል የኮንስትራክሽን ቁሳቀቁሶችን ማጓጓዣ መሳሪያዎች /Hauling Equipment/ | | | | | | | | | |
| 1 | Water trucks | 1,407 | 568 | 839 | - | 126 | 294 | 294 | 126 |
| 2 | Damp trucks (1rucks (15m$^3$) | 8,500 | 4,500 | 4,000 | - | 1000 | 1000 | 1000 | 1000 |
| 3 | Fuel Truck | 143 | 103 | 40 | - | 6 | 14 | 14 | 6 |
| 4 | Courier Truck | 170 | 132 | 38 | - | 6 | 13 | 13 | 6 |
| 5 | Truck tractor | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 6 | Tractor with two trailers | 1,797 | | 1,797 | - | 270 | 629 | 629 | 270 |
| 7 | Truck Mounted/Mobile Truckd Workshop | 11 | | 11 | - | 2 | 4 | 4 | 2 |
| 8 | Low bed | 39 | 24 | 15 | - | 2 | 5 | 5 | 2 |
| 9 | High bed | 40 | 12 | 28 | - | 4 | 10 | 10 | 4 |
| 10 | Trailer Mounted Water tanker (3,500 1t) | 903 | | 903 | - | 135 | 316 | 316 | 135 |
| 11 | Heavy Duty Tractor (375 HP) | 16 | | 16 | - | 2 | 6 | 6 | 2 |
| 12 | Agricultural Tractor (265 hp | 12 | | 12 | - | 2 | 4 | 4 | 2 |
| 13 | Agricultural Tractor (185 hp | 12 | | 12 | - | 2 | 4 | 4 | 2 |
| 14 | Agricultural Tractor (90-105hp) | 40 | | 40 | - | 6 | 14 | 14 | 6 |
| 15 | Pavement Marking Machines | 74 | 30 | 44 | - | 7 | 15 | 15 | 7 |
| 16 | Articulated Trucks | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 17 | Asphalt Melting machine | 76 | 24 | 52 | - | 8 | 18 | 18 | 8 |
| 18 | Dumper (heavy) | 56 | | 56 | - | 8 | 20 | 20 | 8 |
| 19 | Tractor with Front End Loader (heavy) | 23 | | 23 | - | 3 | 8 | 8 | 3 |
| 20 | Concrete Mixers (>500 lt) | 1,375 | 818 | 557 | - | 84 | 195 | 195 | 84 |

ሠንጠረዥ፡- 8 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) የክብደት ማንሻ መሳሪያዎች ፍላጐት በፕሮጀክት ዘመን

| ተ.ቁ | የመሳሪያዎች ዓይነት | የመሣሪያዎች ፍላጐት | በሥራ ላይ ያሉ | ልዩነት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ. ክብደት ማንሻ መሳሪያዎች /Hoisting Equipment/ | | | | | | | | | |
| 1 | Crane | 302 | 170 | 132 | - | 20 | 46 | 46 | 20 |

ሠንጠረዥ፡- 9 በቀጣይ 5 ዓመታት (2003 - 2007ዓ.ም) የኮንክሪትና የፓይል መግፊያ እና የመሬት መሰርሰሪያ መሳሪያ ፍላጐት በፕሮጀክት ዘመን

| ተ.ቁ | የመሳሪያዎች ዓይነት | የመሣሪያዎች ፍላጐት | በሥራ ላይ ያሉ | ልዩነት | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሠ. የኮንክሪትና የፓይል መግፊያ እና የመሬት መሰርሰሪያ መሳሪያ /Concrete Pumping, Pile Driving and Drilling Equipment/ | | | | | | | | | |
| 1 | Wagon drill | 209 | 54 | 155 | - | 23 | 54 | 54 | 23 |
| 2 | Auger Drill Machine | 48 | | 48 | - | 7 | 17 | 17 | 7 |
| 3 | Rig | 30 | 10 | 20 | - | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 4 | Concrete Pumps | 196 | 92 | 104 | - | 16 | 36 | 36 | 16 |

ማሳሰቢያ፣የመሳሪያዎች ግምት በየዓመቱ በሚኖረው አፈጻጸም የሚከለስ ይሆናል፡፡

## 9.4 በኮንስትራክሽን ዘርፍ ሊፈጠር የሚችል የሥራ ዕድል ብዛት

በኮንስትራክሽን ዘርፉ በ5 ዓመታት ሰፊ የሰው ኃይል የሚያስፈልግና በተለይም ከምህንድስና እንዲሁም ተያያዥ ሙያዎች እና የጉልበት ሠራተኞች እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በሙያ ዓይነት እና በፕሮጀክት በመከፋፈል ተዘርዝሮ በሰንጠረዥ-10 ተመልክቷል፡፡

በፕሮጀክቶች ለሚሣተፉ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች አጫጭር ሥልጠናዎች በየፕሮጀክት ባለቤቶች አማካይነት በተከታታይና የሥልጠና ፓኬጅ በማዘጋጀት የሚሠጥ ሲሆን በመካከለኛ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ደግሞ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት በየእርከኑ እንዲሠለጥኑ የሚፈለገው ብዛት ተለይቶ በሰንጠረዥ-11 እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ:- 10 ከ2002 - 2007 ዓ.ም. በኮንስትራክሽን ዘርፉ በ5 ዓመታት የሚፈጠረው ሥራ ዕድል ብዛት**

| ተ.ቁ | የግብዓቱ ዝርዝር | መለኪያ | የመሰረተ ልማት ተቋማት ዝርዝር | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መንገድ | ባቡር | ኃይል ማመንጫ | ቤቶች ልማት | የከተማ መ/ልማት | ስኳር ልማት | ማዳበሪያ | መስኖና ግድብ | |
| 1 | ኢንጅነሮች | በቁጥር | 8360 | 5000 | 1074 | 2958 | 1938 | 780 | 420 | 6543 | 20530 |
| 2 | አሶሲየት ኢንጂነሮች | በቁጥር | 13268 | 25000 | 2686 | 11832 | 7750 | 8988 | 3400 | 7305 | 72924 |
| 3 | ኦፕሬተርና ቴክኒሽያን | በቁጥር | 13290 | - | 3761 | 1479 | 969 | 500 | 200 | 100 | 20299 |
| 4 | ኮንስትራክሽን/ፎርማን | በቁጥር | 3605 | - | 3223 | 20706 | 13563 | 3000 | 1800 | 437 | 45897 |
| 5 | የእጅ ሙያተኛ (ግንበኛ፣ አናጢ....) | በቁጥር | 8567 | - | 32129 | 35496 | 23251 | 7000 | 4980 | 6100 | 111423 |
| 6 | ሌሎች ልዩ /ሙያ/ (ሬድዮ ኦፕሬተር...) | በቁጥር | 7798 | - | - | 1479 | 969 | 210 | 200 | 216 | 10658 |
| 7 | የጉልበት ሰራተኞች | በቁጥር | 309461 | 329250 | 75368 | 87904 | 21056 | 42000 | 19000 | 26,905 | 884039 |
| | | ድምር | **364,349** | **359,250** | **118,241** | **161,854** | **69,496** | **62,478** | **30,000** | **47,804** | **1,264,598** |

**ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በ5 ዓመቱ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ቢታይ 1,264,598 ይሆናል፡፡**

**ሠንጠረዥ፡- 11 የፕሮጀክቶች የመካከለኛ ጊዜ የስልጠና ፍላጎት**

| ተ.ቁ | የግብዓቱ ዝርዝር | መለኪያ | የመሰረተ ልማት ተቋማት ዝርዝር | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መንገድ | ባቡር | ኃይል ማመንጫ | ስኳር ልማት | ማዳበሪያ | ቤቶች ልማት | የከተማ መ/ልማ | መስኖና ግድብ | |
| 1 | ኢንጅነሮች | በቁጥር | 3796 | 2000 | 321 | 780 | 420 | 444 | 291 | 3200 | **11252** |
| 2 | አሶሲየት /ኢን | በቁጥር | 5176 | 5000 | 538 | 8988 | 3400 | 5916 | 3875 | 3300 | **36293** |
| 3 | ኦፕሬ/ ቴክኒሽያን | በቁጥር | 9403 | - | - | 500 | 200 | 740 | 485 | 100 | **11428** |
| 4 | ኮንስ/ ፎርማን | በቁጥር | 7751 | - | - | 300 | 1800 | 3106 | 2034 | 437 | **18128** |
| | | **ድምር** | **26126** | **7000** | **859** | **13268** | **5820** | **10206** | **6685** | **7037** | **77101** |

## IV. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ዋና ዋና ጉዳዮችና የአፈፃፀም ሥልቶች

በሀገራችን በመጪው አምስት ዓመት በመንግስት ታቅደው ለሚካሄዱት የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ልማቱን ሊተገብር የሚችል ተመጣጣኝ የኮንስትራክሽን አቅም ለመፍጠር እንዲቻል ይህ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ተቀርጿል። ከነዚህ ዋና ዋና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም ከሚፈልጉ ዕቅዶች በተጨማሪ አገራዊ ሽፋን ያላቸው ነገር ግን በተናጠል ሲታዩ አነስተኛ የሚመስሉ ሌሎች የመንግሥት እና መጠነ ሰፊ የሆነ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የግንባታ ፍላጐቶች አሉ። እነዚህ ባንድነት ሲታዩ የሚፈጥሩት ጠቅላላ የግንባታ ፍላጐት የአገሪቱ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ይሆናል። በመሆኑም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪያችን በኢንዱስትሪው የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ዋና ዋና ምሰሶዎች ከሆኑት ከሰው ኃይል፣ ከአማካሪ ድርጅቶች፣ ከሥራ ተቋራጮች፣ ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት፣ ከግብዓቶች አቅርቦት እና ከአሠራር ሥርዓት አንፃር የሚታዩበትን ክፍተቶች ለማጥበብ ዋና ዋና ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት መፈጸም ያስፈልጋል።

ይህ የማስፈፀም ስትራቴጂ ኢንዱስትሪው ያሉበትን ክፍተቶች የማጥበብ አካሄድ እና ያለውን አቅም ለልማት አሟጦ መጠቀምን ጐን ለጐን በማስኬድ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን የሰው ኃይል እንዲጎለብት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በየአካባቢው እንዲፈጠር፣ የግንባታ መሣሪያዎችና ዕቃዎች እንዲቀርቡ በዋናነት በታቻለ መጠን በሀገር ውስጥ እንዲተኩ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጥ ይሆናል። በዘርፉ የልማት ሂደት ዋናው ማጠንጠኛ ጉዳይ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ ሲሆን ኢንዱስትሪዉ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በመሸፈን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማብቃት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል።

### 1. ዓላማዎችና መርሆዎች

#### 1.1 ዓላማዎች

1) በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ በሚደረጉ የተለያዩ የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ዕውን በማድረጉ ሂደት የሚሳተፉ ነባር ኢንተርፕራይዞችን የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግና አዳዲሶችንም በማቋቋም ወደ ስራ ማስገባት በዚህም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማጠናከርና መጠነ ሰፊ የሥራ ዕድል ለዜጎች መፍጠር፤
2) ከውጪ የሚገቡ የኮንስትራክሽን ግብአቶችና የመሣሪያዎች አቅርቦት በሀገር ውስጥ ምርት የሚተኩበትን ሥርዓት በመከተል የሀገር ውስጥ አቅርቦትን ማሳደግና ያለንን ውስን አቅም በላቀ ደረጃ መጠቀም፤
3) በየደረጃው የሚኖር ጠንካራ የፕሮጀክት አመራር በመፍጠር፣ ሥርዓቶችን በመፈተሽና በማሻሻል እንዲሁም በተቀናጀ ዕቅድ የባለድርሻ አካላትን ሚና በማጐልበት የመንግስት የልማት ፕሮግራሞች በጥራት፣ በተያዘላቸው መርሃ ግብሮች እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፈፀም፤

4) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን መሠረት ያደረገና የልማት ፕሮግራሞችን ዕውን ለማድረግ እንዲያስችል ሰፋፊ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በመሥራት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ ማድረግ፤

### 1.2 መርሆዎች

1) በልማት ፕሮጀክቶቹ የኮንስትራክሽን ሥራ በስፋት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማሰማራት የስራ ዕድል የሚፈጥር እንዲሆን እና የሚፈጠረው ሰፊ ጊዜያዊ የስራ ዕድል የኮንስትራክሽን ግንባታዎች በሚከናወኑባቸው አከባቢዎች የሚገኙ ዜጎችን እንዲሳተፉ በማድረግ ከልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ፣

2) የማስፈፀም አቅምን በማጠናከር በየደረጃው የሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ሥራዎቻችን የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ማሟላት፣ በአፈጻጸም ሂደት የግንባታ ግብዓቶች ጥራት፣ የሰው ሃይል ብቃት፣ የአሰራር እና አመራር እንዲሁም የተቀናጀ አሰራር ማስፈን፣ የወጪንና የጊዜ ብክነትን መከላከል የልማት ዓላማዎቻችንን ማሳካት፣

3) በሁሉም የልማት ፕሮጀክቶች የኮንስትራክሽን ሂደት የሃገር ውስጥ አቅምን ማዕከል ማድረግና በላቀ ሁኔታ ያለውን አቅም አሟጦ መጠቀም፣

4) ሰፊ፣ የተረጋጋና ፍትሃዊ የገበያ ውድድር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ሁሉንም የመንግሥት የልማት ኘሮጀክቶች በአነስተኛ ወጪ፣ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳና በተሻለ የጥራት ደረጃ መፈፀም እና ምርታማነትንና አዋጭነትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

## 2. የአነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ኘሮግራም

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የልማት ፕሮጀክቶች ለነባር ኢንተርፕራይዞች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግና አዳዲሶችንም በማቋቋም ወደ ስራ በማስገባት መጠነ ሰፊ የሥራ ዕድል ለዜጎች እንዲፈጠር ማድረግ እንዲቻል የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡

### 2.1 ዋና ዋና ግቦች

1) የሥራ ተከታታይነትን በማረጋገጥ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን የእለት ከእለት ክትትል የሚያደርጉ አማካሪዎች (Industry extension agent) በመመደብ የወጣቶቹን አመለካከት ለማሳደግ፣ የቁጠባ ባህላቸውን ለማሻሻል እና የብድር አመላለስ ምጣኔአቸውን ለማስተካከል እንዲደገፉ ይደረጋል፡፡

2) በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የሚያስፈልጉ ተቋማትን ቁጥር እንዲለይ፣ የ1,079,606 ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩና ለሚሳተፉ ሠራተኞች ለየሴክተሩ ግንባታ ተስማሚ የሆነ የአሠራር (working methodology) የሥልጠና ሰነድ በመቅረፅ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡

3) በኘሮጀክቶቹ በተለያዩ ሙያዎች የሚሳተፉ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን የሥራ ትስስር እንዲፈጠርላቸው፣ አቅማቸው እንዲገነባ፣ እና ልዩ ልዩ መሠረተ ልማት እንዲሟሉላቸው በማድረግ ለሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

4) የ8ቱ የልማት ኘሮጀክቶች በተለያዩ መስኮች የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በተቀናጀ ዕቅድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣

### 2.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) የልማት ፕሮጀክቶቹ በአነስተኛ ቴክኖሎጂና በከፍተኛ የሰው ኃይል ሊሠሩ የሚችሉ ሥራዎችን በመለየት አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በስፋት እንዲገቡ ማመቻቸት፤

2) በልማት ፕሮጀክቶቹ ለሚሳተፉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥልጠናና የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፤

3) በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሠሩ ሥራዎች ጥራት የሚያስጠብቁ ሥርዓቶችን መጠቀም፤

4) የብቃትና የሙያ ደረጃ (Occupancy Standared ) በዚሁ የሥራ ዕድል አማካይነት እየተፈተኑ የሚያረጋግጡበት ስርዓት መፍጠር፣

## 3. የሰው ኃይል ልማት ፕሮግራም

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በክህሎቱ ያደገና የበቃ የሰዉ ሃይል ስምሪት እንዲኖር፣ የሚታየውን የሙያ ቁጥርና ስብጥር ከሚያስፈልገው መጠን ጋር ማመጣጠን ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሠረት የሚፈለገውን ባለሙያ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት በማፍራት ለግንባታ ሥራዎች ጥራት፣ ወጪ እና ጊዜ ደረጃውን የጠበቀ የሙያ ግልጋሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን እቅዱ በግብ ከያዛቸው ፊዚካላዊ ውጤቶች ያልተናነሰ የሥራ ዕድል ፈጠራን ዓላማ በማድረጉ ወደ እቅዱ አፈፃፀም የሚያደርሱን ኘሮግራሞች እና ኘሮጀክቶች ሲቀረፁ የሰው ኃይልን በተለይም በመካከለኛ በዝቅተኛ ደረጃ የሰለጠነ እና ያልሰለጠነ የሰው ኃይልን በሰፊው የሚጠቀሙ አማራጮችን ማስቀመጥ ይጠበቃል፡፡ ይህንን ማድረግም ሥራዎችን እንደየክብደታቸው እና የሰው ኃይል ፍላጐታቸው መከፋፈል እና በዕውቀት ብዙዎች ሥራዎች በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ እና በበርካታ የሰው ኃይል እንዲከናወኑ ይደረጋል፣

### 3.1 ዋና ዋና ግቦች

1) በየትኛውም ደረጃ (level) የሚመደብ የሰው ኃይል ለምድቡ የተሟላ ዕውቀት እና ክህሎት ያለው እንዲሆን በማድረግ ለዚህም ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚፈለገውን የሰው ኃይል በየደረጃው በመከፋፈል ማወቅ እና ያለውን ኃይል (stock) ለማወቅም በምዝናና ምዝገባ የታገዘ እንዲሆን ይደረጋል፣

2) ያለንን ውሱን የሰለጠነ የሰው ኃይል በበለጠ ውጤታማነት ለመጠቀም በልዩ ልዩ ተቋማት በተቀጣሪነት የሚሰሩ እና ጥሩ የስራ አፈፃፀም ያላቸውን ባለሙያዎችን በማደራጀት፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ እና መነሻ የሥራ ትስስር በማድረግ መጠቀም እንደ አማራጭ ተወስዶ ይፈጸማል፣

3) በኢንዱስትሪዉ በምዝገባ እና በምዘና ያለንን በመካከለኛ ደረጃ እና በተግባር (practice) የሰለጠነ የሰው ኃይል ከተለየ በኋላ በየዘርፉ የሚጉለዉን በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ከአስፈፃሚዎች ተቋማት ጋር በተሳሰሩ ሥልጠናዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፣

4) ታላላቅ ኩባንያዎች በሥራቸው የሥልጠና ማዕከላት እንዲኖሯቸው ማድረግ እና በማዕከላቸው የሚያሰለጥኗቸውን ባለሙያዎች በሚደረግ የቅድሚያ ስምምነት መሠረት የሚያቆዩበት (retention) ሥርዓት ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ይውላል፣

5) ለየሴክተሩ የተዘጋጁትን የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች (occupancy) በመጠቀም፣ ተጨማሪ ደረጃዎችን በመለየት እና የሙያ እድገት መሠላል በመፍጠር የሚሰጡ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በበቂ እውቀት በፖኬጅ መልክ እንዲዘጋጁ በማድረግ ባለሙያዎች ደረጃ በደረጃ ከፍ ዋዳለ ዕርከን እንዲያድጉ ይደረጋል።

6) የሥራ ተከታታይነትን ለማረጋገጥም የኢንተርፕራይዞቹን ቁጥር ከታቀደው የሥራ መጠን ጋር አጣጥሞ መገመት እና አደረጃጀታቸው ከተዛማጅ ሥራዎች ጋር ተያይዞ ብቃትን እንዲያረጋገጥ ይደረጋል።

7) ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት የምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ስልጠና ከአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲዎች የማሰልጠን አቅም ቢያንስ 40 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው የተጀመረው ሥራ ተጠናቅሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

8) ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት የምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ስልጠና በኢንዱስትሪው ከሚያስፈልገው የሙያ ቁጥርና ስብጥር መጠን ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ይደረጋል።

9) የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን (TVET) በማጠናከርና በማደራጀት በቂ ቁጥርና የሙያ ብቃት ያላቸው መካከለኛ እና ዝቅተኛ ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ፣ በምዘናና ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፉ ይደረጋል።

## 3.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በየሙያውና ደረጃው በሚመለከታቸው አካላት መሰባሰብ፣ፕሮጀክቶችን ለባለሙያዎች ብቃት መመዘኛ አድርጎ መጠቀም፣

2) በምዘናና ምዝገባ ሥርዓት ያለውን የሰው ኃይል መረጃ መያዝ፤

3) የትምህርት ሥርዓቱ ከተቋማቱ የሚወጡ በቀጥታ ኢንዱስትሪውን በሚያገለግሉበት ደረጃ መቅረፅ፣

4) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት አቅም ግንባታ፣

- በሀገሪቱ የተገነቡ ልዩ ልዩ የቴክኒክና ሙያ ማዕከላት የሚሰጡ የሙያና ክህሎት ምዘና ስራዎች፣
- ለምዘናና ስልጠና የሚያስፈልጉ ወጪዎችን መጋራት፣
- ከኢንዱስትሪው ፍላጎት አንጻር ለሚፈጠሩ አዳዲስ ዘርፎች ስልጠናና ብቃት ማረጋገጥ የሚያስችል ዝግጅት አቅም ግንባታ፣

5) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አቅም ግንባታ

- በዘርፉ ልማት ላይ የተመሰረተ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣
- የትምህርት ካሪኩለሞች በተጨባጭ የልማት አጀንዳዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ማድረግ፣
- በስታንዳርድ ዝግጅት ላይ የቴክኒዎሎጂ ፋኩልቲዎችን አቅም ማሳደግ፣

6) የምህንድስና ሙያዎችን ማዕከል ያደረጉ የማበረታቻና የማቆያ ጥቅማ ጥቅሞች፤

## 4. የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ኩባኒያዎች ልማት ፐሮግራም

ደረጃውን ለጠበቀ ግንባታ ሆነ ለምክር አገልግሎት ዋነኛው መሠረት የሰው ኃይል ሲሆን ሌላዉ የተቋማቱ አደረጃጀትና ፍትሃዊ ተሳትፎ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ በሰው ኃይል ልማት ረገድ የሚደረገው ጥረት በትይዩ የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ድርጅቶችን ልማት የሚያግዝ ሲሆን በኢንዱስትሪዉ በብቃት እና በአደረጃጀት የተስተካከለ ቁመና ያለዉ የአማካሪና ስራ ተቋራጮች ተሳትፎ ይበረታታል፡፡

### 4.1 ዋና ዋና ግቦች

1) በመካከለኛ ደረጃ አዳዲስ የስራ ተቋራጮችን በማቋቋም፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ነባር የሥራ ተቋራጮች ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ በማመቻቸት የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች ቁጥር አሁን ካለበት ቢያንስ በ2000 እንዲያድግ ይደረጋል፤ አቅማቸውም በየጊዜው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡
2) በመካከለኛ ደረጃ አዳዲስ አማካሪ ድርጅቶችን በማቋቋም፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ነባር አማካሪዎች ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ በማመቻቸት የአገር ውስጥ አማካሪ ድርጅቶች ቁጥር አሁን ካለበት ቁጥር በ400 እንዲያድግ ይደረጋል፤ አቅማቸውም በየጊዜው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡
3) የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የፋይናንስ አቅም አጎልብተው የአገር ውስጥ የገበያ ፍላጎት እንዲሸፍኑ ይደረጋል፡፡
4) በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የልማታዊ ባለሃብት ዘመናዊ የኮንስትራክሽን አመራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ስልጠና በመስጠት ዝግጁነታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
5) ለልዩ ልዩ የምክር አገልግሎት ግዥ የሚጠየቁ የመግቢያ መሥፈርቶች በማስተካከል ተጨማሪ አማካሪ ድርጅቶች ወደ ሥራዎች እንዲገቡ ማስቻል ተገቢ ይሆናል ፡፡ ይህን ማድረግ በተለያዩ መስኮች ልምድ ያላቸው ድርጅቶች እንዲኖሩ እና ዘርፉም የጠነከረ ውድድር ያለበት እንዲሆን ይደረጋል፣

6) ከወጪ ሃገር ለሚፈፀሙ የምክር አገልግሎቶች ግዢ የአገር ውስጥ አማካሪ ድርጅቶች በፕሮጀክት ትግበራው ላይ አጋዥ /Counter part/ ሆነው እንዲሰሩ የሚያደርግ አሠራር ተግባራዊ ይበረታታል፣

7) በምክር አገልግሎት ዘርፍ የሚታየውን የሽፋን እና ስብጥር ጉድለት ለማጥበብ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ ባለሙያዎችን በተለያዩ ምድቦች /Catagories/ በአማካሪ አሃዶች እንዲደራጁ ይበረታታሉ፣

8) በዕቅድ ዘመኑ በሚከናወኑ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን ማዕከል በማድረግ በአማካሪ ድርጅቶች ውስጥ የሚያገለግሉ ባለሙያዎች ያለባቸውን የዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ችግሮች ለመቅረፍ እና ከነባር እና አዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር በአግባቡ ለማስተዋወቅ ተከታታይነት ያለው የሥራ ላይ ሥልጠና በሙያው የዳበረ ዕውቀት ባላቸው የውጪ ሀገር እና የሀገር ውስጥ አንጋፋ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ይደረጋል፣

9) በምክር አገልግሎት ዘርፍ የምህንድስና የትምህርት ክፍሎች ያሏቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምሩቃኖቻቸውን ከሚቀበሉ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ጋር ስምምነት በማድረግ በምርምር ሥራዎች፣ በአዋጪነት ጥናቶች፣ እና በዲዛይን ሥራዎች ላይ በመሣተፍ ዘርፉን አግዘው የተቋማቸውን አቅም እንዲገነቡ ይደረጋል፣

10) በሥራ ላይ ለሚገኙ አማካሪ ድርጅቶች ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ የደረጃ /grade/ እድገት እንዲያመጡ ይደረጋል፡፡ በልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ላይ ለመሳተፍም የሚጐሏቸው ቁልፍ ባለሙያዎች ሲኖሩ ከውጭ ሃገር በማስመጣት ፕሮጀክቶቹን የሚያከናውኑበት እና የክህሎት ሽግግርም የሚያደርጉበት አሰራር ይዘረጋል፣

11) በየደረጃው የሚደረጉ የአቅም ግንባታዎች ድጋፎች በምቹ የውስጥ አደረጃጀት የታገዙ እንዲሆኑ የአማካሪ ድርጅቶች የISO ወይንም ሌሎች አለም አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ ውስጣዊ ይዘት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

## 4.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) የሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች ልምድ፣ ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የፋይናንስ አቅም እንዲጎለብት ከውጭ ባለሀብቶች ጋር እንዲሠሩ ማመቻቸት፤

2) የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች የተሟላ አቋም እንዲኖራቸው የISO ወይንም የሌሎች ዓለም አቀፍ ደረጃ ሰጪዎች ያላቸውን የአሠራርና የአደረጃጀት ብቃት እንዲያስመዝኑ ማበረታታት፤በእነዚሁ ፕሮጀክቶች አማካይነት የብቃት ደረጃቸው የተረጋገጠ ባለሙያዎችን እንዲያሰማሩ ማድረግ፣

3) ሥራዎች በተሻለ ጥራትና ምርታማነት እንዲሠሩ ንዑስ የሥራ ተቋራጭነትን ማበረታታት፤

4) የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች በአንድ ጊዜ ከአቅማቸው በላይ ፕሮጀክቶች እንዳይዙ በተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት መከላከል፤

5) የብድርና ዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት ከፕሮጀክት የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተናበበ እንዲሆን ማድረግ፤

## 5. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶች፣ የግብዓት አቅራቢዎችና አምራቾች ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች አቅርቦት አቅም እንዲጎለብትና በኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊው የፋይናንስ ድጋፍና የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡

### 5.1 ዋና ዋና ግቦች

1) የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የፋይናንስ አቅም አጎልብተው የአገር ውስጥ የገበያ ፍላጎት እንዲሸፍኑ ይደረጋል፡፡

2) በሥራ ላይ የሚገኙት የኮንስትራክሽን መሣሪያና ማሽነሪ አከራይ ድርጅቶች አቅማቸው እንዲያድግና ፍትሀዊ የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ይመቻቻል፡፡

3) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መካከለኛ የጥገና አቅም ያላቸው የመንግስትና የግል ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ ተመቻችቶላቸው አቅማቸው እንዲያድግ በማድረግ ወደ ከባድ መሣሪያዎች ጥገና እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

4) ባለሀብቶችና አቅም ያላቸው ተቋማት ያላቸውን መሣሪያ ወይም አዳዲስ በማስመጣት ለኪራይ አገልግሎት እንዲያውሉ የመሣሪያ ሊዝ ሥርዓት ይመቻቻል፡፡

5) የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን በሃገር አቅም ደረጃ በደረጃ ለመስራት የሚያስችል የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል፣ ግብዓት አቅርቦት ይመቻቻል፡፡

6) ከኮንስራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት ጋር የተያያዙት ችግሮቻችን ያሉንን በአግባቡ መጠቀም ካለመቻል የሚጀምር በመሆኑ ለመሣሪያ አንቀሳቃሾች በሥልጠና እና በምዘና ሥርዓት እንዲያልፉ ይደረጋል፣

7) በበርካታ ተቋራጮች እጅ የሚገኙ ሥራ ያልያዙ መሣሪያዎች ለመጠቀም በፕሮጀክቶቻችንን አስተዳደር ውስጥ የንዑስ ተቋራጭ አሰራር ሥራ ላይ እንዲዉል ይደረጋል፣

8) ከባድ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠይቁ (heavy and high-tech) መሣሪያዎች ጎን ለጎን መካከለኛ እና ቀላል የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን በመጠቀም መጀመር ስለሚገባን የመካከለኛ እና ቀላል መሳሪያዎች እና የተመጣጠነ የጉልበት አጠቃቀም እንዲበረታታ ማስቻል እና ለዚህም በብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶቻችን ውስጥ መካከለኛ መሣሪያዎች በአቻ ግምት እንዲካተቱ በማድረግ በቀጣይ መሣሪያዎቹ ደረጃ በደረጃ በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ይደረጋል፣

9) ከውጪ የምናስገባቸው መሣሪያዎች በመንግስት ላይ የሚያስከትሉትን የወጪ ጫና ለመቀነስ እና የቁጠባ ባህልን እንዲዳብር ለማድረግ የፋይናንስ አቅርቦቱን ከንግድ ባንክ የ40-60% የብድር ፖሊሲ ጋር በማስተሳሰር እንዲሰራ ይደረጋል፣ የድህረ ሺያጭ አገልግሎትን ጨምሮ ለምናደርገው ግዥ የሚመጥን የማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ አቅም ግንባታ ይሰራል፣

10) አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመሳሪያዎች እና ሌሎች የመገልገያ ቁሳቁስ ግዢ ወቅትም ተጠቃሚዎችን ማሳተፍ እና የሚገዙት መሳሪያዎች እና ቁሳቁስ ጥራት፣ በቂ የመለዋወጫ እና የድህረ ሺያጭ አገልግሎት (after-sell service) እንዲኖር ይደረጋል፣

### 5.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) በጥገና ላይ የተሰማሩ አካላት በየጊዜው አቅማቸውንና ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ የብድር ሥርዓት ማመቻቸት፤
2) የኮንስትራክሽን መሣሪያ መግዛት የሚችሉ ባለሀብቶችና ባለቤት የሆኑ ድርጅቶች የመሣሪያዎች ሊዝ ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
3) የተዛባ የመሣሪያ ኪራይን ለመከላከል ባለሀብቶች በማህበር እንዲደራጁና ሕጋዊ ሰውነትና ሥርዓት እንዲኖራቸው መደገፍ፤
4) በሃገር አቅም በመስራት የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን የመተካት አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የፋይናንስ፣ የሰዉ ኃይል፣ ግብዓት አቅርቦትና እንዲሁም የገበያ ዕድል መፍጠር፣
5) የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አቅም ግንባታ፣
   - የማሽነሪ ማምረትና ቀጣይነት ያለዉ ጥገና ስራ ለመስራት የሚያስችል የስራ ትስስር መፍጠር፣
   - ለስራ የሚያስፈልጉ ማሽነሪ ቴፖሎጂዎችን በጥናትና ምርምር በማስደገፍ ዲዛይን የማድረግ አቅም መገንባት፣

## 6. የኮንስትራክሽን ግብዓት አቅርቦትና ማምረቻ ተቋማት አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ሀብቶችን በግልጽ ለይቶ በማወቅና እጥረት ባሉብን ጥሬ ሃብቶች በምን መልኩ ወይም ደረጃ ከውጭ ልናስመጣ እንደሚገባን በመወሰን ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ በመሥራት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ነባር የግብዓት ማምረቻ ተቋማት እንዲደገፉ፣ አዳዲሶች እንዲገቡ በማመቻቸት የኮንስትራክሽን ግብዓቶች በስፋት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

### 6.1 ዋና ዋና ግቦች

1) የሀገራችን የኮንስትራክሽን ሀብቶችን በግልጽ እንዲታወቁ በማድረግ፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን በማስቀመጥ በመጪው አምስት ዓመት የሚካሄደው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውጤት የተሳካ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
2) የግንባታ ዕቃዎችን በሚፈለገው መጠን፣ ዓይነትና ጥራት በሀገር ውስጥ ምርት ለማቅረብ የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፤ የተጀመሩት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በሙሉ አቅም ማምረት እስከሚቻል ከሀገር ውጭ የሚገባበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡
3) ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ያላቸው ግብዓቶችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን በመለየት የሚደገፉበት ሁኔታዎች ይመቻቻል፡፡ አዳዲስ በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት ፋይናንስ የማመቻቸት፤ ቴክኖሎጂዎቹን የማስተዋወቅ፣ ትምህርትና ሥልጠና የመስጠት እና የማማከር አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይመቻቻል፡፡

4) ከፍተኛ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ዕጥረት በሚታይባቸው የብረትና ማጠናቀቂያ የግንባታ ዕቃዎች በጋራ ግዢ ሥርዓትና ጥብቅ የጥራት ቁጥጥር በመዘርጋት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና የጥራት ደረጃን ጠብቀው እንዲመረቱ ይደረጋል፡፡

## 6.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) በከፍተኛ ደረጃ ለአገልግሎት የሚውሉ የግንባታ ዕቃዎችን ወቅታዊ መረጃ ከCSA በጋር ተቀናጅቶ ማዘጋጀት፤
2) የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በግንባታ ዕቃዎች ምርትና አቅርቦት ላይ እንዲሠማሩ ማበረታታት፤
3) የድጋፍ ሰጪ ተቋማት አቅም ግንባታ
   - የኮንስትራክሽን መሳሪያና ግብዓት ማምረቻ ተቋማትን ልማት ማበረታታትና መደገፍ፣
   - ለሲሚንቶና ብረት እንዲሁም ተኪ ማምረቻ ተቋማት ቅድሚያ መስጠት፣
   - በዝቅተኛ ደረጃ የሚሰሩ ልዩ ልዩ የግንባታ ቁሳቁሶችን ጥራትና ምርታማነት ደረጃ ማሻሻል፣
   - በሃገር አቅም በመስራት ገቢ ምርቶችን የመተካት አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የፋይናንስ፣ የሰዉ ኃይል፣ ግብዓት አቅርቦትና እንዲሁም ገበያ ዕድል መፍጠር፣

# 7. ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የተሻሉ ቴክኒዎሎጂዎችን መጠቀም ፕሮግራም

በሀገር ውስጥ የተሻሉ የግንባታ ዕቃዎች አቅርቦት መጠንና ጥራት ለማሳደግ፣ ከሀገር ውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት፣ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ የአገነባብ ቴክኖሎጂዎችንና ዘዴዎችን ለማስፋፋት፣ በጥናት፣ በምርምርና በማላመድ በመታገዝ የኢንዱስትሪዉ አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው፣ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡

## 7.1 ዋና ዋና ግቦች

1) የኮንስትራክሽን ምርምር ተቋማትን በማቋቋም ለቴክኖሎጂዎች ማስፋፊያነት እንዲያገለግሉ ለማድረግ የተለያዩ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡

2) ከትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከጥራትና ደረጃ መዳቢዎች ባለሥልጣንና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዓለም አቀፍ የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን፣ የዲዛይን ሶፍትዌር መምረጥና ከአገራችን ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

3) ለቴክኖሎጂ ጥናትና ማላመድ ሥራዎች የሚያስፈልግ የሰው ሃይል እንዲለይ ተደርጎ እንዲሟሉና አስፈላጊው የሙያ ድጋፍ እንዲያገኙ ይመቻቻል፡፡

4) ለየግንባታ ዓይነቶች የተቋቋሙ የጥራት መፈተሻ ማዕከላት ብቃት ባለዉ ሰዉ ኃይልና በዘመናዊ የላቦራቶሪ መቆጣጠሪያ ቁሳቁሶች የተሟሉ እንዲሆኑ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡

### 7.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) ዓለም አቀፍ አሠራሮችን በመፈተሽ የተሻሉትን የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን ከአገራችን ጋር በሚጣጣም መልኩ ማዘጋጀት፣
2) ለአዳዲስ አሠራሮች የሚያስፈልግ የሠው ሃይል ዝግጅት እንዲኖር ማድረግ፣
3) ለእነዚሁ ቴክኖሎጂዎች ማስፋፊያነት እንዲያገለግሉ ተቋማትን በማቋቋም፣ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እና አፈጻጸማቸውን መከታተል፤
4) የግንባታ ጥራት መቆጣጠሪያ ማዕከላት አቅም ግንባታ
   - የዘመናዊ የላቦራቶሪ መቆጣጠሪያ ቁሳቁሶች በግዥ ማሟላት፣
   - የስራ ላይ እና የውጭ ሃገር ስልጠናዎችን መስጠት፣
   - ብቃት ባለዉ ሰው ኃይል ማደራጀት፣

## 8. የመንግስትና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ፕሮግራም

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ አካላት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር፣ የሴክተር ልማት ባለቤቶች፣ የመሠረተ ልማት ተቋማት፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶች፣ የሙያ ማህበራት በመደጋገፍና በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት በዘርፉ ለሚፈጠሩ ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ በጋራ ለማመንጨት ነው፡፡

### 8.1 ዋና ዋና ግቦች

1) የመንግስትና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት በማጠናከር ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አስፈጻሚዎችና ተዋናዮች የስነ ምግባር ደንብ በማዘጋጀት፣ በኢንዱስትሪው የተደራጁ የሙያ ማኀበራት ለዘርፉ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ እንዲያሳድጉ ይደረጋል፡፡
2) ዕቅዶቻችንን የጋራ ለማድረግ እና አፈፃፀማችንን የባለድርሻ አካላትን በአግባቡ ባሳተፈ መልኩ ለመከታተል እንዲቻል የመንግስትን አወቃቀር እና አሰራር ከግምት ያስገባ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት (Construction Industry Council) እንዲቋቋም ይደረጋል፣
3) የሙያ ማህበራት የላቀ ተሞክሮ ካላቸው የውጭ የሙያ ማህበራት የክህሎት ሽግግር የሚያደርጉበት ሁኔታዎች ይመቻቻል፡፡
4) በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን የግንባታ አገልግሎትና አቅርቦት በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ከፍላጎቱ ጋር እየተጣጣመ መሄዱን የሚረጋገጥበት፣ በአቅራቢዎችና ልማቱን በአቀዱት ሴክተር መሥሪያ ቤቶች መካከል የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የተቀናጀ የዕቅድና የአፈፃፀም ቅንጅት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

### 8.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) የሚወጡ ህጎች ቀረፃ የሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት፣ የሙያ ማህበራትና የግሉን ዘርፍ ማሳተፍ፤
2) ከሙያ ማህበራት ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
3) በዘርፉ የተሻለ እንቅስቃሴ ለሚያበረክቱ የሙያ ማህበራት ማበረታቻና ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፤
4) የተዋናዮች ልዩ ልዩ ማህበራት አቅም መገንባት፤
   - የሙያና የንግድ ድርጅቶች በማህበር እንዲደራጁ ይበረታታሉ፤
   - በተለዩ ጉዳዮች ላይ እንዲሰሩ ስልጣን መስጠት፤
   - የተቋራጭና ባለሙያ እንዲሁም አማካሪ ምዝገባ ስርዓት ማሻሻል፤

## 9. የኮንስትራክሽን ማስፈፀሚያ የፖሊሲ የህግና አሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በሥርዓት እንዲመራ፣ ሥርዓቶችን በአግባቡ ለመተግበር እንዲበቃ በማድረግ ላይ የተመሠረተና ኢንዱስትሪው ፈጣን ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ለመፍጠር ነው፡፡ ለተያያዝነው መጠን ሰፊ ዕቅድ አፈፃፀም ተመጣጣኝ የሆነ የአሠራር ሥርዓት እና ጠንካራ የሬጉላቶሪ አቅም እንዲኖረን ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ ለዘርፉ የሚያስፈልጉ የሌሉ ህጎችን በመለየት የማዘጋጀት እንዲሁም እስካሁን በሥራ ላይ ያሉትም ተፈትሸው የማሻሻል እና የማጣጣም ሥራ ታቅደው የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

### 9.1 ዋና ዋና ግቦች

1) በሀገሪቱ ኮንስትራክሽን የምቾት፣ የደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሂደቶች፣ የኮንስትራክሽን ጨረታ፣ ውለታ፣ ዋስትና፣ ግጭት አፈታትና ይግባኝ ሥርዓቶች እንዲሁም በውስጡ የሚሳተፉ አካላት የሚመሩበት የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የምክር፣ የቁጥጥር እና የማኔጅመንት ሁኔታዎችን የያዘ የኮንስትራክሽን ህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፤
2) ለመንገድ፣ ለህንጻ፣ ለመስኖ፣ ለኃይል ማመንጫና ለባቡር መሠረተ ልማት ዲዛይኖችና ግንባታዎች ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ፣ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲዳረሱና ተግባራዊነታቸው እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል፤
3) በጥናትና ምርምር የሚገኙ አዲስና የተሻሻሉ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችና የአገነባብ ዘዴዎችን ስታንዳርድ እንዲወጣላቸውና ለምናዘጋጃቸው ህጎች ግብዓት ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፤
4) የአማካሪና ሥራ ተቋራጭ ድርጅቶችና ለሠሯቸው ሥራዎች ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የህግ አግባቦች ቢኖሩም ከዚህ አንፃር ለፕሮጀክት በተያዘበት ጊዜ እና ወጪ መጠናቀቅ እንዲተጉ የሚያደርግ አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

5) የሥራ ተቋራጮችን አቅም ለመገንባት ፕሮጀክቶችን በንኡስ፣ በንኡስ በመክፈል ወደ አብዛኛው ሥራ ተቋራጭ አቅም ማምጣት እና የመግቢያ መስፈርቶችን ለማመጣጠን የሚያስችል ማሻሻያ ይደረጋል፤

6) የፕሮጀክቶቹን አጣዳፊነት ልዩ ባህሪያት እና የአገር በቀሉን አቅም መገንባትን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በመያዝ ለአቅም ግንባታ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን በመለየት፣ በውጪ ሀገር ሥራ ተቋራጮች እና አገር በቀል ሥራ ተቋራጮች መካከል፣ በአገር በቀል ሥራ ተቋራጮችም መካከል እርስ በእርስ የንኡስ ስራ ተቋራጭነት (sub contracting) አሰራር እንዲኖር ይበረታታል፤

7) የሽሙር (joint venture) አሰራርን ጨምሮ ሌሎች ከኮንስትራክሽን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አሰራሮች እና ህጎች በመከለስ ማስተካከያዎች ይደረጋል፤

8) የሥራ ተቋራጮች የፋይናንስ (cash flow) ችግር ለማቃለል መተዋወቅ ያለበት አሰራር በአሰሪ፣ በተቋራጭ እና በፋይናንስ ተቋማት መካከል የብድር አሰጣጥ እና የአመላለስ የሶስትዮሽ ስምምነት አሰራር ለጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት አቅም ግንባታ በሰፊው የምንጠቀመው እና ውጤት ያስገኘ አሰራር እንደመሆኑ ለመካከለኛ እና ከፍተኛ ሥራ ተቋራጮችም በሚመጥን መልኩ ተቀርፆ ስራ ላይ ይውላል፤

9) አንድ ተቋራጭ ሊይዘው የሚገባው የፕሮጀክት መጠን ካለው አቅም ጋር እንዲመጣጠን በማድረግ ያልተመጣጠኑ ፕሮጀክቶችን ከመያዝ ጋር የተገናኙ የአፈፃፀም ችግሮች ለመቀነስ፡ የአገራችን ሥራ ተቋራጮች ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸማቸው (annual turnover) ለማሻሻል ትላልቅ እና በርካታ ፕሮጀክቶችን እንዲያገኙ በማድረግ አካሄዱም ከድርጅቶቹ ውስጣዊ ጥንካሬ እና ከተመጣጠነ ውድድር ጋር እንዲሆን ይደረጋል፤

10) በመንገድ፣ በህንጻ፣ በመስኖ፣ በኃይል ማመንጫና በባቡር መሠረተ ልማት ግንባታዎች ፕሮጀክት አስተዳደር ባለሙያዎች በብዛት እንዲፈሩ የኮንስትራክሽን አመራር ማብቃት ሥርዓት ይዘረጋል፤

11) በየሴክተር ልማቱና በማዘጋጃ ቤቶች የሚገኙ ባለሙያዎች፣ በኢንዱስትሪው የተሰማሩ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ምዝገባ ምቹ፣ ቀልጣፋ፣ በሙያ ምዘና የሚያልፉበት ሥርዓት የተቀመጠለትና ተመጣጣኝ መስፈርት ያለው እንዲሆን ይደረጋል፤

12) የኮንስትራክሽን ሥራዎች በጥራት፣ በጊዜ፣ በወጪ፣ በምቾት እና በደህንነት በላቀ ደረጃ የሚያስጠብቅና በሚፈለገው ደረጃ መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ይውላል፤

13) የአማካሪዎች የአገልግሎት ክፍያ በውጤትና በፕሮጀክት አፈጻጸም መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣

14) የተሟሉ ወቅታዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰባሰቡ ይደረጋል፤

### 9.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ማስፈፀም አቅም ግንባታና የድጋፍ ማዕቀፍ ስትራቴጂ በመንግስት ማፀደቅ፤
2) በኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉ የሬጉላቶሪ ኮዶችና ስታንዳርዶች መዘርዝር፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማሰባሰብ፣ በየዲሲፕሊኑ መከፋፈልና እንዳስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የዘርፉና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የጋራ ዕቅድ አዘጋጅቶ መምራት፤
3) በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች በየጊዜው በምዘናና ምዝገባ ሥርዓት አልፈው መሰማራታቸውን በማረጋገጥ፤
4) የኮንስትራክሽን ማቴሪያል ምርምር ኢንስቲትዩት በማቋቋም፡-
   - የየንዑስ ዘርፉ ማኔጅሜንት ብቃት ለማሳደግ፣
   - በንዑስ ዘርፉ ዕቅዶች ከዲዛይን አገልግሎት ዘመን ጋር ያላቸውን ቁርኝት በማየት በጥገና፣ በክብካቤና አጠቃቃም እንዲሁም ማሻሻል ላይ የተመሰረተ አቅጣጫ እንዲከተሉ የማስቻል አቅም ግንባታ፣
   - በስራ ሂደት የተለዩ የውጭ ሃገር ተሞክሮዎችን በመቀመር በሃገር ውስጥ የመተካት አቅጣጫ በመከተል አቅም መገንባት፣

## 10. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኤግዚቢሽንና ንግድ ትርኢትና ምክክር መድረክ

በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የኮንስትራክሽን ዕድገት የሚያመላክቱ የተሻሻሉ የዲዛይንና የግብዓት አቅርቦቶች፣ የቴክኖሎጂና የአሠራር ለውጦች ለመረዳት እንዲሁም የልምድ ልውውጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው መድረኮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

### 10.1 ዋና ዋና ግቦች

1) በየዓመቱ የዲዛይንና የግብዓት አቅርቦቶች ኤግዚቢሽንና የንግድ ትርኢት በማዘጋጀት የልምድ ልዉዉጥ የቴክኖሎጂ ሽግግር መድረክ እንዲፈጠር ይደረጋል።
2) የኢንዱስትሪውን ዕድገት ደረጃ፣ ብቃትና አቅም የተግባር ማሳያ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል።
3) የኢንዱስትሪው አዳዲስ ፈጠራ፣ ምርምር ውጤቶችና ግኝቶች ዕውቅና ይሰጣቸዋል።

### 10.2 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1) ዓመታዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ቀን፤
2) ልዩ ልዩ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ነክ ኤግዚቢሽንና መድረኮች ዝግጅት፤
3) የሙያና የንግድ ማህበራት የጋራ ምክክር መድረክ ዝግጅት፤

## V. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ባለሚናዎች፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ተቋማትና ሚናቸው

### 1. የልማት ዕቅዶቹን ለማሳካት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ባለሚናዎች፤

#### 1.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

1) በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀማቸውን መከታተል፤
2) በየፕሮጀክቶቹ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የብቃት ደረጃቸው የተረጋገጠ እንዲሆን ተገቢውን ሥርዓት መዘርጋትና ድጋፍ መስጠት፣
3) ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነውን መጠን ከ17 በመቶ ያላነሰውን በቋሚነትና በተከታታይነት የሚቆጥቡበት ሥርዓት ለመፍጠር ከተዋናዎቹ ጋር መግባባት ላይ መድረስ፣

#### 1.2 ሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች ባለሙያዎች

1) በከፍተኛ ሥነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃት ተቋማቸውን ማደራጀት፣
2) በተሰማሩበት ስራ ስኬታማነት በጊዜ የለኝም ቅኝት ለመፈፀም መስራት፣
3) በውለታ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በመሆኑ ስምምነቱን በላቀ ሁኔታ ማክበር፣ ለጋራ ውጤት ተባብሮ መሥራት፣
4) የልማት ስራዎቻችን ወጪ ቆጣቢ ጥራት ያላቸዉ ሆነው እንዲጠናቀቁ በዲዛይን ዝግጅትም ሆነ በግንባታ ሂደት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣

#### 1.3 የናሙና ፍተሻ ተቋማት

1) የውስጥ አቅም በመገንባት ለኢንዱስትሪው አስተዋፅዖ ማበርከት፣
2) ለሙያ ሥነ ምግባር በመገዛት የግንባታዎች እና ዕቃዎች የጥራት ደረጃ ቁጥጥር ማካሄድ፣
3) የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣

#### 1.4 የኮንስትራክሽን ግብአት አምራቾችና አቅራቢዎች

1) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያስፈልገዉን ልዩ ልዩ ግብዓት በተወዳዳሪ ዋጋና በበቂ መጠን ማቅረብ፣
2) በማህበራት በመደራጀት በኢንዱስትሪው ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥና ተገቢው ግልጋሎት በመስጠት ኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል፣

#### 1.5 የአማካሪዎችና ስራ ተቋራጮች ማህበራት

1) በሚወጡ ህጎች ላይ ተሳትፎ ያደርጋል፤ በአባላቱ የሚመለከቱ ክፍተቶች እንዲሞሉ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፣
2) አባላቱ የሚመሩበት የሥነ ምግባር ደንብ ያዘጋጃል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

3) በነጻ ገበያ ላይ የተመሰረተ የገበያ ዉድድር ለማድረግና የዘርፉን ተወዳዳሪነት አቅም ለመገንባት የላቀ የስራ ዲሲፕሊንና ስነ ምግባር ደረጃ መገንባት፣

## 2. የስትራቴጂው አስፈጻሚ አካላትና ድርሻ

### 2.1 ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

1) የማስፈፀሚያ ዕቅዱ እንዲተገበር ያስተባብራል፣
2) የራሱን ፕሮጀክት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን በሃላፊነት ይመራል፣ በባለቤትነት ይከታተላል፣
3) ለአፈጻጸሙ ስኬት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
4) የኢንዱስትሪው አካላት የግብዓት ፍላጎት መረጃ ይሰበስባል፤ ያቀናጃል ፍላጎቱ እንዲሟሉ ከሚመለከታቸውጋር ምክክር ያደርጋል፤
5) በዘርፉ ሚና ያላቸውን አካላትን ማስተባበር፤
6) በስትራቴጂው የተቀመጡ የአሠራር ሥርዓቶች፣ ህጎችን ያጠናል፤ ያስፀድቃል፣ በተግባር ላይ እንዲውል ይደግፋል፣ ይከታተላል። የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል።

### 2.2 የልማቱ ፈፃሚ ሴክተር መ/ቤቶች

1) የልማቱ ሴክተር መሥሪያ ቤት የራሱን የፖሊሲ ማዕቀፍና ህግና አሠራር ሥርዓት ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ይፈፅማል፣
2) በየጊዜው ዕቅዳቸውን በመከለስ ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች ይለያሉ፣
3) በየጊዜው የተደረጉ ለውጦችን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ያደርጋል፤

### 2.3 የክልል አስፈጻሚ አካላት ድርሻ

1) ለስትራቴጂው ተፈፃሚነት የሚወጡ ህጎችን መሠረት ያደረጉ ዝርዝር መመሪያዎችና ማንዋሎች ያዘጋጃሉ። ለህጎች ተግባራዊነት ይደግፋሉ። ክትትል ያደርጋሉ፤
2) በክልል ደረጃ ዕቅዱን በሃላፊነት ያስፈጽማሉ፣ በባለቤትነት ይከታተላሉ፤

### 2.4 የከተማ አስፈጻሚ አካላት ድርሻ

1) በከተሞች ደረጃ የከተማ ምክር ቤቶች ዕቅዱን በሃላፊነት ያስፈጽማሉ፣
2) የመሠረተ ልማት አቅርቦቶችና የቅንጅት ሥራዎች የተሳኩ እንዲሆኑ ያስተባብራሉ፣

### 2.5 የትምህርት ሚኒስቴር ድርሻ

1) የሰው ኃይል ፕሮጀክት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን በሃላፊነት ይመራል፣ በባለቤትነት ይከታተላል፤
2) ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመስፈርት ዝግጅት በቅንጅት ይሠራል፤

### 2.6 የፌደራል ቴክኒክና የሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ ድርሻ

1) በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን የመለስተኛ ባለሙያ የሥልጠና ዕቅድ ያዘጋጃል፣

2) የሥልጠና ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፤

3) ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር የምዘና ሥራዎችን ይሠራል፤

4) የክልል የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲዎች አቅም ይገነባል፤

## 2.7 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ምክክር ምክር ቤት ድርሻ

1) በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዉ የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የበላይነት እንዲይዝ አቅዶ መፈፀም፤

2) በኢንዱስትሪው ቅንጅታዊ ሥራ እንዲጎለብት አስተዋፅዖ ማበርከት፤

3) ለአማካሪውና ለኢንዱስትሪው ዕድገት አስተዋጽኦ ማበርከት፤

4) የሬጉላቶሪ የአቅም ግንባታና ዋና ዋና ግብዓቶች አቅርቦት ማረጋገጥ፤

5) በፖሊሲና ስትራቴጂዎች እንዲሁም እነዚህን መሰረት አድርገው በሚረቀቁ ህጎች፣ ስታንዳርዶች ምክር መስጠት እና አዳዲስ ሃሳቦችን ማመንጨት፤

6) በዘርፉ በሚያጋጥሙ መሰረታዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ የጋራ አቅጣጫ መያዝ፣

## VI. የክትትልና የግምገማ ሥርዓት

### 1. ውይይትና ዝርዝር ዕቅድ ዝግጅት

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም በቅድሚያ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በዕቅዱ ላይ በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚሁ መሠረት በፕሮግራሙ ላይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይት ማድረግ የሚገባ ሲሆን በየደረጃው ባሉ አስፈጻሚ አካላትም ዝርዝር የማስፈጸሚያ ዕቅድ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም፡-

1) በዕቅዱ ላይ ግልጽነት፣ ተነሳሽነት የጋራ አመለካከት እና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖር ሁሉም የፌዴራል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የሚመለከታቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኤጀንሲ፣ የክልል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች እና የከተማ መስተዳድሮች እንዲወያዩበት ይደረጋል፣

2) እያንዳንዱ የፌዴራል አካል፣ የክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮዎችና ከተሞች የተዘጋጀውን አገራዊ ዕቅድ መሠረት አድርገው የራሳቸውን ዝርዝር የማስፈፀሚያ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ይደረጋል፣

### 2. የአፈጻጸም ክትትል ሥርዓት መዘርጋት

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን አፈጻጸም አስመልክቶ ቀጣይነት ያለው ክትትል ለማድረግ አፈጻጸሙን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች እና ማንኛውም ዓይነት መረጃዎች በየደረጃው ባሉ መዋቅሮች በአግባቡ ተደራጅተው እንዲያዙና በየጊዜው ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

1) በፌዴራል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ በፌዴራል በሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ በክልሎችና በከተሞች ደረጃ ዕቅዱን በሚያስፈጽሙ አደረጃጀቶች ውስጥ የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትል እና ግምገማ ክፍሎች እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣

2) የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስፈጻሚ አካላት የዕቅዱ" ዝርዝር የአፈጻጸም ሪፖርት በየሶስት ወርና በየስድስት ወሩ በማዘጋጀት በየደረጃው ላሉ አካላት ያስተላልፋሉ፣

3) የሪፖርቶቹ ዝግጅትና አቀራረብ በዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን ግቦችና ተግባራት እንዲሁም በሚቀጥለው ክፍል የተመለከቱትን የክትትልና ግምገማ አመልካቾችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፣

4) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ ባለሙያዎችና የሙያ ማህበራት፣ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች፣ የሚመለከታቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ሌሎች በኢንዱስትሪው የተሰማሩ አካላት የዕቅዱን አፈጻጸም ውጤት፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በማጥናት ለተሻለ አፈጻጸም ድጋፍ የሚሰጡበት አሠራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፣

## 3. የክትትልና ግምገማ አመልካቾች

በየፕሮጀክቶቹ የተመለከቱትን ግቦችና ተግባራት አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችሉ አመልካቾች ተቀርፀው በሚዘረጋው የክትትል ሥርዓት መሠረት ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡ በፕሮግራሙ ለታቀፉት ፕሮጀክቶች ዋና ዋና የሆኑት አመልካቾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

### 3.1 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የፖሊሲ ማዕቀፍ ፕሮጀክት አመልካቾች

1) በማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ሰነዱ ላይ የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣
2) ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማስፈፀሚያ የተዘጋጁ ሠነዶች ዓይነትና መጠን፣
3) ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተዘጋጀ የማስፈፀሚያ መዋቅር፣
4) ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ማስፈፀሚያ ዕቅድ የተፈጠረ አደረጃጀት፣
5) የአስፈጻሚ አካላትን የአፈጻጸም አቅም ለመገንባት የተሰጡ ስልጠናዎችና የተቀረፁ አዳዲስ አሠራሮች፣
6) የተደራጁና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የኢንዱስትሪው መረጃዎች፣

### 3.2 የሥራ ዕድል ፈጠራ

1) በልማት ፕሮጀክቶቹ ለተፈጠረው የሥራ ዕድል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዞ የተዘረጋ የመረጃ ሥርዓት፣
2) አንቀሳቃሾችን ለመደገፍ የተዘጋጁ የሥራ ዕድል ፈጠራ አስፈፃሚ አካላት፣
3) ለየፕሮጀክቶቹ ተለይተው፣ አቅማቸው የተገነባ እና መሠረተ ልማት የተሟሉላቸው አንቀሳቃሾች፣
4) በግንባታ ፕሮጀክቶቹ መሠረታዊ አገልግሎቶችና መሠረት ልማት የተሟላለት የተሰማሩ የሰው ኃይል፣

### 3.3 የተቋራጮችና አማካሪዎች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት አመልካቾች

1) ወደ አለም አቀፍ ጨረታ የገቡ ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር
2) አዲስ የተቋቋሙ የሥ^ ተቋራጮች ቁጥር፣
3) አዲስ የተቋቋሙ አማካሪ ድርጅቶች ቁጥር፣
4) ደረጃቸውን ያሳደጉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር፣
5) የሥራ አቅማቸው ያደገ አነስተኛና መካከለኛ የሥራ ተቋራጮች፣
6) ሥራ ላይ የተሰማሩ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ቁጥር፣
7) የተሻሻለ የምዝገባ አሠራር፣
8) ከህንፃ ሥራ ተቋራጭነት በተጓዳኝ ለጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት በቅተው የሙያ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች ቁጥር፣
    - ከህንፃ ሥራ አማካሪነት በተጓዳኝ ለመንገድ ሥራ ተቋራጭነት በቅተው የሙያ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች ቁጥር፣
    - ለተቋራጮችና አማካሪዎች የተደረጉ የስልጠና፣ የፋይናንስና የማሽነሪ ወዘተ… ድጋፎች፣

### 3.4 የሰው ሃይል አቅም ግንባታ ፕሮጀክት አመልካቾች

1) በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሠልጥነው የሚወጡ የምህንድስና ባለሙያዎች ፆታ፣ ብዛትና ዓይነት፣
2) በምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ባለሙያዎች ፍላጎትና አቅርቦት ዳሰሳ በሙያ ቁጥርና ስብጥር
3) የምህንድስና/ኢንጅነሪንግ ስልጠና ላይ የተደረገ ምጥጥን በሙያ ቁጥርና ስብጥር
4) በኢንዱስትሪው ላሉ ባለሙያዎች የተዘጋጀ መስፈርት፣ የሙያ ዝርዝር እና ደረጃ፣
5) አዲስ የተቀረጸ ወይም የተሻሻለ የትምህርት መርሐ ግብር (Cariculum)'
6) የሰለጠኑ ዝቅተኛና መካከለኛ ባለሙያዎች ቁጥር፣
7) የተጠናከሩ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ቁጥር፣
8) በምዝገባና በምዘና ሥርዓት ያለፉ መለስተኛ ባለሙያዎች ቁጥር፣

### 3.5 የፋይናንስና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት አመልካቾች

1) የተሻሻሉ የብድር ሥርዓቶች፣
2) የተሰጡ የፋይናንስ ድጋፎች መጠን፣
3) የኮንስትራክሽን መሣሪዎች ቁጥር እድገት፣
4) የተሻሻለ የኮንስትራክሽን መሣሪዎች አቅርቦት፣
5) ነባርና አዲስ የተደራጁ የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራይ ድርጅቶች ቁጥር፣
6) አቅማቸውን ያሳደጉ የመሳሪያ አከራይ ድርጅቶች ቁጥር፣
7) አቅማቸውን ያሳደጉ የመካከለኛ የኮንስትራክሽን መሳሪያ ጥገና ድርጅቶች ቁጥር፣

### 3.6 የግንባታ ዕቃዎች አቅም ማሳደግ ፕሮጀክት አመልካቾች

1) ከውጭ ተገዝተው የቀረቡ የፋብሪካ የግንባታ ዕቃዎች ብዛትና ዓይነት፣
2) የተመረቱ የአገር ውስጥ የፋብሪካ የግንባታ ዕቃዎች ብዛት፣ ጥራትና ዓይነት፣
3) የአካባቢ የግንባታ ዕቃ የምርት ዓይነትና መጠን ዕድገት፣
4) የተቋቋሙ የአካባቢ ቁሳቁሶች ማሻሻያና ማስፋፊያ የቴክኖሎጂ ተቋማት ቁጥር፣
5) አዲስ የተገኙ ወይም የተሻሻሉ የግንባታ ቁሳቁሶች ዓይነት፣
6) የተዘረጋ ወይም የተሻሻለ የሎጀስቲክ ሥርዓት፣

## 4. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የአፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት

1) በዕቅዱ በተመለከቱት ግቦች፣ ተግባራትና አመልካቾች መሠረት መደበኛ አገር አቀፍ ግምገማ በየስድስት ወር ይደረጋል፣

2) የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት፣ የሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የዕቅዱ" አፈጻጸም በየወሩ እና በየሶስት ወሩ በተናጠል ይገመግማሉ፣ የግምገማውንም ውጤት ለሚመለከታቸው ያሳውቃሉ፣

3) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች አፈፃፀም ተገምግሞ ደረጃ ይወጣል፡፡ የላቀ አፈፃፀም ያላቸው ሽልማትና ሰርተፊኬት ግብረ መልስ ይሰጣቸዋል፤

4) ክልሎችና ከተሞች የዕቅዱን አፈጻጸም በኢንዱስትሪው ከተደራጁ ማህበራትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይገመግማሉ፣

5) የዕቅዱ አፈጻጸም ያስገኘው ፋይዳና ውጤት፣ ያጋጠሙ ደካማና ጠናካራ ጎኖች፣ እንዲሁም የተገኙ ልምዶች እየተጠኑ ይገመገማሉ፣ ተቀምረው ለቀጣይ የተሻለ አፈጻጸም እንዲውሉ ይደረጋል፣

## 5. አስፈጻሚ አካላት

1) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዕቅዱን ያስተባብራል፣ ለአፈጻጸሙ ስኬት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ እያንዳንዱ የሚመለከተው የሴክተር መሥሪያ ቤት የራሱን ፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸም በሃላፊነት ይመራል፣ በባለቤትነት ይከታተላል፣

2) የክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች በክልል ደረጃ ዕቅዱን በሃላፊነት ያስፈጽማሉ፣ በባለቤትነት ይከታተላሉ፣

3) በከተሞች ደረጃ የከተማ ምክር ቤቶች ዕቅዱን በሃላፊነት ያስፈጽማሉ፣

4) ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የግንባታ ግብዓት አቀናጅ ፎረም፣ የመሠረት ልማት ቅንጅት አስተባባሪ (steering committee) ተቋቁሞ የጋራ ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

5) ባለድርሻ አካላትን በማስተሳሰር ለሚሰሩ ጉዳዮች እንደአስፈላጊነቱ አስተባባሪ ግብረ-ሃይል በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይቋቋማል፣

6) የፕሮጀክት ባለቤቶች ሙሉ ኃላፊነት ወስደው ፕሮግራማቸውን የሚያስፈጽሙ ሲሆን የኮንስትራክሽን አቅም ግንባታ እና ሥራ ዕድል ፈጠራ ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሠራሉ፡፡

## VII. ማጠቃለያ

የአምስት ዓመቱ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስፈፀም በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይል በግብዓት አቅርቦት እንዲሁም በቅንጅታዊ አሠራር ረገድ መከተል ያለብንን አቅጣጫ ስትራቴጅው አመላክቷል፡፡ ሆኖም በሥራ ተቋራጮች ፣አማካሪዎችና ሰው ኃይል ልማት ከፍተኛ ፋይዳ ያለውን የፕሮጀክት አሰጣጥና ስምሪት፣ በሥራዎች ጥራት እና በጊዜ መንዛዛት የሚፈጠረውን የዋጋ ንረት፣ የልማት ዕቅዶቹ የሚፈልጉትን ግብአቶችና የሰው ኃይል ማቅረብ እንዲሁም ግልጽ፣ ተጠያቂነትና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ሥርዓት በመቅረጽ መተግበር አስፈላጊነት በሰፊው ተነስቷል፡፡በኢንዱስትሪው የሚሰማሩ ተዋናዮች ቅንጅታዊ አሰራር ፣የግብዓት አቅርቦት አስተማማኝነት ማረጋገጥ ፣በሰው ኃይል በኩል ብቃቱ በምዘና የተረጋገጠ ባለሙያ ስምሪት ፣በመሳሪያዎች አቅርቦትና ልማት በሃገር ውስጥ የመተካት አቅጣጫ በመከተል የኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚፈጥረውን ሥራ ዕድል ማላቅ ያስፈልጋል፡፡ የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት በተለየ ሁኔታ ለእነዚህ ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ወይም አለመስጠት የዕቅዱን መሳካት ወይም አለመሳካት የሚወስን መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማስፈጸም አቅም ለማጎልበት የተናጠል እና የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አፈፃፀሙን መከታተል ይጠይቃል፡፡በመሆኑም ዕቅዶቻችንን ለመፈጸም በምናደርገው እንቅስቃሴ ፕሮጀክቶች እርስ በእርስ እንዳይጠላለፉና በዘርፉ የሚታየውን ሥር የሰደደ ኪራይ ሰብሳቢነት ከሥር መሠረቱ በመናድና በማፈራረስ ተወዳዳሪ ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማስፈጸም አቅም ግንባታ የመጀመሪያ ምዕራፍ ስራ መሠረት የሚጣል ይሆናል፡፡

ስትራቴጂው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሂደት የሚቀሰሙ ምርጥ ተሞክሮዎች እያሰፉ ፕሮጀክቶች የአገር ውስጥ አቅም መፍጠሪያ ሆነው በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ዘርፉ የሚያበረክተው ድርሻ ማሳደግ ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል የዲዛይን ጥናት ውጤቶች የሃገሪቱን አቅም ያገናዘቡና ወጪ ቆጣቢ፣ ጥራት ላይ የማይደራደሩ፣ ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ ፣ ተቀባይነት ባለው ጊዜ በማጠናቀቅ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገታችን ለማረጋገጥ የአምስት ዓመቱ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሳካ መረባረብ ይኖርብናል፡፡